
# ሰላዩ ሬሳ

አስገራሚው የእንግ
ሊዞች የስለላ ታሪክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከ ማሞ ውድነህ

# ሰላዩ ሬሳ

ከኤዊን ሞንታጉ ተጽፎ ፤

ማሞ ውድነህ

እንደ ተረጐመው

ታህሣሥ ፲፱፻፸፰ ዓ. ም.

አ. አ. ተራመድ ማ/ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

መጀመሪያ በ፲፱፻፸፯ ታተመ
ሁለተኛ በ፲፱፻፹፰ ታተመ

እንደገና ለማሳተም መብቱ የተጠበቀ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማ ብ ራ ሪ ያ

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የአክሲሶች (ጀር መን ኢጣሊያና ጃፓን) ወታደራዊ ኃይል ዓለምን ከስጋ ትና ከጭንቅ ላይ በጣለበት በዚያ ጨለማ ዘመን ውስጥ ከመሣሪያ ኃይል ይልቅ የመረጃ ኃይል የቱን ያህል ታላቅ ውጤት እንዳስገኘ በየጊዜው በልዩ ልዩ ጽሑፎችና ፊል ሞች ተመልክተናል ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምናየው የመረጃ ውጤት ግን ከሁሉም ላቅ ያለ እንግዳ ታሪክ ሆና ለመላው ዓለም ቀርቧል ።

ሬሳ ከሟች ቤተሰብ ለምኖ ደንበኛ ወታደራዊ ልብስ አልብሶ በየኪሶቹ ሐሰተኛ ሓሳብ ያዘለ ጽሑፍ አስቀምጦ ያም ጽሑፍ ከጠላት እጅ እንዲደርስ አድርጎ የጠላትን ጦር በልዩ ልዩ ስሜት አመሰቃቅሎ በዘመቻ እቅድ በታ ትኖ ጠላትን ድል ማድረግና የሀገርን ነፃነት ማስከበር ወገንን ከአሰቃቂ እልቂት ማትረፍ በእርግጥ ከችሎታም የላቀ ችሎታ የሚገለጽበት የተራቀቀም ችሎታ ነው ።

ይህ ታላቅ ውጤት ያተረፈ ዘዴ የፈለቀውም ከአ ንድ ባለሙያ ጭንቅላትና ጭንቀት ነው ። የሙያውና የሀ ገሩ ፍቅር በብርቱው ሲያሳስበው የነበረው ባለሙያ ረቂቅ ሓሳብ በሥራ ላይ ሲገለጽ በሰሜን አፍሪቃና በሜዴት ራኒያ አካባቢ የነበረውን የጦርነት ታሪክ ሊለውጠው ችሏል ። እንግዲህ አንድ ሰው ሊብዙዎች ልማትም ሆነ ጥፋት ምክንያት እንደሚሆን ይህ ታሪክ በይበልጥ ያስረ ዳናል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌ/ኮማንደር ሞንታጐ የተባለ እንግሊዛዊ የመረጃ ባለሙያ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ረቂቅ ሐሳብ አፍልቆ በድርጊት እንዲገለጽም ከልብ ጥሮበት የተባበሩት መንግሥታት የጦር ኃይል ያለምንም ግጭት የናዚዎች ኃይል ተከማችቶባት የነበረችውን ሲስሊን እንዲይዝ በማድረጉ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ታሪክ ውስጥ ተጨማሪ ውጤት አስገኝቷል።

በዚህ መጽሐፍ እንደምንመለከተው እንግሊዞች በናዚ ላይ ድል ለማግኘት ሲሉ የፈፀሙት የተራቀቀና ለጀሮም እንግዳ የሆነ የማስመሰል መረጃ ውጤት ሰፊ ትምህርት ያዘለ ነው።

ከሁሉ አስቀድሞ ለመማርም ሆነ ለመሥራት የሚሰማሩበትን ሙያ መምረጥ ያስፈልጋል። የተሰለፉበትን ሙያም መውደድ ማክበርና መንከባከብ ለሚያመረቃ ውጤትም መጣር ይገባል። ቀጥሎም ሙያው የሚስፋፋበትን የሚጠነክርበትን ለትውልድም የሚተላለፍበትን ስልት ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆንም የሙያዎች ስፋትና ጥልቀት እየዳበረ የሕዝብና የሀገር አንድነቱና ብልጽግናው እየተደላደለ ይሔዳል። ለሀገር ዕድገትና ብልጽግና የሙያዎች መከበርና መስፋፋት መሠረቱ ነውና።

የዋህ መስሎ ያላዩና ያልሰሙ መስሎ ያላሰቡና ያልነቁ መስሎ በሀገርና በወገን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የጠላት ውጥኖችን ተከታትሎ ማክሸፍና እንበለ ይሉኝታ ለትክክለኛነት መሰለፍ የዜግነት ብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሆን የሕልውናም ግደታ መሆኑን ይህ መጽሐፍ ከያዘው ታሪክ ላይ ለመረዳት እንችላለን ።

ይህ መጽሐፍ "THE MAN WHO NEVER WAS" (ዘማን ሁ ኔቨር ወዝ) በሚል ርእስ መታተም ከጀመረበት እ-ኤ-አ- ከ1953 ዓ/ም ጀምሮ እስከ 1968 ዓ/ም ድረስ ማለት በአስራ አምስት ዓመታት ውስጥ አስራ አንድ ጊዜ ታትሟል ። በፊልምም ተሠርቶ ታላቅ አድናቆት አትርፏል ።

በርካታ ታላላቅ ሊቃውንት የደከሙበትን የጦር መሣሪያ ክምር ከፍተኛ የጦር መሪዎች የተሰለፉበትን የጦርነት ስልት ሒትለርም ጓጉቶበት የነበረውን ድል የመጨበጥ ተስፋ ያከሸፈበትን የአንድ የተራቀቀ ባለ ሙያ እቅድና ሥራ ማቅረብ ለሀገራችንም ታላቅ ዕውቀት የሚያስገኝ እንደሚሆን በመተማመን ለወገኖቼ ሳቀርብ ልባዊ ደስታ ይሰማኛል ።

ተተኪዎቻችንም በዚሁ ጉዳይ እንዲተጉበትና ታላላቅ ትምህርትና ዕውቀት የሚገኙባቸውን ጽሑፎች እየተረጐሙና እያቀነባበሩ እንዲያበረክቱ በዚች አጋጣሚ አደራዬን ላስተላልፍ እወዳለሁ ።

ተርጓሚው ማሞ ውድነህ

ህዳር ፲፱፻፸፫ ዓ/ም

አዲስ አበባ

t.me/OLDBOOKSPDF

## ብርቱ ምሥጢር ።

## የማስመሰል ዘመቻ ።

፩ መሠረተ - ሐሳቡ ፤

ጀርመኖች የሠፈሩበትን የሜዲትራኒያ የመከላከያ እቅዳቸውንና የጦር ሠፈራቸውን እንዲለውጡ ለማታለልና የተባበሩት መንግሥታት ጦር ሲሲሊን በተቃና ሁኔታ ለመያዝ እንዲችል ለማድረግ ነው ።

፪ ዘዴው ፤

አንድ ሰው ያልታወቀ ወታደር መመልመልና የሮያል ባሕር ኃይል አባል እንዲመስል የሻለቃነት ማዕርግ ማልበስ የምሥጢር መልእክትም እንዲይዝ ማድረግ ከዚያ በኋላ ከገለልተኛዋ እስፔይን የባሕር ጠረፍ እየተንሳፈፈ እንዲገኝ በባሕር ውስጥ ጠላቂ መርከብ መውሰድ ቀጥሎም ዋናው ተስፋና ጸሎት ይህንኑ ሬሳ እስፓንያውያን ከነ ሐሰት መልእክቱ አግኝተውት ለናዚዎች እንዲያስረክቡት ነው ።

፫ ውጤቱ ፤

አጅግ የሚያጓጓው የ፪ኛው የዓለም ጦርነት የስለላ ታሪክ ይገኝበታል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# መ ግ ቢ ያ

ጠላትን አስመስሎ ማታለል ማጭበርበርና ግራ ማጋባት ከጦርነት ስልቶች አንደኛው ዘዴ ሆኖ ኑሯል፣ ምናልባትም ቀደም ሳይል አይቀርም እንጅ በትሮይ ከተማ መግቢያ በር ላይ በፈረስ ምስል ተሠርቶ ቁሞ በተገኘው ምስል ውስጥ የነበሩት ግሪኮች ያን ሁሉ እልቂት በጠላቶቻቸው ላይ አድርሰው ከተማዋን ካጠፉዋት ወዲህ ተመሳሳዩ የማታለልና የማስመሰል ተግባር በየጊዜው ሲፈጸምና ውጤትም ሲሰጥ እንደኖረ የታወቀ ነው።

ይኸው የማታለል ዘዴ ለብዙ ዘመን ሲሠራበት ቢኖርም ቅሉ አዳዲስ ብልሃት አመንጭቶና አስመስሎ ጠላትን ለማወናበድ አቅጣጫውን ለማስለወጥ ኃይሉንም ለማዳከም ሐሳቡን ለማወቅ ቀላል አይደለም።

ያወጣውን ብልሃት በትክክል ከሥራ ላይ አውሎ ውጤት ለማግኘት ደግሞ ብርቱ ጥንቃቄና ጥረት ይጠይቃል፤ ያለዚያ ግን ጠላትን ለማታለል የሚደረገው ድካም ከንቱና አደገኛም ይሆናል።

በ፪ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት የጦር አዝማቾች ከቱኒዚያ ጦርነት በኋላ በሲስሊ በኩል ዘልቀው ኢጣሊያን ለመያዝ ቍርጥ ሐሳባቸው ሆነ።

ወደ ሰሜን አፍሪቃ ለመዝመት የነበረንን ምርጫና ግዴታ ጠላት ተረድቶ፤ ኃይሉን አጠናክሮ እንደሚጠባበቀንም ተሰምቶናል። ከዚያ ምሽግና ሠፈርስ እንደምን ወደ ኋላው መመለስ ይቻላል?

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ቀን ወደ ማታ የማስመሰያው ዘመቻ እቅድ ሲቀ ርብልኝ በሁኔታው በመጠኑ ተጠራጠርኩ ፤ ቢሆንም ጉዳ ዩን ለችፍ አብ ስታፍ ተውኩለት ፤ እርሱም በመሠረተ ሐሳቡ ተስማማበት ፣ ከዚያ በኋላ ይህንኑ ሐሳብ ያመነ ጨው ሌ/ኮማንደር ሞንታጉና የሥራ ጓደኞቹ ሙሉውን ኃላፊነት ወስደው በእቅዱ መሠረት ትግባራቸውን ማከና ወን ቀጠሉ ። እቅዳችን ከገመትነውና ከተጠራጠርነው ልቆ ውጤት ሰጠ ። የጀርመንን የጦር ኃይል ለመከላከልና በአውሮፓም ውስጥ ለመሠራጨት የሚያስችለውን መሥ መር ተከተልን ።

ሌላው ቀርቶ የጀርመንን የባሕር ኃይል ከሲስሊ ለማ ስወጣትም ተችሏል ። ይህም ደግሞ አስደናቂ የሥራ መቀ ላጠፍ ሆነ ። ሲስሊንም ለመያዝ የቻሉት የጦር ኃይሎቻ ችን ደስተኞች ለመሆን በቁ ።

የምሥጢራዊ ዘመቻ ታሪክ ብዙውን ጊዜ በግልጽ ተዘርዝሮ ለሕዝብ አይገለጽም ፤ ቢሆንም በተለየ ቅልጥፍ ናና ጥንቃቄ ስለ ተከናወነው የጦርነት ታሪክ ሁሉ ጉዳዩ የሚመለከተውንና የሚያሳስበውን ማስደሰቱ አይከድም ፤ ለሌሎችም አንባቢዎች በእርግጥ አስደናቂ እውነተኛ የን ባብ እርካታ ይሰጣቸዋል ። ምክንያቱም ከሐሳብ ወለድ ታሪክ በይበልጥ እውነተኛ ታሪክ ተፈላጊና ትምህርት ያለው በመሆኑ ነው ።

ጀኔራል ሎርድ ኢስማይ
የሰሜን አትላንቲክ ስምምነት ዋና ጸሐፊ ።

ፓሪስ ሰኔ ፺ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

t.me/OLDBOOKSPDF

# የደራሲው ማስታወሻ

ይህ እውነተኛ ታሪክ የሚያስረዳው ከ፲፱፻፷፮ - ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ የተፈጸመውን የዘመቻ እንቅስቃሴ ነው ። በታሪኩ እውነተኛ ትረካ ላይ የኔ የራሴ የግል አስተሳሰብና እውቀት ከዋናዎቹ ማስረጃዎችና ጥናቶች ጋር የተጣመረ ነው። ማስረጃዎቹም ከዐሥር ዓመታት በፊት ከተጠራቀሙት ጉዳዮችና ጥናቶች የተገኙ እንጂ አንድ ግለኛ ሰው የራሱን ሥራ ወይም ተባባሪ አባልነት ለማሳወቅ ሲል ብቻ ከአጠራቀማቸው የተወሰዱ አይደሉም ።

ሐሳብ ወለዱ ትረካ በዘመቻው ሥራ ላይ ተደምሮ ሲወራ ስለ ነበረ እኔም ይህንኑ የፈጠራውን ክፍል ተመርኩዤ ለመጻፍም ሆነ ለመናገር አልፈለግሁም ነበር ። የማታለሉ ዘመቻ የተፈጸመባቸው ጀርመኖችም የሚያቀርቡትን እውነተኛ ማስረጃም ማግኘት አስፈልጎኝ ነበር ። ይህ ሁሉ ከተጣራና ከተቀነባበረም በኋላ ሁላችንም የታገልንበቱ የማታለል ዘመቻ ታሪክ የምሥጢርነቱ ጊዜ በማለቁ እውነተኛው ታሪክ ለመታተም በቃ ።

ይህነኑም እውነተኛ ታሪክ ባለሥልጣኖቹ አምነው ተቀብለውት አረጋግጠውታል ። ቢታተምና ሕዝብ እንዲያውቀው ቢደረግም የሚያስከትለው ጥፋት እንደማይኖርም መርምረውታል ። ይልቁንም ገሚሱ ታሪክ በተገለጸላቸው ጸሐፊዎች ቢቀነባበር የሚያስከትለውን ጉዳት ተረ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድተጠ.ታል ። በዚህ ምክንያት እውነተኛውን ታሪክ በሙሉ እንዳሳትም ፈቃድ ተሰጠኝ ።

ይህ አስደናቂ ዘመቻ የተቀነባበረውና የተፈጸመው በቡድን ሥራ ነው ። ተግባሩን ከግብ ካደረሱት ሰዎች መካከልም ጥቂቶቹ ዛሬም ድረስ በሥልጣን ላይ ስለሚገኙ የአንዳንዶቹ ስም ተደብቆላቸዋል ።

ይህን ታሪክ በማንበብ ጠቃሚ ጉዳይ ሊገኝበት ይቻላል ። ምናልባት የአንድ ምሥጢራዊ ሥራ ጉዳይ በሕዝብ ጆሮ ይሠራጭ ይሆናል ። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በፀጥታ ክፍል ላይ ወቀሳ ሊሰነዝርም ይችገርበታል ፤ ይህም በኛ የመረጃ ድርጅት ላይ የደረሰ ነው ። በዚህም ጊዜ የፀጥታ ድርጅት ከንቱ ወይስ ብልጣ ብልጥ ነው ? የሚል ትችት ይሠነዘራል ። ሁኔታዎችን ለማጣራትና ለማደነጋገር ይረዳል ።

የታሪኩን መግቢያ የጻፉልኝ ሎርድ ኢስመይንና እኔንም ያደፋፈሩኝ የማስመሰሉም ዘመቻ በሚገባ እንዲከናወን የደከሙትን የሥራ ጓደኞቼን ሁሉ በዚህች ዘለዓለማዊነትን በምትቀዳጀው ጽሑፍ ውስጥ ፤ ላመሰግናቸው እወዳለሁ ።

ኤዊን ሞንታጉ (፲፱፻፶፫) ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# የሐሳቡ ጀማሪ

በእስፐይን ከተማ ሂውልባ በተባለችው ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው የመቃብር ቦታ አንድ እንግሊዛዊ ሰውዬ ለዘለዓለሙ ተጋድሟል ። እርሱም በ፲፱፻፴፭ ዓ. ም. በፀደዩ ወራት በጉምና ቅዝቃዜ ተሸፍኖ በነበረው ኢንግላንድ ውስጥ የሞትን ጽዋ ብቻውን የተቀበለ ነበርና በዚያም የመቃብር ቦታ ብቻውን አርፏል ።

በሙሉ ወታደራዊ ክብር የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በእስፐይን ውስጥ ሲፈጸምለት በመጠኑ ትውስት አግኝቶ ነበር ። እርሱ ግን ያን ክብርና አጋጣሚ ቀርቶ ከሞተ በኋላ ሬሳው ለተባበሩት መንግሥታት አገልግሎት ውሎ በብዙ መቶ የሚቈጠሩትን አሜሪካውያንና እንግሊዛውያን ሕይወት ማትረፉን አላወቀውም ። አላሰበውም ።

ሰውየው በሕይወት በነበረበት ዘመኑ ለሃገሩ ያበረከተው አገልግሎት መጠነኛ ነበር ፤ ከሞተ በኋላ ግን ብዙዎቹ በሕይወታቸው ከሚፈጽሙት የበለጠ ታላቅ ተግባር ፈጽሟል ።

* * *

እውነተኛውን የታሪኩን መሠረተ - ሐሳብ ያመነጨው ጆርጅ (እውነተኛ ስሙ አይደለም) ነው ። እኔና እርሱ በየሳምንቱ እየተገናኘን የዘመቻውን ድርጅት የፀጥታ ጉዳይ የሚያዘጋጀው ደርግ አባሎች ነበርን ። ከየቦታው ተለቃ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅሞ በሚቀርብልን ልዩ ልዩ መረጃ ላይ እንወያይበታለን እንከራከርበታለንም ። ወሬዎቹ የሚጠረቃቀሙትም ከሃገር ውስጥ ልዩ ልዩ የመረጃ ክፍሎችና ከጠላት አገሮች ጭምር ነበር ።

ይህንና የመሳሰሉትን መረጃዎች እያጠረቃቀምን የተባበሩት መንግሥታት የጦር ኃይል እንዲያውቀው እናደርጋለን ። በአስቸኳይና በጥርጣሬም የሚፈጸም አልነበረም ። ከብዙ ጊዜያት በኋላ ሊደርስ የሚችለውን ሁሉ ማነፃፀርም ነበረ ።

የኛ የምሥጢር ሥራ እንዳይወጣ እንዳይሰማ እንዲሁም የጠላት የመረጃ ድርጅት እቅዳችንን አስቀድሞ እንዳያደናቅፈው መከላከልና መቈጣጠርም ነበረብን ፤ ጠላት በልዩ ልዩ ዘዴዎች አንዳንድ ጉዳት ያደረሰብን በመረጃ ውጤት በመሆኑ ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይደርስብን የወደፊቱን አቋም ሁሉ ማቀነባበር መቈጣጠርና መጠንቀቅም ከፍተኛውን ጥረት የጠየቀን ሁኔታ ነበር ።

ኃላፊነቱ ቀላል አልነበረም ፡ ቢሆንም በደርጉ (በኮሚቴው) ውስጥ በእርግጥ የታመኑና ችሎታቸው የላቀ አባሎች ነበሩበት ፤ አባሎቹ ነባር የጦር አለቆች ብቻ ሳይሆኑ አዳዲስ መኰንኖችና የረቀቀ ችሎታ የነበራቸው ሰላማዊ ሰዎችም ነበሩበት ። ከየክፍሉ የተውጣጣን ስለ ነበርን ከየትኛውም አቅጣጫ የሚነፍሰው ወሬ አያመልጠንም ነበር ። ሁኔታዎችን ጠልቀን የምንረዳበት ከጥናት ያገኘነው ዕው



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀት ቢኖረንም ያልደረስንበቸው አንዳንድ ጉዳዮች ደግሞ ነበሩብን ።
በጦር ኃይል ከተያዙት የአውሮፓ ሃገሮች በተላኩልን የመረጃ ምሥጢሮች ላይ በምንነጋገርበት ጊዜ ጆርጅ ይህ ታሪክ የተፈጸመበትን ሐሳብ ወይም ምኞቱን አቀረበልን። በጉዳዩ በየጊዜው በተነጋገርንበት ቊጥር በትክክለኛነቱ ወይም ደግሞ ጀርመኖች ወደ ተባበሩት መንግሥታት የጦር ኃይሎች እንዲሠራጭ ብለው የጠነሰሱት ተንኰል ይሆናል በማለት በሁለቱ ጉዳዮች ግራ ተጋባን ።
ጆርጅ አስቸጋሪና ግልጽ የሆኑ ሁኔታዎችን በማቅረብ ረገድ የታወቀ ሰው ነበር፤ አእምሮው አስደናቂ ነገሮች ያፈልቅለታል። ተከታትሎ ለፈጸማቸውም ቀዋሚ ውጤት ያገኝባቸዋል ። የእርሱ ሐሳቦች ወይም የጥናት ውጤቶች ሲሰነዘሩ ለመጀመሪያ ጊዜ አጠራጣሪዎች አስቸጋሪዎች መያዣ መጨበጫ የሌላቸው ይመስላሉ ። ሲያምሰለስሉዋቸው ደግሞ ግልጽልጽ ያሉ ይመስላሉ ። ግን በሚገባ ለተመራመረባቸውና ላምሰለሰላቸው በእርግጥ ግልጽና ትክክለኞች ጉዳዮች እንደሆኑ ሊረዳቸው ይችላል ። ቢሆንም ያ የዚህ ታሪክ መሠረት የሆነው ጉዳይ ሲቀርብልን ትክክለኛ የጥናቱ ውጤት ይሁን ወይም ጀርመኖች ስለ ዚሁ ጉዳይ የተመደበውን ሰላይ ማርከውት በእርሱ በኩል ያሠራጩት፤ ያለዚያም ለጆርጅ እንዲደርስ በዘወርዋራ ዘዴ ያቀባበሉት የትኛውን መሥመር የተከተለ ሐሳብ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆነ ለማጣራት ግራ ተጋብተንበታል ። ለጦር አለቆች ማነኛውም የምሥጢር ሰነድ ሁሉ በአይሮፕላን ተጓጓዞ የተላከ እንደሆነ በጠላት ተመትቶ ይወድቅና ምሥጢሩ ከጠላት እጅ ስለሚገባ ምሥጢር ነክ ሰነድ በአይሮፕላን እንዳይላክ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ጆርጅ አልረሳውም ። ነገሩን ለመጀመርና ለማጣራትም ያህል አንድ ጉዳይ ሠርተን ጀርመኖችን መሞከርና አውቀን በሠራነውም ጉዳይ ላይ የሚያደርሱትን ተቃውሞ ማወቅ አለብን የሚል ሐሳብ ጆርጅ አቀረበልን ።

አቅጣጫቸው (ምርጫቸው) በሚከተሉትም ጉዳይ ላይ የሚያደርጉትን ተግባር ማወቅ ተገቢያችን ሆነ ። በሬዲዮ ዘዴ ወሬ ማስተላለፍ የሚችል መሣሪያ ፈረንሳይ ውስጥ ከአየር ላይ ብንጥልና ያም መሣሪያ ተግባሩን ቢቀጥልለኛም ዜናዎችን ቢያስተላልፍልን መሣሪያውን ይዘው የሚያታልሉን ጀርመኖች ወይም ወዳጆቻችን ፈረንሳዮች ለመሆን ስለሚችሉ ማነኛነታቸውን ለይተን ለማወቅ እንችልም (ሲል ጆርጅ ሐሳቡን በማቅረብ ዝርዝሩን ጉዳይ ቀጠለ)።

ዳሩ ግን ይህ መሣሪያ ከሬሳ ጋር ታስሮ ቢላክና ከአየር ላይ በመጥፎ አኳኋን በጃንጥላ ወድቆ እንደሞተ ሰው ቢታወቅ ቀላል ይሆንልናል ።

ይህ ሆኖ ቢገኝ የደረሰውን ሁኔታ አብራርተው ፈረንሳዮች ሊነግሩን ይችሉ ይሆናል ፤ ጀርመኖች ግን ነገሩን ለመደባበቅና የተላከውም ሰው እንዳልሞተ አስመስለው በመሣሪያው ሊሠሩበት ይሞክራሉ ። እርግጥ ነው ይህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘዴ ፍጹም አዲስ ነው ። ግን ብዙ ችግር የሚያስከትል ብንና በማንኛውም መስመር ቢሆን ዋጋ ያለው ውጤት የሚያስገኝልን ይሆናል ። ስለዚህ ከመከከላችን የሞተ ሰው (ሬሳ) የምናገኝበትን ዘዴ የሚነግረን አለ ? ሲል ንግ ግሩን በጥያቄ ደመደመው ።

ይህ ሐሳቡ የተሻለ መስሎ አልታየንም በፍጥነት አራ ከስንበት ። ከሁሉ አስቀድሞ የምሥጢር ሠራተኞች በድ ብቅ ቃላት መልእክታቸውን የሚያስተላልፉበትን ማስረጃ ጽሑፍ ይዘው እንዳይሄዱ ግልጥ ነው ። ስለዚህ የሞተ ውን ሰው በሕይወት እንደሚገኝ አስመስለው መልእክት ማስተላለፍ ጀርመኖች እንደምን ይቻላቸዋል ? ደግሞም የአየር መንሳፈፊያው መሣሪያ በሚገባ ሳይሠራ ቢቀር የተሸከመው ሰውም ሆነ ዕቃ በኃይል ከመሬት ላይ ይፈ ጠፈጣል ። ሰውም የሆነ እንደሆነ ሬሳው እንኳ በኃይል ሊጐዳ ስለሚችልና ስለሚቈራረጥ ምን ጊዜም ቢሆን አስ ቸጋሪ ይሆናል ፤ ለክትትልም ያመቻል ስለዚህ ሬሳ ከአየር ላይ በመጣል የሚገኘው ውጤት ዋጋ ቢስ ነው ። በአጭሩ ሬሳው ሲመረመር መሬት ከመንካቱ በፊት ሙቶ እንደ ነበረ ለማወቅ ይቻላል ።

ሬሳም እንኳ ቢገኝ (ይኸውም ያጠራጥራል) ከአየር ላይ ወድቆ የሞተ ሰው ለማስመሰል የሚኖረን ምርጫ የተወሰነ ይሆናል ። በዚህ ረገድ ጉዳዩን ከመረመርነውና ከተነጋገርንበት በኋላ የጀርጅ ሐሳብ ውድቅ ሆነ ፤ ከዚያም

t.me/OLDBOOKSPDF

በመሠረታዊው ጥናት ላይ መወያየት ቀጠልን፤ ነገሩ ትክ ክለኛ ነው አይደለም? በሚል ጥያቄ ተከራከርንበት፤ ግን የጆርጅ መሠረተ ሐሳብ ከጥቂት ወራት በኋላ ውጤት ሰጠ።

በ፲፱፻፷፱ ዓ. ም. በበጋው ወራት የጦርነቱ ችቦ የሚ ለው ንቅናቄ ተጀምሮ ስለ ነበረ የኛም ደርግ እጅግ ከባድ ሥራ ጋር ተጋፈጠ፤ ሰሜን አፍሪቃን ለመውረር የነበረው የዘመቻ እቅ፡ ቅድሚያ ተሰጥቶታል። በመጠነኛ ዝግ ጅት ሲከናወኑ የነበሩትን የዘመቻዎች ፀጥታ ለመጠበቅ ስንል በፈጸምነው ልምምድ መሠረት የነበሩንም መጠነኛ የፀጥታ ክፍል ወታደሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ከብርቱ ፈተና ላይ ወደቁ።

ለፀጥታ ጥበቃ ሲባል ያ ሁሉ ከባድ ተግባር ቢፈጸ ምም ቅሉ አሳሳች ጉዳይ ለመፈጸም እቅድ ወይም ሐሳብ የተጀመረ መሆኑን የጠላት የመረጃ ሠራተኞች እንዳይደ ርሱበት ለመከላከል ደግሞ ምን ጊዜም አስቸጋሪ ነበር።

ከሁሉ በፊት የተባበሩት መንግሥታት ጦር እስከ መቸውም ድረስ ቢሆን ሁኔታውን ሁሉ በሩቅ ሆኖ በጽ ሞና ሊመለከተው እንደማይችል ለማንም ቢሆን ግልጽ ነበር። በአንድ አቅጣጫ ዘምቶ ጦርነቱን እንደሚገፉበት እርግጠኛና ተገቢም ነበረ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለውጭ ሃገር የመንግሥታት እን ደራሴዎችና የዲፕሎማቲክ ሠራተኞች ከዚህ አትለፉ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚል ገደብ ሊኖርባቸው አይችልም ። በየሃገሩ እየተዘዋ ወሩ ከሕዝብ ጋር መገናኘትና መነጋገር ይችላሉ ። በዚ ህም ጊዜ የጦር መርከቦችና የምድር ጦር ኃይሎች ለዘ መቻ ከሃገራቸው ከመነሳታቸው በፊት የሚያደርጉትን ዝግጅት ከሚያውቁና ከተመለከቱ ሰዎች ጋር ዲፕሎማ ቶቹ ሊገናኙም ሆነ ሊነጋገሩ ይቻላቸዋል ። እኛም ደግሞ የዲፕሎማቲክ መልእክተኞች እንዳይገቡብን ሃገራችንን በገለልተኝነት ልንደብቃት አይቻለንም ነበር ።

ስለዚህ የእንግሊዝ ወዳጅ የሆነ የዲፕሎማቲክ ሰው እንኳ ሌላ የሥራ ሥምሪት ሊኖረው ይችላል ። በሃገራችን ውስጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እያብራራ ለራሱ መንግ ሥት ሪፖርት ማስተላለፍ ሊኖርበት ነው ፤ ሪፖርቱንም ወደ ሃገሩ ከስተላለፈ በኋላ አንድ በከፍተኛ ገንዘብ የተ ገዛ ወይም በመሠረተ ፍልስፍና ያመነ ባለሥልጣን ወሬ ውን ለጀርመኖች ለማሳለፍ እንደሚችል አይጠረጠርም ።

በሮኛ ረድፍ ደግሞ ነጋዴዎችና ባሕረኞች ከሃገረ እንግሊዝ ወደ ሌላው አህጉርና ሃገር ይመላለሳሉ ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የጦርነት ዝግጅትና ንቅናቄ መኖሩን ከጀርመን ሰላዮች ለመከላከል አይቻለንም ነበር። ልናደርግ የምንችለው መከላከል ቢኖረን ግን መቼ እና በየት የሚሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ማድበስበስ ነበር ። የሰሜን አፍሪቃ ጦርነት እስከ ተጀመረበት ጊዜ ድረስ የተባበሩት መንግሥታት ጦር ከማነኛውም ወረራ የሚጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለልባት በቃ አውሮፓ ውስጥ አልነበረውም ፤ በሰሜን አፍሪቃ ውስጥ ሲካሄድ የነበረውንም ጦርነት ስንገፋበት የነበረው በስዊዝ ካናል አካባቢ ተከማችቶ የነበረውን ጦራችንን እያዘዋወርንና እያመላለስን ነበር ።

በዚሁ ሁኔታ ምክንያት የተባበሩት መንግሥታት ጦር በሆነው ሁሉ አቅጣጫና ሁናቴ ጦርነት የማይጀምርበት ምንም ምክንያት አልነበረውም ። በዚህ ነገር ጀርመኖች ቢያምኑበትም ቅሉ ጦርነቱን ለመጀመር በኖርዌ ወይም ጠቅላማዎቹ ሃገሮች ባንደኛው ያለዚያም ፈረንሳይ ውስጥ ገብተን የጦር ኃይል እንደምናከማች አድርገው ጀርመኖች በእስፔይን በኩል ለመግፋት ሳንሞክር እንደማንቀር ተረድተውታል ።

ምናልባትም የጀርመንን የባሕር ኃይል ለመቋቋም የሚደረገውን ጦርነት ለመረዳት ስንል ካናፈሰን ያለዚያም አዘረሰን ይህም ባይሳካልን ሊቢያን ይዘን የሮሚልን ኃይ ል አልፈን አልፈን በአቅራቢያነት ሳንደበድብ እንደማን ቀር አድርገው ጀርመኖች ይጠባበቁናል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ከግብጽ በስተቀር በጀርመን ኃይል በተያዘው የአውሮፓ ክፍል ወይም ገለልተኛ በሆነ ሃገር ገብተን ጦር ነቱን ለመጀመር የሚያስችለው ዕድል አልነበረንም ፣ በዚ ሀ ሁሉ ምክንያት የኛ ድርግ የነበረበት ኃላፊነት የዳይፒን ወይም የሎፎቴን ደሴቶች ለመያዝ የምናደርገው ጦርነት እንደዚሁም የምናወጣው የጦርነት ስልት ቀኑና ሁኔታው በጠላቶቻችን ዘንድ እንዳይታወቅ መታገል ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ለማድረግ ደግሞ ለዘመቻ ይዘጋጁ በነበሩት ወታደሮቻችን የሚሄዱበትን የውጊያ አቅጣጫ አስመስ ለን በማስወራት ወሬው ወደ ጠላት እንዲደርስ ማድረ ግም ነበረብን ። ያንኑ የሐሰት ማደናገሪያ ወሬአችንን ለመ ደገፍ ስንል ደግሞ ለጦሩ የፀሐይ ሙቀት መከላከያ ቆብ እንዲሠራለት ማዘዝ መጻፍ ወደ ሌፎተን ደሴቶች የሚዘ ምት መሆኑም የተረጋገጠ ማስመሰል፤ እና ይህን የመሳሰ ለው ዘዴ እንዲታወቅ ማድረግ ቀጥለንም ወሬው ከሃገራ ችን ሾልኮ እንዳይወጣ የምንጣጣር መምሰላችንን ማሳ ወቅ ነበረብን ።

ዋናው እምነታችን የጦር ኃይላችንን ፀጥታ በተቻለ መጠን መጠባበቅ ቢሆንም ቀጥሎ ደግሞ እውነተኛው የጦርነቱ አቅጣጫና ስልታችን እንዳይገለጽና ለጠላታችን ጆሮ እንዳይደርስ መታገል ነበር ። በዚሁ የማስመሰል ዘዴ ቀጠልንበትና ሌላው እንኳ ቀርቶ፤ በሰሜን አፍሪቃ የጦ ርነቱ ችቦ የተባለው ስልታችን ተጀምሮበትም በነበረበት ሰዓት ያንኑ የማደነጋገሩን እቅዳችንን እንሠራበት ነበር ። ከልዩ ልዩ የመረጃ ድርጅቶቻችን ሲቀርብልን የነበረውን ዜና በማጥናት ጀርመኖችም ሲፈጽሙት የነበረውን በመ ከታተል በፈጸምነው የማስመሰል ወሬ ጠላት ግራ እንደ ገባውና ዋናው ውጊያ የምንጀምርበቱንም አቅጣጫ ለማ ወቅ እንዳልቻለ ተረዳነው ።

የጦርነቱ ችቦ የተባለው የዘመቻ እቅድ ከተጠናቀቀ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልን በኋላ ግን የነበረብን ችግር ሌላ ጉዳይ ያዘለ ሆነ ።
ጦርነቱ ሲካሄድ በነበረበት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት
ጦር የሰሜን አፍሪቃን አካባቢ በቍጥጥሩ ሥር ማዋልና
እንደዚሁም ሚዛኑን ሳያዛንፍ ጠብቆ በፈረንሳይ ውስጥ
ሌላ የጦር ግንባር ለመጀመር መዘጋጀትና ብቁም ሆኖ
መገኘት ግዴታው ከሆነ የጊዜ ውሳኔ ላይ ደረስን፤ ያነንም
የጦርነት አቅጣጫ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ለስላሳው የአውሮፓ ገሚስ አካል" ብለውታል። በዚህ ምክንያት የኛ ደርግ
ዋናው ኀላፊነቱ ከጦር ኃይሉ አዝማቾችና ከአሜሪካ የጦር አዛገሮች ጋር በየጊዜው መወያየትና ዘዴዎችን ማቀነባበር ነበር። በሐሳብ ያለመግባባት ሰንቅፋት በጦር ባለሥልጣኖቹ መካከል እንደነበረ እናውቃለን። ቢሆንም በታለመው ቦታ ላይ ጦርነቱ መጀመር እንደነበረበት በትክክል
ተረድተነዋል። ስለዚህ ጦርነቱ ሲጀመር የተመደብንበትን
ኃላፊነት ከሥራ ላይ ለማዋል የኛ ደርግ ዝግጅቱን ማሳመር ነበረበት።

የሰሜን አፍሪቃን አካባቢ የተባበሩት መንግሥታት
ጦር ከያዘ በኋላም በዚያ የነበረውን ጦራችንን ወደ እንግሊዝ አዛውረን ፈረንሳይን ለመያዝ እንደማንችል የታወቀ
ነበር፤ ከዚያ የዙሪያ ጥምዝ ጉዞ ሌላ ደግሞ ከኃይላችን
ገሚሱ የሜዲትራኒያን አካባቢ መያዝ ነበረበት። ምክንያቱም በባሕሩ አካባቢ በሚገኙት አገሮች ሠፍሮ የነበረው
ጦር ኃይሉን አጠንክሮ ኢጣሊያንን ለመያዝ ወይም በደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጦብ ፈረንሳይ ውስጥ ለመስፈር ያለዚያም ወደግሪክ ለመ ዝመት ማዘጋጀት ዋና ዓላማው ነበር ። ይህም እቅድ ደግ ሞ በሥራ ሊገለጽ የሚቻል ነበር ። በእነዚህ የጦርነት መሥመሮች ላይ የሚሰጠውን ውሳኔና ሐሳብ ሁሉ መከ ታተል ማስረዳትና መጠበቅም የኛ ደርግ የሥራ ግዴ ታው ሆነ ፤ በዚህ መሠረተ ጥናት ላይ ተገቢውን የሥራ ድርሻ ለመፈጸም ምናልባት ሳይቻለን አይቀርም ነበር ። ዳሩ ግን ሌላ አስቸጋሪ ሁኔታ ደግሞ መጣብን ።

ሲስሊ በሜዲትራኒያ ባሕር ማእከላይ በታ የምትገኝና በኢጣሊያን መዳረሻ ላይ እንደ ኳስ ሜዳ የምትታይ ቀበ ሌ ናት ፤ እርሷ እስከ ተያዘች ድረስ በሜዲትራኒያ በኩል የጦር ኃይል ለማመላለስ ብንሞክር ያልታሰበ ጠቅላላ ውድቀት እንደሚደርስብን ግልጽ ሆኖ ቀረበ ። የቀበሌዋ አስጊነት በዚህ ብቻ ሳይወሰን በሰሜን አፍሪቃ በሚገኘ ውና በይዞታችን በነበረው የጦር አይሮፕላኖች ሠፈር ላይ እንኳ ጠቅላላ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ታመነበት ።

ስለዚህ ወደ የትኛውም የጦርነት መሥመር ምንም ዓይነት የጦር ኃይል ከማሠማራታችን በፊት የሲስሊን ጉዳይ አጥብቀን የምናስብበትና በተቻለው ሁሉ ዘዴ በቀ በሌዋ ተከማችቶ የነበረው የጠላት ኃይል የሚቀነስበ ትንና የሚደናገጥበትን ስልት ማከናወን አስፈላጊያችን ሆነ ። ጦርነት ከመጀመራችን በፊት ረዘም ላለ ጊዜ ለጦር ነቱ መዘጋጀት እንደሚገባን ሁሉ የሲስሊንም ጉዳይ ከጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ናታችንና እቅዳችን ጋር አዋሕደን ማንሰላሰል ግዴታችን መሆኑን ተረዳነው፤ ይህም ማለት ሲ.ስሊ.ን ለመያዝ የሚዘምተው የጦር ኃይላችን ፀጥታ እንዲጠበቅለት የጦርነቱ ችቦ የተባለው እቅድም ከመጨረሻው ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት የሲ.ስሊ.ን ጉዳይ ማቃለል የደርግልችን ግዴታ ሆነ ።

በዚህ ሐሳብና እቅድ በምንዋልልበት ጊዜ ደግሞ ሌላ ችግር እንደሚደርስብን ተረዳነው ።

ሰሜን አፍሪቃ በእጃችን ገብቃ ሲ.ስሊ.ንም ደግሞ ለመያዝ በቀጥርጥ መነሳሳታችን ግልጽ የሆነውን ያህል ለጀርመኖችም እንደዚሁ እንደሚሆን ተረዳነው፤ እርግጥ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህንኑ ጉዳይ አስቀድመው ተረድተውት ስለነበረ በዚህ ታሪክ ላይ የተፈጸመውን መሠረተ ሐሳብ ሲያጸድቁት "ሲ.ስሊ. ዋናዋ ግባችን መሆኗ እንዳይታወቅ ጥረት ብናደርግም ማነኛውም ቂላ-ቂል ቢሆን ሊደርስበት ይችላል" ብለው ነበር ።

ጊዜው ደርሶ የጀርመን መንግሥት በነገሩ ተጠራጥሮ ሲስሊ ውስጥ የነበረውን የጦር ኃይሉን ማጠናከር የጀመረ እንደሆን ይህን እርምጃውን ለመከላከልስ እንደምን እንችላለን? ዋናው ጥያቄ ይህ ሆነ ።

በዚህ ሁሉ ተውጠን በምንጨነቅበት ጊዜ አንድ ድንገተኛ ሐሳብ በር ቄረቄረ ። የጆርጅም አስገራሚው እቅድ ትክክለኛነቱን ለማስመስከር ጊዜ አጋጠመው፤ በዚህ ጊዜ

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔም ራሴን በራሴ ስለምን አንድ ሬሳ እንፈልግም? እርሱ ንም እንደ አንድ የጦር መኰንን ለምን አናለብሰውም? ከእ ርሱስ ጋር ብርቱ ምሥጢር ያዘሉ ደብዳቤዎች ለምን እን ዲገኙ አናደርግም? በዚያስ ደብዳቤ ላይ የጦር ኃይላችንን ወደ አንድ ሌላ በታ ለማዝመት ማቀዳችንን ለምን እንገ ልጽም? ያንም ሬሳ ከአየር ላይ መጣል ሳይሆን በፈረን ሳይ ወይም በእስፐይን የባሕር ዳርቻ እየተንሳፈፈ ከነወረ ቀቱ እንዲገኝ እናደርጋለን በየትኛውም በታ ቢገኝ ውጤ ቱ ያው ነው። እንዲያውም ምናልባት እስፐይን የተሻለች ትሆናለች ምክንያቱም ሬሳው በእስፐይን የባሕር ዳርቻ ሲንሳፈፍ ከጀርመኖች እጅ የገባ እንደሆን ለመመርመርና ለማጥናት ጊዜና ሁኔታው አይፈቅድላቸውም። ግን የም ሥጢር ሰነዱን ራሱን ወይም ግልባጩን ለማግኘት ይችላሉ ከሚል ሐሳብ ላይ አረፍኩ፤ በዚህ ነገር ላይ ነጥብ በነጥብ ተወያየንበት። ዝርዝሩንና ጥቃቅኑን ጉዳይ ሁሉ መራመርነው፤ ሬሳውን የጫነው አይሮፕላን ከባሕር ላይ ከወደቀ በኋላ ሬሳው ምን ዓይነት ሁናቴ ይኖረዋል? የአ ሟሟቱ ሁኔታስ በምን ዓይነት መሆን ይኖርበታል? አስቀ ድሞ የሞተ ሰው ጠቅላላ ጉዳይ እንደምን ያለ ሁኔታ ይታይበታል? ለዓላማችን ተስማሚ የሆነ ወይስ ማነኛው ንም ሬሳ ማግኘቱ ይበቃል? እንደዚህ የመሳሰሉ ጥያቄ ዎች ነበሩብን፤ መልሳቸውን ደግሞ ራሳችን ማቅረብ ነበ ረብን መልሶቹ አጥጋቢዎች ከሆኑ እቅዱ በጥንቃቄ ይጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

ናል፤ በዚያም እቅድ ላይ ማንኛችንም አልተጠራጠርንም ነበር፤ የአጋጣሚውን ዕድል በር እኛ ከከፈትንላቸው የእስፐይን ሰዎች ሊረዳን የሚችል ተግባር እንደሚፈጽሙ ተስፋ አደረግን፤ ከዚያም በኋላ ሌላ ዕድል ለራሳችን ማጐናፀፋችንን ተረዳነው ።

## ተቀዳሚዎቹ ጉዳዮች ።

“ሬሳ ለማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ ተነጋገርንበት” ቢሆንም አስቸጋሪነቱን አመንበት በመጀመሪያ ሬሳ የማግኘቱ ነገር አስቸጋሪ የሆነብን ወደ ዝርዝር ጥናቱ ስንገባ ደግሞ የሁኔታው ክብድነት ብዙ ጉዳዮች ሊያስተምረን ችሏል ። ሬሳ የማግኘቱና በሬሳ የማታለሉን ሐሳብ ማንኛችንም ቢሆን አልወደድነውም፤ ይከብዳል ይቀፋል ። በጦርነት መሥመር ላይም እንኳ ቢሆን ሬሳ ክቡር ነው ። ማንገላታት መናቅ ለአእምሮ እንደሚከብድ እናውቃለን፤ ቢሆንም በአንድ ሬሳ አማካይነት የብዙ መቶ ሰዎች ሕይወት አትርፎ በኋላ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ግባተ መሬቱን መፈጸም የጊዜ ምርጫ ሆኖ ቀርቦልናል ። በመጀመሪያ ከጋጠሙን ጉዳዮች ዋናው የፀጥታ ጉዳይ ነበር ።

ቤተ ዘመድ በኃዘን ተከራምቶ ወደሚገኝበት ቤት ሄዶ የሟቹን ልጅ ወይም ባልተቤት ያለዚያም ወንድም ጉዳዩ ሳይነገራቸው ሬሳ እንዲሰጡ ማድረግ እንዴት ይቻላል? እንዲያው ለነገሩስ ጉዳዩን መንገር ቢኖርብን ምን



t.me/OLDBOOKSPDF

ልንላቸው ነው? ለማታለል ያህል ከሆነ ለአቅዳችን የሚጠቅም ሰው የሞተበትን ቤተ ዘመድ ፈልገን ለማነጋገር ምናልባት ይቻል ይሆናል። ምናልባትም ያ ሰው ሬሳውን እንድንወስደው ያለ ጥያቄ ይስማማ ይሆናል። ይህ የሚሆነው ጉዳዩን እንዲያው በማስመሰል የያዝነው እንደሆነ ነው፤ ለእውነተኛው ጉዳይና ፍጻሜስ እንደምን ሊስተካከል ይቻላል?

የሆነ ሆኖ ወደፍለጋው ከመሠማራታችን በፊት በምን ይዞታ ላይ የሚገኝ ሬሳ እንደምንፈልግ መመካከርና ማረጋገጥ ነበረብን በባሕር ላይ ከአይሮፕላን እንደወደቀ መዋቲ አድርገው ሬሳውን ጀርመኖች የሚመለከቱልን ከሆነ በዚሁ አኳኋን የሞተ ሰው ሬሳ ማግኘት ነበረብን።

ለዚህ ጉዳይ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል መልስ ለማወቅ የሚቻለው ስለ መዋቲዎች የሚያውቅ ሰው ማነጋገሩን ነው።

አንድ አይሮፕላን በባሕር ላይ ወድቆ ከተሰባበረ በኋላ አንድ ሬሳ ሲንሣፈፍ ቢገኝ ምን ዓይነት የመዋቲነት ሁኔታ እንደሚገኝበት የበሽታዎችንና የመዋቲዎችን ነገር አጣርቶ የሚያውቀው ሐኪም ምን ይላል? በመሠረቱ ደግሞ አይሮፕላኑ በእርግጥ በአስቃቂ ሁኔታ መውደቅና መነኳኮትም አይኖርበትም።

ስለዚህ ሁሉ ሁኔታ ከሰር በርናርድ እስፖልስበረይ ጋር መወያየት አስፈለገ። ያም ሰው በሕክምና ረገድ እጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግ የተራቀቀ ባለሙያ ነበር፤ በፀጥታው ማለት በምሥጢ ርነቱም ረገድ ከእርሱ የተሻለ ሰው አልነበረም ።

ታማኝ ነው ለምለው ሰው ይህን ጉዳይ ባጫውተው በሆነው ሁሉ ነገር ለማንም ቢሆን እንደማይናገር ምሥ ጢርነቱን ጠብቆ እንደሚይዘው የታወቀ ነው ።

በዚህ መሠረት በሰር በርናርድና በአንድ ታማኝ ዝምተኛ ሰው መካከል ምንም ልዩነት አይኖርም ። እንዲ ያውም በጣም እምነት ከሚጣልባቸው አንዳንድ ሰዎች የሚደመር ሰው ነው ። ችግሩንም ሳካፍለው ስለጉዳዩ በልዩ ልዩ ጥያቄ እንደማያዋክበኝ ተማምኜበታለሁ ። እርሱም ወደ ዝርዝር ነገር ሳይገባ አይሮፕላን ከባሕር ላይ ወድቆ ሲንሣፈፍ የተገኘ ሬሳ ነው ብለው ጀርመኖች ወይ ም እስፓንሾች እንዲያምኑበት ለማድረግ መፈለጌን ብቻ ከነገርኩት ይኸው እንደሚበቃው እንጅ ሌላ ጥያቄ እንደ ማያስከትል ተማምኜበታለሁ ከዚሁ ሐኪም ሌላ ሰው ለጥያቄዬ መልስ እንደማይሰጠኝም ተረድቼዋለሁ ።

በዚሁ ነገር ሐሳቤን ደመደምኩና ወደ ሠር በርናርድ ስልክ ደውዬ ከርልቶን በሚባለው ክበቡ ለመገናኘት ተቃጠርን ። በዚያም ተገናኘንና ብርጭቆዎች ካቅጨለጨ ልን በኋላ ችግራችንን አነሣሁበት ።

በነገሩ ከምስለሰለበት በኋላ ብዙዎቹን መርማሪዎችና ዳኞች ለማሳመን የሚችል ሐሳብ ነገረኝ ። ተስፋ ያለው መ ልስ ሆነኝ፤ በማይ ዊስት በኩል ሲንሣፈፍ ሬሳ ነው ተብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎ እንዲታመንበት ለማድረግ በውሃ ውስጥ ገብተው ከሞቱ ሰዎቻችን ወይም በተፈጥሮ ሕመም የሞተ ሰው ለማግኘት እንችላለን። ከባሕር ላይ በአይሮፕላን ወድቀው የሚሞቱ ሰዎች ግን ብዙውን ጊዜ አንዳንዶቹ ከመጋጨት የተነሣ ይሞታሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ውሃ ውስጥ በመግባት ይሞታሉ። ብዙዎቹ ግን አይሮፕላኑ ከመበታተኑ የተነሣ ወይም በኃይለኛ ንቅናቄው ይሞታሉ። ስለዚህ ሬሳ የማግኘታችን ነገር ከአሰብነው በላይ ይሆናል ብዬ ፈራሁ።

ሐሳቤን ሰር በርናርድ አስተካከለልኝ በጉዳዩ ሳይገረምና በሐሳብ ሳይሸበር ነገሩን በጽሞና አዳምጦኝ መልሱን በትክክል አብራራልኝ። እርግጥ ነው በሕክምናው ረገድ መልሱን ለማቀነባበር እንዲችል አንዳንድ ነገሮች ጠይቆኛል። ግን ለምን ለማወቅ እንደፈለግሁ ወይም ሬሳውን ለምን አገልግሎት ለማዋል እንዳሰብኩ አልጠየቀኝም። ስለ ተባለም ያቀረበልኝ ጥያቄዎች ቀላል አልነበሩም። ሬሳ የማግኘቱን ነገር በግልጽ ልንጠያየቅበት አንችልም። ነገሩ እንዳይወጣብን የንግግር መንሾካሾኪያ እንዳይሆንብን በሆነው ሁሉ ነገር በተፈለገው ሁሉ ዋጋ መደባበቅ ያስፈልገናል! "አንድ ሰው ሬሳ ለማግኘት ያፈላልግ ነበር" የሚባል ጭምጭምታ እንዳይፈጠር መጠንቀቅ ነበረብን። ነገሩ በሰዎች ዘንድ የንግግር መጀመሪያ ለመሆን እንደሚችል አላጣነውም።

አንዳንድ የማውራት ልክፍት ያለበት ሰው ከሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋር በተገናኘ ቁጥር "አንድ የደረሰ አንግዳ ነገር ተፈጽ ሟል ለምተኸዋል? አገሴና አገሴ ሬሳ እንደምን ለማግኘት እንደሚችሉ ያፈላልጉ ነበር" እያለ ነገሩን ሊያዛምት ብን ይችላል ።

ይህን ነገር በመፍራት የሚገባውን ጥንቃቄ በማስቀ ደም ፍለጋችንን ቀጠልን፣ እርግጥ ነው በ፲፱፻፵፪ ዓ. ም. ብዙ መዋቲዎች ነበሩ፣ ግን ለኛ ተግባር የሚያገለግለን ሬሳ አላገኘንም ነበር ።

የባሕር ኃይል ባልደረባዎች የነበሩ ሰዎች ሬሳዎች ነበሩ፤ ግን ለሥራችን ተስማሚ አላገኘንም ። ለነገሩ ግን ስድስት መኰንኖች በፍለጋው ተሠማራን ። ሬሳ ለመቀማ ትም ከሚያስፈልገን ሁኔታ ላይ እንደርስ ይሆናል ብለን ሰግተን ነበር ። ግን ነገሩን ጠላነው፤ እንዲያውም በተቻለ መጠን ወደዚህ ዝንባሌ እንዳንደርስ መጠንቀቅ ፈለግን ።

የምንተማመናቸው የጦር መኰንኖች በሚገኙበት የሕ ክምና ክፍል ሁሉ ለማጠያየቅም አሰብን ። ግን የሚገኝ መሆኑን ስንሰማ ደግሞ የሟቹ ቤተ ሰቦች መስማማታ ቸውንና መቃወማቸውን እንደዚሁም ሬሳውን ለመውሰድ ፈቃድ የሚሰጡን ሰዎች ነገሩን ለሌላ ሰው እንዳያወጡ ብን ፈራን ። ከዚህ ሁሉ ሌላ ደግሞ የሟቹ ሰው የአሟ ሟቱ ሁኔታ ልዩነት ሊያስከትል የሚችል እንደሚሆን ተገነዘብን ።

በመጨረሻ ዘርፎ መውሰድ ወይም ጥያቄያችንን በሰ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊው በመቀጠል የሚነሳውንም ጥርጣሬና ወሬ ሁሉ በተ
ቻለ መጠን መከላከል አማራጭ የሆነውን ዘዴ ለመወሰን
በተቃረብንበት ጊዜ በሳንባ በሽታ የሞተ ሰው መኖሩን
ሰማን ። የሕክምና አዋቂዎች እንደሚያምኑበት የሟቹ
ሬሳ የጥያቄያችን መልስ እንደሚሆን ተረዳነው ። ከዚያም
አከታትለን የሰውየውን ያለፈ ታሪክና ቤተ ዘመዶቹን
መጠየቅ ጀመርን፤ ይህም የመጠየቃችን ዜና ደግሞ እንደ
ማይዛመት ተረዳነው፤ ቢሆንም ከአስቸጋሪ ጥያቄ አላመ
ለጥንም ። ይኸውም ለምን ተግባር እንደምናውለው ሳናስ
ረዳና ሐሳባችንን ሳንገልጽ ሬሳውን ለመውሰድ እንችላ
ለን? የሚል ነበረ ። ለሚቀርብልን ጥያቄ ለመመለስ የም
ንችለው ያለጥርጥር በእርግጥ ሬሳው ጠቃሚያችን መሆ
ኑ፡ ብቻ ነበር፤ ሊማነኛውም ነገር ቢሆን ደግሞ ጉዳዩ
መጸደቅ የነበረበት በከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነበር፤ ሬሳ
ውም ስሙ ተለውጦ ለተፈለገው ተግባር ከዋለ በኋላ ተገ
ቢው የቀብር ሥነ ሥርዓት እንደሚፈጸምለት ማረጋገጫ
ለቤተ ሰበቹ መስጠት ተገቢ ነበር ።

ሬሳው የማን እንደሆነ እስከ መጨረሻው ድረስ ለማንም
ላልናገር ቃል ገብሁና ከታላቅ ምስጋና ጋር ፈቃድ አገ
ኘን፤ የተሰጠንም ሬሳ የ፴ ዓመት ጐልማሳ መዋቲ ነበር ።
ሰውየው በሕይወተ ሥጋ በነበረበትም ሰዓት በጤንነቱ
ረገድ የተጐዳ ስለነበረ እንደክፍል ባልደረባ መኰንን
እንጅ ራሱን እንደቻለ አዛዥ መኰንን ስለማይመስል ይጠ
ቅመናል ብዬ የሬሳውን ተገቢነት አረጋገጥኩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለጥንቃቄም ያህል ከሠር በርናርድ ጋር ስለጉዳዩ ተነ ጋገርኩበት በሬሳው መገኘትና በሁኔታው ራሱም ደስተኛ ነበር ። በውስጥ ሕመም በመሞቱ ለእቅዳችን የተመቸ ሆነ። ሬሳው ቢመረመርም እንኳ በሳንባው ውስጥ ፈሳሽ ነጠብ ጣብ ይገኝበታል ። ይህም ሊያመለክት የሚችለው በውሃ ውስጥ ገብቶ እንደሞተ ሰው ነው ፣ እርግጥ ነው ከሬሳው የሆድ ዕቃ ውስጥ የሚገኘውን ነጠብጣብ ቀድቶ፣ በጥን ቃቄ ለሚመረምረው ከውሃ ጋር ልዩነት ሊያገኝበት ይች ላል ።

ሰር በርናርድም ማንኛውንም ጉዳይ ከመረመረው በኋላ ሙሉ ለሙሉ እምነት የሚጣልበት ምስክርነቱን "የእስፓይን ሐኪሞች ሬሳውን ይመረምራሉ ብላችሁ መስጋት የለባችሁም ። አይሮፕላን ከባሕር ላይ ከወደቀ በኋላ ይህ ሰው የሞተበትን ምክንያት ለመመርመር እስ ፈላጊ ሆኖ እንደማይገኝ አምናለሁ ። ቢያስፈልግም እንኳ የዚህ ባለሙያ እስፓይን ውስጥ የለም" ሲል አረጋገ ጠልን ። ከዚህ በኋላ እኛ ዝግጅታችንን እስክንፈጽም ድረስ ሬሳው በቀዝቃዛ ቦታ እንዲቀመጥ አደረግን ።

## የማስመሰሉ ዘመቻ ።

የጦርነቱን የእንቅስቃሴ ትእዛዝ ጀኔራሉ እንዲያጸድ ቅልን አስፈለገ፣ በመጀመሪያ ነገር እንደተለመደው ዘመ ቻው ከመጀመሩ በፊት የምሥጢር ስም ማግኘት ተገቢ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ለታላላቅ የዘመቻ መሥመር ሲሆን ግን የምሥጢር መጠሪያውን ስም መርጠው የሚሰይሙት ራሳቸው ጠቅ ላይ ሚኒስትሩ ነበሩ ። ይህም የሚሆነው ከጦር ኃይሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች ራሳችን ዝርዝሩን ሠርተን ካቀረብን በኋላ ነበር ።

ስለዚህ ራሴ ወደ አድሚራሊቴው ሠፈር ሄድኩና የምሥጢር መጠሪያ ስም ጠያይቄ "የማስመሰያው ዘመቻ" የሚል የጥቅል ስም አወጣሁ ፤ (ሰየምኩ) ።

ቀጥለን ደግሞ ሬሳውን የምንሰድብትን አቅጣጫ ለመ ምረጥ ውይይት ጀመርን ፤ ለማድረስ ማለት ሬሳው እንዲ ደርስ ማድረግ ከተቻለ ሂውልባ የተባለችው የባሕር ጠ ረፍ የተሻለች እንደምትሆን መረጥኩ ።

ይህችንም ቦታ የመረጥኩበት ዋናው ምክንያት በቀ በሌዋ የሚቀመጥ እጅግ ቀልጣፋና ንቁ የሆነ የጀርመን ሰላይ መኖሩንና ከእስፐይን ተወላጆችም ጋር በጣም የተ ቀራረበ ግንኙነት ያለው መሆኑን ስለምናውቅ ነበር ። የሰ ላዩም መቀራረብና ወዳጅነት ከተራው ሰው እስከ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ድረስ መሆኑን እናውቃለን ።

ሬሳው ከተባለችው ቀበሌ ከደረሰልን በሆነው ሁሉ ዘዴም ቢሆን ከሬሳው ጋር የሚገኘውን ወረቀት የጀር መኑ ሰላይ ሊያገኘው እንደሚችል ግልጽ ነበር ።

እንዲያው ለነገሩ ያህል እንኳ ሁኔታው ጠንከር ብሎ በት አስቸጋሪም ቢሆንበት ቅሉ ከሬሳው ጋር ከተገኘው



t.me/OLDBOOKSPDF

መረቀት ከፒውን ወይም ዝርዝር ዜናውን ሳያገኝ እንደ ማይቀር ያለ ጥርጥር አምነንበታል ። ራሱ ለማግኘት የማይ ቻለው እንኳ ቢሆን ማድሪድ ውስጥ ለነበሩት አለቆቼ አመልክቶ እነርሱም ከከፍተኞቹ ባለሥልጣኖች ጋር ተነ ጋግረውበት ጉዳዩን እንደሚያገኙት ተማምነንበታል ።

በዚህም ጊዜ እኛ የምናደርገው ጥረት በተቻለ መ ጠን ሬሳው በአስቸኳይ ከነመረቀቱ ማድሪድ ለነበረው ለእ ንግሊዝ ም/ቆንሲል ተሰጥቶ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት እንዲ ፈጸም እንጂ፤ ማንም ቢሆን ጣልቃ እንዳይገባ መከላከል ይሆናል ። ግን በጀርመንና በእስፔይን መካከል የነበረው ወዳጅነትና መቀራረብ የጠበቀ ስለ ነበረ የኛ ጥያቄ በቶሎ እንደማይፈጸም ተረድተነዋል ።

እንዲያው ለትዝብቱ ያህል ሲል እንኳ የኛን ጥያቄ ለመፈጸም የሚጣጣር የእስፔይን ተወላጅም ቢገኝ በሆ ነው ሁሉ ዘዴ ምክንያት ተፈጥሮ የጀርመኖች ጣልቃ ገብ ነት እንደሚኖርበት አልተጠራጠርኩም ነበር ።

ይህችው ሂውልባ የተባለችውም ቀበሌ ሌላው ጠቃ ሚነቷ ለጅብራላታር ቅርብ ያለመሆኗ ነበር ። ምክንያቱም የእስፔይን ባለሥልጣኖች ሬሳው እንዲቀበር ወደ ጅብራ ላታር እንዲልኩት አንፈልግምና ነበር ። ሬሳው ወደ ጀብ ራላታር ቢላክና እዚያውም ቢደርስ ኑሮ ግን፤ የመኰንን ነቱም ማዕረግ ስለሚገለጽ የሰውየው በጦር ኃይሉ ውስጥ ፈጽሞ ያለመኖሩ ይታወቅና፤ በየቀኑ የሚመላለሱትም



t.me/OLDBOOKSPDF

የጀርመን ሰላዮች በነገሩ ይደርሱበትና ያልታሰበ ራስ ምታት ይከተለን ስለ ነበረ ነው ።

ስለዚህ ወደ ባሕር ኃይላችን የንድፍና የአየር መቁጣጠሪያ ክፍል ሄድኩና በየዓመቱ በእስፐይን የባሕር ጠረፍ የሚደርሰውን የአየር መለዋወጥ ሥርዓት ጠየቅሁ ። በዚህም ጊዜ ዕድላችንን ሌላ ዕንቅፋት እንደ ተደቀነበት ተረዳሁ ፤ የአየሩ ሁናቴ የሚረዳን አልነበረም ፤ ከደቡብ ምዕራብ የሚነሳው የሚያዝያ ወር ነፋስ ባሕሩን ወደ ውጭ የሚገፋ አልነበረም ። ቢሆንም የአየር ሁኔታ መቁጣጠሪያው ክፍላችን እንዳመነበት ፤ አንድ መጠነኛ ክብደት ያለውን ነገር ወደ ባሕሩ ዳር አየሩ ገፍቶ ለማውጣት እንደሚችል አረጋገጠልኝ ። ስለዚህ በማይዊስት በኩል የሚጣለውን ሬሳ ፤ አየሩ በተገቢው አኳኋን እየገፋ እንደሚያወጣው ተረዳሁት ።

ይህን የመሳሰለው ዝርዝር ጉዳይ ከተጠና በኋላ ፤ ሂዊልባ የተባለችው የባሕር ዳር ቀበሌ ተስማሚነቷ ተመረጠ ። ያለጥርጥር ሬሳው በነፋስ እየተገፋ ወደ ባሕሩ ዳርቻ እንደሚደርስ ተማመንበት ። ከዚያ በኋላ የተለመደው ውጣ ፤ ውረድ ፤ ይጀመራል ። ሬሳውንም እንዲቀብር ለእንግሊዝ ም/ቆንሲል ይሰጠዋል ። ከዚያም እንደ ተማመንኩበት ሁሉ ከሬሳው ጋር የተገኘው ወረቀት ግልባጭ ወይም ዝርዝር ታሪኩ ከጀርመናዊው ሰላይ እጅ ይደርስና ወደ በርሊን ይተላለፋል ፤ እምነታችንና ጥናታችንም በከንቱ አይቀርም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የማስመሰሉን ዘመቻ ለመፈጸም ትክክለኛ የመዳረሻ ውን ቦታ ለመምረጥ በምንወያይበት ጊዜ፤ የመጓጓዣው ነገር ደግሞ ተደቀነብን። ከአየር ላይ የተጣለ እንደሆነ ሊቆሳስል ይችላል ብለን ፈራን፤ ቢሆንም ፫ አማራጭ ዘዴዎች ነበሩን። እነዚህም በጠላቂ መርከብ ወይም በፈጣን ባለሞተር ጀልባ ወስዶ ማድረስ፤ ያለዚያም እስከ እስፔይን የባሕር ጠረፍ ድረስ የሚሄዱትን መርከቦች ከሚያጅቡት መርከቦች አንዱ አቅጣጫውን ለውጦ ወስዶ እንዲያደርሰው ነበር።

ከነዚህ አማራጭ ዘዴዎች ሁሉ የባሕር ውስጥ ለውስጥ ጠላቂ መርከብ ያለ ስጋት ሬሳውን ከተባለው ቦታ እስከ ባሕሩ ዳርቻ አድርሶ ለመመለስ እንደምትችልና የተሻለውም ዘዴ ይኸው እንደሚሆን ተማመንበት።

ስለዚህ ጠላቂ መርከብ እንዲፈቀድልን ከባሕር ኃይላችን ም/ኃላፊ ተነጋገርኩና ከአድሚራል ባረይ ጋር ስለ ሁኔታው እንዲወያዩበት ጠየቅሁ።

በጉዳዩ የባሕር ኃይላችን ከፍተኛ ኃላፊዎች ከተወያዩበት በኋላ ለባሕር ኃይሉ ችፍ አፍ እስታፍ እንዲቀርብ ወሰኑ።

ሐሳቡ በሥራ ላይ ሊገለጽ እንደሚችል አድሚራል ባረይ ተረዱት። ስለ ጉዳዩም ከአድሚራሉ ረዳት ዋና አዛዥ ጋር ተነጋገርንበት። ዘማቹን ሬሳ ወደ ሞልታ የምታልፍ የባሕር ውስጥ ለውስጥ የጦር መርከብ ይዛው እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ደምትሄድ የባሕር ኃይሉ አዛዥ አረጋገጠልን ። ሌላው ጥያቄያችን ደግሞ ፤ ሬሳው በልዩ ሣጥን ቢጓዝ ወይስ እንደዚሁ በግልጽ ሆኖ ከመርከቧ ውስጥ በልዩ ክፍል ሆኖ ቢጓዝ ይሻላል ? የሚል ነበር ። ይህንም ጉዳይ ሬሳው በመርከቧ ውስጥ በልዩ ክፍል ሆኖ በሣጥን ሳይታሸግ ሊጓዝ መቻሉን የባሕር ኃይሉ አዛዥ አረጋገጠልን ፤ በዚህ በኩል የነበረው ችግራችን ተቃለለ ።

ሌላውን ችግራችንን ደግሞ ፤ ከቀዝቃዛ ክፍል የነበረውን ሬሳ አውጥተን በባሕር ውስጥ ለውስጥ እንዲጓዝ ከማድረጋችን በፊት በተለየ ዕቃ ውስጥ መቈየት ይኖርበት እንደሆነ በማለት ፤ ከሰር በርናርድ ጋር ተወያየንበት ። ከቀዝቃዛ ክፍል ወጥቶ በባሕር ውስጥ ለውስጥ ቢጓዝም አየር እንዲያገኝ ማድረግ እንጅ ፤ ሌላ ጉዳይ እንደ ማያስፈልገው ተረዳሁ ። ይህም ስለ ተባለ ሬሳው የሚጓዝበትን ሣጥን ባንድ በኩል በረዶ እንዲቀመጥበትና ፤ በረዶው ቀስ በቀስ እየቀለጠ የሬሳውን ጠረን እንደ ነበረ እንዲያቈየው እንደሚያስፈልግም ተነገረን ። ወዲያውም ሬሳው በነበረበት ሣጥን ዙሪያ በረዶ እንዲከማች አደረግን ። ያም ሁሉ ጥረትና ጥንቃቄ ያስፈለገው ፤ ሬሳው ወደ ባሕር ዳርቻ ተጥሎ ሲንሳፈፍ ከተገኘ በኋላ ጥቂት ራቅ ብሎ በባሕር ላይ ከወደቀ አይሮፕላን ወጥቶ ሲንሳፈፍ እንደ ሰነበተ ሆኖ በጀርመኖች ዘንድ እንዲገመትልንና እንዲታወቅልን በማለት ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማንኛውንም ጥንቃቄና ዝግጅት ከከናወን በኋላ በሚያዝያ ወር መጨረሻ ላይ የማስመሰሉን ዘመቻ ለመጀመር ዝግጁ መሆናችንን ለአድሚራል ባረይ ነገርኩ። ይህም ሐሳቤና ዝግጅታችን ደግሞ በባሕር ኀይሉ ባለሥልጣናት ዘንድ የተደገፈ ሆነ። ምክንያቱም ወራቱ የጨረቃ ብርሃን የሌለበት ስለ ነበር ጠላቂዋ መርከብ እስከ ባሕሩ ዳርድረስ ያለ ስጋት ሂዳ ተልእኮዋን መፈጸም ስለምትችል ነበር። የግርማዊነታቸው የእንግሊዝ ንጉሥ ነገሥት የባሕር ውስጥ ለውስጥ ጠላቂ መርከብ "ሠራፍ" የተባለችው በሃገር ውስጥ ባሕር እንድትለማመድ ተብሎ ወደ ሞልታ ብሰሜድ ለዐሥራ አምስት ቀን ዘግይታ ስለ ነበረ፤ ሬሳውን ወደ ተባለው ሥፍራ ለማድረስም እንደምትችል አድሚራሉ ተስማማ።

ለዚያ ተልእኮ "ሠራፍ" መመረጧ እንደ ታላቅ ዕድል የሚገመት ነበር። ምክንያቱም የመርከቢቱ አዛዥ የመቶ አለቃ ጀዊልና የሥራ ባልደረቦቹ በሰሜን አፍሪቃ ውስጥ ጦር ለማሥፈር በተደረገው ዘመቻ የሚመሰገን ተግባር ያከናወኑና ዘዴውንም ያጠኑት ስለ ነበሩ ነው። እነዚሁ መርከበኞች ወደ ባሕር ዳርቻ ተጠግተው፤ ጀኔራል ጊራውድ ከእስር ቤት አምልጦ ሲወጣ ይዘውት በባሕር ውስጥ ለውስጥ ያመለጡና ጀኔራል ማርክ ክላርክንም ወደ ሰሜን አፍሪቃ የባሕር ዳርቻ ተጠግተው አድርሰውት ከፈረንሳዮች ጋር በምሥጢር ተገናኝቶ ከተነጋገረ በኋላም



t.me/OLDBOOKSPDF

መልሰው እንደዚሁ በባሕር ውስጥ ለውስጥ ይዘውት የተመለሱ የታወቁ ባለሙያዎች ስለ ነበሩ ነው ።

የዘመቻውን ትእዛዝ በጥንቃቄ ተከታተልኩ ፤ ለመርከቢቱ አዛዥ የተሰጠውንም ትእዛዝ አድሚራሉ አረጋገጠው ፤ የጠላቂዋ መርከብ ዋና አዛዥም ስለ ጠቅላላ ጉዳዩ ከኔ ጋር በሰፊው ከተወያየንበት በኋላ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጠሁት ።

## የ ማ ስ መ ሰ ሉ  ዘ መ ቻ ።

### ፩ - ዓላማው ፤

ከታላቋ ብሪታኒያ መንግሥት በሰሜን አፍሪቃ ለነበረው የተባበሩት መንግሥታት ጦር ጠ/ጽሕፈት ቤት የተጻፈ ደብዳቤ አንድ መኰንን ይዞ በአይሮፕላን ሲበር በባሕሩ ላይ አይሮፕላኑ ወድቆ የመኰንኑም ሬሳ እየተንሣፈፈ ወደ እስፓይን የባሕር ዳርቻ ሄዊልባ የደረሰ ለማስመሰል እንዲቻል በሆነው ሁሉ ዘዴና ቈራጥነት ፤ አንድ የሙሉ መኰንንነት ልብስ የለበሰ ሬሳ እስኪ ባሕሩ ጠረፍ ማድረስ ነው ።

### ፪ - ዘ ዴ ው ፤

የሮያል ባሕር ኃይል የሻለቅነት ማዕረግ የለበሰ ሬሳ በጠላቂዋ መርከብ ወስዶ የምሥጢር ወረቀቱን ከያዘበት በልዩ አኳኋን በተሠራው በርሳው ጋር ወደ ባሕሩ ዳርቻ ይጣላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬሳው መጐሳቈልና መፈራረስ እንዳይደርስበትም በ ልዩ ልዩ መከላከያዎች ይወሰዳል።

፫ - አቅጣጫው ፤

ሬሳው በተቻለ መጠን ሄዊልባ በተባለችው የባሕር ዳር ቻ አቅራቢያ ተጠግቶ ይጣላል፤ በነፋስ እየተገፋ ወደ ውጭ እንዲወጣም በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በኩል ይሆናል።

ከአየር መቈጣጠሪያ ክፍል በተገኘው መረጃ መሠረት የቀበሌው ማዕበላዊ ጠባይ ተለዋዋጭ ስለሆነ፤ በተቻለ መጠን ሬሳውን ወደ ባሕሩ ዳርቻ ነፋሱ ገፍቶ የሚያወጣ በትን አቅጣጫና ጊዜ መምረጥ ያስፈልጋል። ለዚህ ተግ ባርም ከደቡብ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የሚሠራጨው የነ ፋስ መጠንና ብርታት ይረዳ ይሆናል።

በቅርብ ጊዜ የተገኘው የቀበሌው አየር ሁኔታ ማመ ልከቻም ከዚህ ትእዛዝ ጋር ተያይዟል።

፬ - የመረከቢያው ጊዜ ፤

ሬሳውን የያዘው ሣጥን በተፈለገው ቀን ወደ ወደቡ በመኪና ይወሰዳል፤ ይህም የሚሆነው መርከቧ ጉዞዋን ልትጀምር በተዘጋጀችበት ቀን ቢሆን የተሻለና የሚመ ረጥ ይሆናል፤ የማስመሰያውን የምሥጢር ወረቀት የያ ዘው ቦርሳ ለመርከቧ አዛዥ ይሰጣል።

፭ - የሬሳው ይዘታ ፤

ሬሳው ከጠላቂዋ መርከብ ወጥቶ ከባሕር ላይ ከመ ጣሉ በፊት የምሥጢር ወረቀቱን የያዘው ቦርሳ በከፍተኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥንቃቄ በሰንሰለት ከቀበቶው ጋር ይታሠራል ። ቀጥሎም ከዶረቱና ከጫንቃው ጋር ይጠመጠማል ።

ይኸውም መኰንኑ አይሮፕላኑን ሲያበር በነበረበት ጊዜ በርሳውን እንዲአነገተውና በጥንቃቄም እንዲይዝ እንደተደረገ ለማስመሰል ነው ።

ማነኛውም ነገር ነጥብ በነጥብ በጥንቃቄ ከተፈጸመ በኋላ ሬሳው ከባሕሩ ላይ ይጣላል ። መንሳፈፊያውም ላስቲክ ከዊ መሣሪያ ተያይዞ ይጣላል ። ይኸውም ከሬሳው በተለያየ የጕዞ ፍጥነት እንዲቀራረብ ሆኖ ነው ። ትክክለኛ አቅጣጫውን ከያዘም መንሳፈፊያው ላስቲክ ከሬሳው እንዲላቀቅ ማድረግም አስፈላጊ አይሆንም ። ቢሆንም ከተቻለ ሬሳውና መንሳፈፊያው እንዲያያዙና እንዲቀራረቡም አያስፈልግም ።

፭ - በጅብራላታር የሚገኙትን ማስጠንቀቅ ፤

ጉዳዩን በጅብራላታር የሚገኙት የባሕር ኃይል ልዩ ልዩ ክፍሎች እንዲያውቁትና እንዲጠነቀቁበት አስፈላጊው ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል ።

፮ - ምልክቶች ፤

ይህ ዓላማ በትክክል የተፈጸመ እንደሆነ ፤ የሚላከው ምልክት "ሽፍንፍኑ ተከናውኗል" ተብሎ ነው ምልክቱ የሚላከው ከጅብራላታር የሆነ እንደሆነ ለባሕር ኃይሉ የመረጃ ሹም የግል ተብሎ ይተላለፋል ። ከተወሰነው ጊዜ ቀደም ያለም እንደሆነ ከአድሚራል ባረይ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይፈጸማል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ፰ - ሽረት ፤

ይህ ተግባር እንዲቀር እንዲሻር ያስፈለገም እንደሆነ የሚተላለፈው ምልክት "ቅልቅሉ ወይም ሽፍንፍኑ ቀርቷል" ተብሎ ነው ። በዚህም ጊዜ ሬሳው በማጥን ሆኖ ጥልቀት ባለው በኩል በባሕሩ ውስጥ እንዲሰጥም ይደረጋል ። ያልታሰበ ስሕተት ተፈጽሞ ሬሳው ሲንሳፈፍ እንዳ ይገኝ ማድረግ ያስፈልጋል ፤ ደብዳቤውን የያዘው ቦርሳ ግን ጅብራላታር ለሚገኘው ለባሕር ኃይሉ የመረጃ ኃላፊ ይሰጣል ። እርሱም ቦርሳውን ከነ ወረቀቱ እንዲያቃጥል ይነገረዋል ። የመንሳፈፊያው ላስቲክም አብሮ ይሰጠዋል ።

## ፱ - መቋረጥ ፤

ይህ ጉዞና ተግባር እንዲቆም የተወሰነም እንደሆነ የሚተላለፈው ትእዛዝ "ሽፍንፍኑ ቀርቷል" ተብሎ ነው ። በተራ ቁጥር ፯ የተሰጠውን ማብራሪያ አስታውስ ።

## ፲ - መሸፈኛ ፤

ለጥንቃቄ ያህል ፤ ዋናው ሥራ እስከ ተጀመረ ድረስ ሬሳውን የያዘው ሣጥን በሚገባ ተሸፍኖ ይቄያል ። እንዲሁም ይህ የመሸፋፈኛ ዘዴ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቅበቱ ውጤት እጅግ የተቀላጠፈው ጀርመናዊው ሰላይ ይህን የማስመሰያ ዘዴ ተከታትሎ ይደርስበትና ለሚያደርገውም የስለላ ተግባሩ እንደ በቂ ማስረጃ ሆኖ እንዲያገለግለው ከእስፐይን ወዳጆቹ ዘንድ የሚገፋፋው ነገር ያገኛል ብለን ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህንም ሰው ለማጥመድ የሚቻለው ዕድል ሁሉ ያረፈው በኛ መርከብ ሠራተኞች ላይ ነው። የኛ ኀይልና ችሎታ ከእስፐይን ተወላጆች ጋር ተጣምሮ ካሰብነው ሊያደርሰን የሚችለው በነገሩ ላይ ብርቱ ጥንቃቄና ምሥጢራዊ ጥበቃ ያደረግን እንደሆነ ነው ። የኛ እቅድ የተጠበቀና የተቃናም እንደሆነ፤ እነርሱ ሊተባበሩበትና የበኩላቸውንም በግል ሊፈጽሙበት ይመቻቸዋል ።

እንግዲህ በዚህ ዘመቻ ላይ ጀርመኖችና እስፐይናውያን በተራ ቍጥር እንደ የተገለጸውን ምሥጢራዊ ጽሑፍ እንዲቀበሉትና እንዲተማመኑበት ማድረግ ዋናው ጥረታችንና ዓላማችን ነው ፡ ግን በእቅዳችን ላይ ጥርጣሬ ያደረባቸው እንደሆነ ተከታትሎ የሚነሣብን ውጥንቅጥ በቀላሉ ሊቃለል የማይችል ይሆናል ።

ፊርማ፤

ኢ. ኢ. ኤስ. ሞንታጉ

ሌ/ኮማንደር ፴፩ - ፫ - ፵፫ ።

ከዚህ ትእዛዝ በኋላ ደግሞ እንደገና ስለ ጉዳዩ ነጥብ በነጥብ ተመካከርንበት ከዚህ ሁሉ ሌላ ደግሞ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ አጋጠመን ።

ጀርመኖች የነበሩበትን የጦር ሠፈር እንዲለቁና የጦርነት ስልታቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ ምን ዓይነት ሊተማመኑበት የሚያስችላቸው የምሥጢር ጽሑፍ ማቅረብ ያስፈልገናል? የምናቀርበውስ የምሥጢር ጽሑፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሥር ከመሠረቱ እምነት የሚጣልበት በትክክለኛነቱ ጀር መኖች አምነውበት የሚቀበሉት ለማድረግስ እንደምን አድርገን አስመሳይነታችንን ማሳመርና ማቀነባበር እን ችላለን ?

— ይህን ሐሳብ በምናውጠነጥንበት ጊዜ በ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. "ሚከዶ" በሚል አርእስት ጅልበርት በጻፈው ትያ ትር ውስጥ በ-ብ የተባለው ተዋናይ "የተቀነባበረና የተረ ጋገጠ ዝርዝር ጉዳይ በከፍተኛ ጥንቃቄና ማስመሰል ተዋ ህዶ እውነት ሆኖ ካልቀረበ በቀር ታሪኩን አጋልጦ በዶ ነቱ ሊያመለክት እንደሚችል ማወቅ ያሻል" ሲል የተና ገረው ትዝ አለኝ ።

## አስፈላጊው ሰነድ ።

አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ወለል ብሎ ይታየኝ ጀመር ። ጀርመኖችን ለማታለልና እንዲያምኑንም ለማድረግ የምና ዘጋጀው የማስመሰያ ሐሳብና የምናቀባብላቸው ሰነድ በከ ፍተኛ ደረጃ ባሉ ባለሥልጣኖች መቀነባበር ይኖርበታል እንጂ ፤ በተራ ሥራ ላይ በተሠማሩ ባለሥልጣኖች መከ ናወን አይገባውም ፤ እምነትና ተቀባይነት አይኖረውም ። ሌላው ቀርቶ ከአንድ ብ/ጀኔራል ወይም ከአየር ኃይል ኃላፊ ያለዚያም ከባሕር ኃይሉ ክፍል ከአንድ አድሚ ራል ቢተላለፍ ጉዳዩን ሊያከብደውና እምነት ሊጣልበት እንደ ማያስችል ተረዳሁት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሲሲሊ ሌላ የጦር መሥመር እንደሚኖረን በመጠራጠር እውነቱን ለማረጋገጥ የጀርመን የጦር ባለሥልጣኖች የሚከታተሉን መሆኑን ከመንበት በማስመሰል አቅድ የምናስተላልፈው ሰነድ መዘጋጀት የሚገባው እውነተኛውን የጦር አቅዳችንን አጣርተው በሚያውቁና በከፍተኛ ሥልጣን ላይ በሚገኙ የጦር መኰንኖቻችን መቀነባበር ይኖርበታል። እነዚህም ከፍተኛ የጦር ባለሥልጣኖቻችን የሚቃመኑና በማስመሰያው አቅዳችን ራሳቸው የማይታለሉ መሆን ይገባቸዋል፤ ይኸው የማስመሰያው ዘመቻችን ውጤት የሚሰጥ መሆኑን እምንንበት የምናቀነባብረው ከሆነ ከማታለያው ሰነድ ላይ ከፍተኛ የጦር አዛዥ እንዲፈርምበት አስፈለገ። ያም የጦር አዛዡ ጀርመኖች የሚያውቁትና ከታመነ ምንጭ ያገኘነው ብለው የሚተማመኑበት እንዲሆን ያሻል።

ስለዚህ ሐሳቡን የመንግሥቱ የጦር ኃይል ም/ቁና አዛዥ ለነበሩት ለጀኔራል ሰር አርችባልድ ንይ ጽንሰቁ ብላቸውና ወረቀቱን እርሳቸው ጽፈው እንዲፈርሙበት ወሰንኩ። የሚጽፉትም ደብዳቤ በጀኔራል አይዘንሀወር ሥር ሆነው በቱኒዚያ የነበረውን የጦር ኃይል ሲመሩ ለነበሩት ለጀኔራል አሌክሳንደር ሆኖ ወደ ፷ኛው ምድብ ጦር ጠ/ጽሕፈት ቤት የሚላክ እንዲመስል ሆነ።

የደብዳቤው መንፈስና አጻጻፍም እኛ ምክትል ከፍተኛ መኰንኖች እንደምናስበው "የድሮ ሰዎች ባሕሪይ"



t.me/OLDBOOKSPDF

እያልን እንደምንቀልድበቱ ዓይነት እንዲመስል ሆነ። እንደዚያ በምንቀላለድበቱ ጽሑፍ ውስጥ አልፎ አልፎ "አዳምጠኝ ጓዴ! እየው ተመልከተው! ችግሩን ተረድ ተንልሃል፤ እኛ ደግሞ ብዙ አደናቃፊ ጉዳዮች አሉን፤ የጠና ጠ/ጽሕፈት ቤት አንዳንዶቹን ጥያቄዎችህን ሠርዟ ቸዋል። ቢሆንም መወትወትህን አትተው፤ የጠየቅኸውን ነገር ሁሉ በቶሎ ለማግኘት የማትችልበትም እውነተኛ ምክንያቶች አሉ። ሰንቅፋቶቹም እንደዚህ የመሳሰሉት ናቸው"፣ በዚህ ዓይነት የተጻፉት የወዳጅነት ደብዳቤዎ ችም እውነተኛ ምሥጢርነት የማይታይባቸውና እንደ መንግሥታዊ ሰነድም ሊቈጠሩ የማይችሉ ነበሩ። ቢሆ ንም ሲስሊን ለመውረር የማንችል መሆናችንን ጀርመ ኖች ሊረዱት ይችሉ ነበር፤ ሊገኙ የሚገባቸውም በተለ መደው መንግሥታዊ ጽሑፍ በሚመላለስበት እና ከሃገራ ችን ውጭ ወደሚገኝ ጦር ቦርሣ ሳይሆን በአንድ መኰንን ኪስ መሆን ይኖርበታል።

ዓላማዬን በከፍተኛ ቦታ ላይ አነጣጠርኩ። ደረስኩ በትም፣ አንድ ነገር እንዲፈነዳ ፈልጌ ነበርና ተሳካልኝ፤ ይህን ለመሳሰለው ሥራ እጅግ የታወቁ ባለሙያዎች እንኳ ቢሆኑም ሞክረውት ቢከሽፍባቸው ያስመሰግናቸዋል እን ጂ አያሳፍራቸውም። በተለያዩ አቅጣጫዎች እቅድ አው ጥቶ በተራቀቀ ችሎታ አሳክቶ ለመገኘት ተደራራቢ የሆ ኑ መሰናክሎች ከብዙ አኳያዎች ይፈልቃሉ። የእንግሊዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

የመረጃ ሥራ ኃላፊ ስሆን የጦር መኰንን ተቃራኒው የጠ
ላት የመረጃ ኃላፊ መኰንን ይሰለፍበታል ። በለፈው ጦር
ነት እንደ ተፈጸመው ሁሉ በርሊን ላይ ሆኖ በለንደን
ላይ የሚያነጻጽር የመረጃ ድርጅት ተቋቁሟል ። ከዚያ
ሌላ ደግሞ የጀርመን ጦር የበላይ አዛዥ አስገምግሞበታል።

እንግዲህ ከዚህ ኃይል ጋር ተቋቁሞ ብሪታኒያን ከጥ
ፋት ለማትረፍ የሚችለው የመረጃ መኰንን እንደምን
ያለ ሰው ምን ችሎታና የቱን ያህል ታማኝነት ያለው መ
ሆን አለበት ? በማስመሰል በሚያቀርበው የምሥጢር ሰነ
ድስ ምን የሚያሳምን ቃልና ሐሳብ ማቅረብ ያስፈልገዋል ?
በሚቀርብለት የማስመሰያ ሰነድ ላይ በችሎታው ራሱን
የተማመነው ጀርመናዊ የመረጃ ሠራተኛ ምን አስተያየት
ያሰርፍበታል ? ስለዚህ ይህን ሁሉ በዝርዝር አጥንቶ አው
ጥቶና አውርዶ የሚያዋጣውን አመዛዝኖ በተዘረጋበት
ወጥመድ ላይ እንዲገባ ከተፈለገ አእምሮው በሐሳብ የሚ
ጨነቅበት በአሠራሩ ግራ የሚጋባበት አንድ እንቆቅልሽ
ማቅረብ ያስፈልጋል ።

ምናልባት ተጠራጣሪ ሊሆን ይችልና ሊያምንበት
የሚያስችለው ማስረጃ ማግኘት ይፈልጋል ፤ የሚሰነዝራ
ቸው ጥያቄዎችም በምን ነጥብ ላይ የሚያተኵሩ እንደ
ሚሆኑ ማንሰላሰል ያሻል ። የእርሱን ጥያቄዎች አጥንቶ
አጥጋቢ መልሶችንም አቀነባብሮና ሸፋፍኖ ማቅረብ ይኖ
ራል ። ይህ ከታመነበት ደግሞ አንድ ጀርመናዊ በአስተሳ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰቡና በአሠራሩ አንድ አንድ እንግሊዛዊ ሊያስብና ሊሠራ አይችልም ይሆናል። የራሱ አስተሳሰብና አኗኗር አለው፤ ስለዚህ በእርሱ አእምሮ ውስጥ የአንድ እንግሊዛዊ አስተሳሰብ ሠርፆ መግባት አለበት።

በእንግሊዛዊው ወጥመድ ጀርመናዊው እንዲያዝ ለማድረግ ከተፈለገ ደግሞ ያ ሰው የሚያገኘው ሪፖርት ለማንኛው የጦር ባለሥልጣን እንደሚያቀርብ ማንሰላሰልን ያለ መርሳት አለ። ለምሳሌ ያህል የጀርመን ጦር አዛዦች የተባበሩት መንግሥታት የጦር ድርጅት የገጠመውን ዕንቅፋት አላወቁት ይሆናል እንበል፤ ምን ያህል የመጓጓዣ መርከብ እንዳለን አያውቁም፤ የኛ የጦር ባለሥልጣኖች በማያውቁት የጦርነት እንቅስቃሴ እቅድ ላይ የጠላት የጦር አዛዦች የሚቀበሉትና የሚተማመኑበት የማስመሰያ የዘመቻ እቅድ እንደምን ማውጣት እንደሚቻል አስቸጋሪ ነበር። የሚወጣው የማስመሰያ የዘመቻ እቅድ ጠላትን እንጂ የኛን የጦር አዛዦች የማያታልል መሆን እንዳለበት መዘንጋት አይቻልም። እርግጥ ነው ይህን ጉዳይ ሁሉም አባሎች ሳይሆኑ ጥቂቶቹ ማወቅና መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። በዚህ ሁሉ ምክንያት ከአንዳንድ ዕንቅፋቶች ጋር ተጋፈጥን፤ ችግሮቹን ከማውሳቴ በፊት ስለ መሸፋፈኛው ዓላማ ወይም እቅድ በመጠኑ ላወሳ እወዳለሁ።

በምታቅደው ትክክለኛ ሐሳብህ ላይ ጠላትህ እንዲያተኩርብህ ከፈለግህ አቅጣጫውንና አጥቂነቱን ወደ ሌላ


t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ እንዲመልስ ብዙ መጣጣር ሊኖርብህ ነው ። ከተቻለህም እውነተኛውን አቅጣጫህን ላለመከተል መወሰንህን ጠላትህ እንዲተማመን ተጣጣርበት ፤ አስተሳሰብ ህን ዝንባሌህንና እቅድህን ወደ ሌላ ማዛወርህን የማስመ ሰያ ዒላማህን ተፎካካሪህ እንዲረዳው አድርግለት ።

ባለፉት ገጾች እንደ ተጠቀሰው አንድ የዘመቻ እቅድ ሲዘጋጅ ወሬ መሹለኩ የተለመደ ነው ፤ ያን ቀዳዳ ለመድ ፈንም የመረጃ ሠራተኞች ልዩ ልዩ ብልሃት ይፈጥራሉ ፤ በዚህም ጊዜ የሚረዳቸው ዋናውን እቅድ ለማስመሰያው እቅድ ተደራቢ ማድረጉ ይሆናል ።

ለምሳሌ ያህል የሴሮቴንን ደሴቶች ለመውረር ያወጣ ነውን እቅድ ለመፈጸም የወታደሮች መለዮ እንዲዘጋጅም ትእዛዝ የመተላለፉ ነገር በወሬ ወሬ ቢሰማ ጠላት የሚያ ስበው ዋናው ዒላማችን በሌላ አቅጣጫ እንጅ ፤ በእርግጥ ደሴቶቹ እንደ ማይሆኑ አድርጎ ነው ። በተጨማሪም ወታ ደሮቹን የሚያጓጉዙ መርከቦች ትእዛዝ ወይም ሌላ ወሬ እንዲደርሳቸው ቢደረግ ፤ በዚያም ላይ ወደ ማስመሰያው አቅጣጫ ለመዝመት እንዲዘጋጁ ሆኖ ቢነግራቸው (ለም ሳሌ ያህል ወደ ዳካር) እንበል ከየአቅጣጫዎቹ ለጀርመን የሚተላለፉት ወሬዎች ራሳቸው የጀርመን የመረጃ ክፍ ሎች ከሚያቀርቡት ወሬ ጋር ይደማመርና ለጀርመኖች እንዲደርስ የሚፈለገው ወሬ በእርግጥ ተቀነባብሮ ሊቀር ብላቸው ይችላል ማለት ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዋናው ዲላማ በታና አቅጣጫ የማታለያው ዲላማ ሩቅ የሆነ እንደሆነ ደግሞ ይበልጥ ዋጋ ይኖረዋል። ምክንያቱም በባሕር በየብስና በአየር ለመከላከል ሲል ጠላት የሚያደርገው መሰናዶ እውነተኛው ዲላማ ላለበት ቀበሌ ወለል ብሎ የሚታይና የሚታወቅ ስለሚሆን ነው። ነገሩንም እያጋነኑ በምሳሌ ለማስረዳት ይቻላል። ይህም ማለት የሰሜን አፍሪቃን ለመውረር ዋናው ዲላማ ከሆነ፤ ጠላት ደግሞ ወደ ኖርዌይ የሚዘምት መስሎት ቢሰናዳና ቢከታተል ግሩም ድንቅ ሕልም ነው እንጅ፤ ኃይሉንም ሁሉ ወደዚያው ወደ ኖርዌይ እንዲያተኵር ቢያደርገው ዋናውን ዲላማ ለመምታት በሚደረገው ጦርነት ላይ ሊከላከልም ሆነ ሊያደናቅፍ የማይቻለው ይሆናል።

እውነተኛ ጦርነት በተጀመረበት ወቅት ግን የማስመሰያው ዲላማ በዋናው የጦርነት ቀበሌ ዙሪያ ቢሆን መልካም ነው። ምክንያቱም የጠላትን ኃይል ሙሉ ለሙሉ አዛውሮ ለመዋጋት ይቸግረዋል።

ለምሳሌም በ፲፱፻፵፪ ዓ. ም የሰሜን አፍሪቃን ለመያዝ በዘመትንበት ጊዜ የማስመሰያውን የጦር ሜዳ ሮሜል በነበረበቱ አካባቢ እንበል፤ በቱበርግ ግድም ቢሆን ኑሮና ጀርመኖችም በነገሩ እንዲያምኑበት ለማድረግ ችለን ቢሆን ኑሮ ምናልባትም የምድርና የአየር ጦር ኃይሉ አቅጣጫውን ለውጦ ወደ ማስመሰያው የጦር መስመር እንዲዘምትም ለማድረግ እንችል ነበር። በዚህ አንጻር ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

የባሕር ኃይሉ ደግሞ ወደ ጅብራላታር የባሕር ሰላጤ ይዛወር ነበር፤ ያ-ቀበሌ ደግሞ ወደ ዋናውና እውነተኛው የጦር መሥመር ኃይላችን የሚንገዝበት ነበር፤ ከዚያም በኋላ ያላሰብነው ችግር ይደርስ ነበር ማለት ነው።

ስለዚህ እንደዚህ የመሳሰለውን ተከታታይ ጉዳይ በየረድፉ ማጥናትና የማስመሰያውን የጦር መስመር ከዋናው እውነተኛ የጦር መስመር ጋር አነጻጽሮ የሚያስከትለውን ጥቅምና ጉዳት ተንትኖ ከተረዱ በኋላ፤ ጠላትን ለማሳመን መጣጣር ያስፈልጋል።

ይህን የመሰሰለውን የቃል ጥናት በሥራ ላይ ለመግለጽ የመረጃ ድርጅታችንን ያጋጠመውን ችግር ለማቃለል ጀርመኖችም በማስመሰያው አቅዳችን እንዲተማመኑበት ለማድረግ ዋናው ዒላማችን ሲስሊ ያለመሆኗን ለማሳወቅ ተጣጣርን።

በሌላ ቀበሌ አዲስ ጦርነት ለማስነሳት እንደምናስብና ጀርመኖችም እውነት ነው ብለው እንዲከታተሉን ጊዜም አግኝተን በሌሎች የጦር ሠፈሮች የተከማቹትን ኃይሎቻችንን ለማጠናከር እንድንችል መጣጣር ጀመርን።

በተባበሩት መንግሥታት የጦር ድርጅት በኩል ነገሩን ስንመለከተው ደግሞ በጀኔራል አይዘንሀወር ሥር የሚመራ ጦር በፈረንሳይ ሰሜን አፍሪቃ ይዞታ በሚዲትራኒያ ጫፍ በኩል ነበር፤ ከዚህ ጦር ሌላ ደግሞ በፊልድ ማርሻል ሰር ሄንሪይ ዊልሰን የሚመራ ኃይል ግብጽ ውስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥ ነበረን፤ ሁለቱ ምድብ ጦርም የሰሜን አፍሪቃን የባ ሕር አቅጣጫ ይዘታል። ያን ያህል የዳበረና የተጠናከረው ኃይል ለመጠነኛ ጦርነት ብቻ እንደሚሰለፍ ተረድተን ዋል። ግን በሲስሊ በኩል ገብቶ ወደ ኢጣሊያ ለመዝለቅ ደግሞ በጠቅላላው ለማሰለፍ የምንችለውን ኃይል የሚጠ ይቅ ዘመቻ ሆነብን።

ያን ለማከናወን ደግሞ የነበረን የምድር ጦር እንከ ተኛ ከመሆኑም ሌላ በጦርነቱ ቀከፋይ የሚሆኑ የአየር ኃይል ተዋጊና ማጓጓዣ አይሮፕላኖች እጥረት ነበረብኝ፤ መርከቦችም ለጦሩ አስፈላጊውን ስንቅና ትጥቅ ለማቀ በል ሲመላለሱ በተዋጊ መርከቦች ለማሳጀብ የማይሳከልኝ ስለሚሆን በአንድ ጊዜ ሁለት የጦር መስመር ለመክፈት ፈጽሞ የማይቻል እንደሚሆን አስቀድመን ተረድተነው፡፡ በጀርመኖች በኩል ሆነን ጠቅላላ ይዞታውን ስንመለከ ተው ደግሞ፤ የተድበሰበሰ ነበር። በእነርሱ በኩል እንደ ተጠባበቁትና እንዳመኑበት በምዕራባዊ የሜዲትራኒያ ባሕር ሠፍሮ የነበረው የጀኔራል አይዘንሀወር ጦር የደ ቡብ ፈረንሳይን ግዛት ይደበድባል ብለው ገምተዋል። በዚህም ካመኑበት በሲስሊ በሳርዴኒያና በኮርሲካ የነበረ ውን ኃይላቸውን መቀነስ ነበረባቸው። ይህን እርምጃ ከወ ሰዱ የኛ ኃይል ኢጣሊያንን ለመያዝ ቢዘምት ለመከላ ከል እንደማይቻላቸው ግልጽ ነበር። በዚሁ ጊዜ ደግሞ ግብጽ የነበረው የኛ ጦር ኢጣሊያንን ለመያዝም እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF 

ሚቻለው ግልጥ ሆነ ። እንግዲህ በምዕራባዊ አቅጣጫ የነ
በረው የጦር ኃይላችን ለዚህ ግብ የሚዘምት ከሆነ በመጀ
መሪያ እንዳቀድነው ሲስሊን መውረር እጅግ አስፈላጊ
ሊሆንብን ነው ፤ በመጨረሻም በምሥራቅ በኩል የነበ
ረው የጦር ኃይል ግሪክን ይዞ ወደ ባልካን አገሮች እንዲ
ያመራ ለማድረግ የሚያመች ይሆናል ።

የመጓጓዣ ችግር የደረሰብን መሆኑን ጀርመኖች ለማ
ወቃቸው ደግሞ ፤ ማስተማመኛ አላገኘንም ፤ ምክንያ
ትም አልነበረም ። በሁለት አቅጣጫ ጦርነቱን ለመክፈት
ማሰባችንን ጀርመኖች ለማመን እንዲያውም ቀርበዋል ።
ሁለቱም አቅጣጫችን በጀኔራል አይዘንሀወርና በሰር ሄን
ረይ ዊልሰን የሚመራው ጦር ነበር ። የተጠረጠረው የማ
ስመሰያው ዘመቻ እቅድ ለማውጣት በምንወያይበት ጊዜ
ሁሉ ጉዳዮቹን በሚከተሉት ምክንያቶች ከፋፈልናቸው ።

የተባበሩት መንግሥታት ጦር አብዛኛው ክፍል ቱኒ
ዚያ ውስጥ መከማቸቱ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ በዚያ ከነበ
ረው ኃይል ቀንሰን የጀርመን አየር ኃይል በሠፈረበቱ
በሲስሊ አጠገብ ለማለፍ መጓዝና ጀርመኖችም በዚሁ እቅ
ዳችን እንዲተማመኑበት መሞከር ዋጋ የሌለው ይሆናል።

ስለዚህ የማስመሰያውን ጦርነት በምዕራብ ኢጣሊያ
ውስጥ እንዲጀመር ከቱኒዚያ የምንወስደውም ጦር የዚሁ
ዘመቻ ተከፋይ እንዲመስል ብናደርግ ምናልባት ጀርመ
ኖች እውነት ይመስላቸውና ይከታተሉናል ። ሳርዲኒያ ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ሲል በግልጽ ዘመቻ የምናደርግበት አስመስለናታል ። ወደዚያ ለመሄድ ደግሞ በሲሲሊ በኩል እንደምናልፍ አስመስለናል ። ጦራችን በሲሲሊ በኩል አልፎ ፎዘምትና ሁለቱን አገሮች ማለት ሳርዴኒያንና ኮርሲካን ለመያዝ እንደ ተዘጋጀ ፤ ከዚያም ቀጥሎ የኢጣሊያንን የባሕር አካባቢ ለመያዝና በደቡብ ፈረንሳይ ጦርነቱን ለመጀመር እንደሚያስችለን በግልጽ የታወቀ ያስመሰልነው እንደሆነ ፤ የዚህም እቅዳችን ዜና ለጀርመኖች መድረሱ ወይም ያለመድረሱን ማረጋገጥ ስለማይቻለን አንድ የምሥጢር ጽሑፍ አዘጋጅተን ብንልክ ለመስፈንጠራችን ሁለተኛው ኸበ ሊሆንልን ይችላል የሚል አስተሳሰብ አፈለቅሁ ።

በተጨማሪም ጀርመኖችን ለማታለል በሰር ሄንሪይ ዊልሰን የሚመራውና በፊልድ ማርሻል ሞንትጎመሪ የሚታዘዘው ጦር በምናዘጋጀው ጦርነት ተካፋይ እንደማይሆን ማስመሰልና በጀኔራል አይዘንሀወር የሚታዘዘው ጦር ግሪክን ይዞ ወደ ባልካን አገሮች ለመዝለቅ እንደሚዘጋጅ ማስመሰሉም የተሻለ ይሆናል ብዬ አሰብኩ ።

በእነዚህ በሁለቱ እቅዶች ለማመን ጀርመኖች እንደማይጠራጠሩ ተረዳሁ ። በዚህ እቅዳችን ከተማመኑበትም ኃይላቸውን ይበታትኑትና እኛም ሳርዴኒያን ብቻ ለመያዝ የምንዘጋጅ ለመሆን እንችላለን ብዬ ተማመንኩ ። የእነዚህን እቅዶች ዝርዝር ጥናት ከፈጸምኩ በኋላ ፤ ለጀኔራል አሌክሳንደር በምሥጢር አንድ ደብዳቤ እንዲጻፍና ፀጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስጡም በሁለት አቅጣጫ ጦርነቱን እንድምንጀምር እንዲ ገለጽ ፈለግሁ ። በምሥጢሩ ደብዳቤውም ላይ በጀኔራል አይዘንሀወር የሚታዘዘው ጦር ሳርዴኒያንና ምናልባትም ኮርሲካን ለመያዝ እንደሚዘምት በፊልድ ማርሻል ሰር ሄንሪይ ዊልሰን እዝ የሚመራው ጦር ደግሞ ግሪክን ለመ ያዝ እንዲዘምት እንደዚሁም ሲስሊንም ለመውረር እንደ ምንዘጋጅ በደብዳቤው ላይ እንዲገለጽ ሐሳብ አቀረብኩ ። የዚህ ሐሳብ ውበቱና ጥራቱም የሚታወቀው ስለ እውነ ተኛው እቅዳችን ጀርመኖች ወሬ የሰሙብን እንደሆነ፤ የማስመሰያውን እቅዳችንን በደብዳቤ ስለሚያገኙት ከወ ሬው ይበልጥ እምነት ይጥሉበትና ይዘጋጃሉ፤ በደብዳቤ የምናቀርብላቸውን የማታለያ ጉርሻ ከዋጡልንም ስለ ዋና ው እቅዳችን ሊደርሳቸው የሚችለውን ትክክለኛውንም ወሬ ላይቀበሉት ይችላሉ ተብሎ ታቀደ ።

ስለዚህ ይኸው ሐሳብ ለጦሩ ችፍ አቭ እስታፍ ሲቀ ርብ፤ የጉዳዩም አስቸጋሪነት ተያይዞ ተቀጣጠለ፡ ለተለመ ደው መሥመር እቅዱን ብዙ ሰዎች አላዩትም፤ መሥመ ሩን ተከትሎ እንዲቀርብ አልተደረገም ። ቢሆንም እቅ ዱና ረቂቁ ወደ ብዙ ባለሥልጣኖች ጽ/ቤት መግባትና መታየት ግዴታ ሆነበት፤ ሁሉ የተራቀቀ ችሎታ ያለው የጀርመኖችን ጠባይና ምንነት አሳምሮ የሚያውቅ ይመስ ላል ። ግን እጅግ አደገኛ ጉዳይ ነበር ። ደብዳቤው በዝቅ ተኛ መኰንኖች እንዲዘጋጅና እንዲፈረም አንዳንዶቹ ጠ



t.me/OLDBOOKSPDF

የቃ፤ በዚህ ሐሳብ መሠረት ብንገፋበት ጀርመኖች ታሪ ኩን አምነው ስለማይቀበሉን ሲሲሊን እንይዛለን የምን ለው እቅዳችንና ተስፋችን አማራጭ የሌለው ይሆንብ ናል። ሳርዲኒያ ዋናው ዒላማችን መሆኗን መግለጽ የለብ ንም ፤ ከምናቀርብላቸው የማታለያ እቅዳችን ላይ ጀርመ ኖች መረዳት የሚችሉት ሲሲሊ ዋናዋ ዒላማችን መሆ ኗን ነው።

የጠቅላላው እቅዳችንና የምንጠባበቀውም ውጤት የበላዮቻችን በመጀመሪያ አምነውበት ሁለተኛም የማይ ገኝ አጋጣሚ መሆኑን ተረድተውት እንዲከታተሉት ስለ ሆነ ማነሣሣትም የነበረብን ወደ ከፍተኛዎቹ ባለሥልጣኖች ነበር።

እኔም ነገሩን ሳንሰላስለው የጀርመንን ከፍተኛ የጦር አዛዦች ለማታለል መታገል የእነርሱው ተቃራኒ የነበሩ ትን አስቸጋሪዎቹን እንግሊዛውያን የጦር ባለሥልጣኖች ለማሳመን እንደ መጣጣር ያህል ሆኖ ተሰማኝ። ይህም ማለት ተጠራጣሪዎቹን ጀርመኖች ለማታለል እልኸኞቹ ንና ችኮዎቹን አለቆቻችንን ማሳመን ነበረብን።

እንደ መታደል ሆነና ከጥቂት ውይይት በኋላ፤ ሰር አርችባልድ ነይ በቁልፍልፉ ጨዋታ ውስጥ ገቡበት። እኔ ባቀረብኩት ረቂቅ መሠረት ደብዳቤውን ራሳቸው ማቀነባ በር ቀጠሉ። በደብዳቤውም ላይ የመሸፋፈኛው ዒላማ እንደ ትክክለኛው ግብ ተገምቶ እንዲጠቀስ ራሳቸው ተስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሙበት ። ደብዳቤውም በአንድ የጦር መኰንን ኪ.ስ ከሚ ላክ ይልቅ በመሥሪያ ቤቱ ከረጢት ወይም ሻንጣ ውስጥ እንዲላክ ተስማሙበት ። ከዚያም በኋላ ራሳቸው አስገ ራሚ የሆነውን ደብዳቤ ጻፉት ። በዚያም ደብዳቤ ላይ የማታለሉን ተግባራችንን የሚያሳምንልንን ተግባር አቀነ ባበሩት ። ጀርመኖች (በማታለያ ቃል ሐሳኪ ብለን ስለ ሰየምነው) ሲስሊ ዘመቻ ጉዳይ የሰሙብንም እንደሆነ፤ "ሐሰኪ" የሚለው የምሥጢር ቃል ወደ ግሪክ ለሚዘም ተው ጦር ምልክት እንዲሆን ሳርዴኒያንም ለመያዝ ለሚ ዘምተው ጦር "ብረም እስቶን" የሚለው አጠራር የምሥ ጢር መታወቂያ እንዲሆን ራሳቸው ወሰኑና የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ ።

ስልክ ኋይት ሆል 9400
የንጉሥ ነገሥቱ የጦር ኃይል
ጠቅላይ እዝ ጽ/ቤት ።

የጦር ሚኒስቴር
ኋይት ሆል
ለንደን ኤስ ዳብልዩ
ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ. ም.

የግልና ብርቱ ምሥጢር
የማፈቅርህ አሌክሳንደር ።

ከማውንትባትን የጦር መኰንኖች አንዱ ወደዚያው የሚመጣ በመሆኑ ይህን ማስታወሻ ልጽፍልህ ወደድኩ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህም አጋጣሚ በሜዲትራኒያ ባሕር አካባቢ ስላለው የጦር ኃይላችን እንቅስቃሴ ጉዳይ የተላላክንባቸውንና የተወያየንባቸውን አቅዶች ልገልጽልህ እወዳለሁ። ይህንም ሐሳባችንን ከዋናው ጉዳይ እንደሸሸንና አማካይ ውሳኔ እንደተከተልን አድርገህ ትመለከተው ይሆናል። ግን የጦሩ ዋና የእዝ ድርግ እንተና የመከከለኛው ምሥራቅ ጦር ዋና አዛዥ ፊልድ ማርሻል ሰር ሄንረይ ዊልሰን ያስተላለፉችሁትን ጉዳይ ሁሉ በዝርዝሩ በጥንቃቄ የተወያየበት መሆኑን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ።

በቅርቡ ከደረሰን የተረጋገጠ ዜና ላይ መረዳት እንደቻልነው በግሪክና በክሪይት የሠፈረው የጠላት ኃይል እጅግ ተጠናክሯል ይባላል። የኛም የጦር ኃይል ደርግ በአሁኑ ይዞታችን የጠላትን ጦር ለመግጠም ያልተዘጋጀና ያልተጠናከረ መሆኑን ተረድቶታል።

የጦሩ የበላይ እዝ ድርግም የ፩ኛው ክፍለ ጦራችን አንድ ብርጌድ [illegible] ተጨምሮለት፣ በደቡብ ኬፕ አራኮስ የባሕር [illegible] ሽመጥ ለምናደርገው ወረራ እንዲዘጋጅና እንደዚሁም በካላማታ የሠፈረው ፺፯ኛው ክፍለ ጦራችን ተመሳስዩ የኃይል ጭማሬ እንዲደረግለት ስለ ተወሰነ፣ አስፈላጊውን ዝግጅት በማሟላት ላይ ነን።

ሰር ሄንረይ ዊልሰን ሲስሊ የማስመሰያዋ ዒላማችን እንድትሆን ሐሳብ አቅርበዋል፤ እኛ ግን የመረጥነው ሳርዲኒያን ነው፤ የጦራችን እዝ ድርግ የቀረቡለትን ጉዳዮች



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ መርምሯል ። በአልጀሪያ በኩል ፣የሚደረገውን ዝግጅት ለማከናወን በቱኒዚያ የባሕር ዳርቻ በኩል የሁለገብ ወታደራዊ ልምምድ ይሰጣል ፤ በሲስሊ የሚገኘው የአይሮፕላን ማረፊያ በከባድ በምብ ይደበደብና ከጥቅም ውጭ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ አጥብቀን ልንከተለው የሚያስፈልገን የሳርዲኒያውን እቅዳችንን ነው ። በአጭሩ በጉዳዩ ራሱ ሐሳብ አቅራቢው እንዲያስብበት ለማድረግ አጋጣሚው ሁሉ ረድቶናል ፤ የሲስሊው ዘመቻችን ራሱን የእልኸኛነት ጠበይ የሚያመለክት ሊሆንበት ይችላል ።

በሌላው በኩል ደግሞ በምሥራቅ ሜዲትራኒያ በኩል ያለው ኃይል ወደ ሲስሊ ለመዝመት መዘጋጀቱን ሊያምንበት የማይቻለው ለመሆኑ አያጠራጥርም ። ስለዚህ የዊልሰን የማስመሰያው እቅዱ ወደ ሌላ አቅጣጫ ለምሳሌ ድክንስ እንዲያተኩር ተነግሮታል ።

ከቱርክም ጋር ያለን ወዳጅነት የተቀራረበ በመሆኑ በዚያ አካባቢ ያሉት ደሴቶች ሁኔታ ኢጣሊያኖችንም ስጋት ሳያሣድርባቸው አይቀርም ።

አንተም በዚህ ሐሳባችን እንደምትስማማ አምናለሁ ። በጉዳዩ የምትገባበት ብትሆንም ቅሉ ስለ ወደፊቱ የዘመቻ እቅዳችን ከአይዘንሀወር ጋር ለመወያየት አጋጣሚ ጊዜ አላገኘህም ።

ግን እንደ አጋጣሚ ሆኖ የዊልሰንን ሐሳብ የምትደግፍ ከሆነ፣ በፍጥነት እንደምታስታውቀን ተስፋ አደርጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁ ። ምክንያቱም በዚህ ነገር ብዙም መዘግየት ስለ ማይ ገባን ነው ።

ለጋርድ ብርጌድ ሌላ አዛዥ እንዲሰጥህ ለማድረግ ባለመቻላችን በጣም አዝናለሁ ። የመረጥከው መኰንን በብርቱ ሕመም ስለ ሚሰቃይ ለጥቂት ሳምንታት ያህል ሥራውን ሊረከብ አይችልም ፤ ፎርሰርተን በግል እንደ ምታውቀው አልጠራጠርም ። በአገራችን ውስጥም ሆኖ በብርጌድ አዛዥነቱ የተመሰገነ ስለሆነ ፤ በአሁኑም ጊዜ የተሻለውና ለመምጣትም የሚችለው እርሱው ነው ።

ስለ ጠቅላላው የጦር ሜዳሊያ ጉዳይ እኛ የምናውቀ ውን ያህል ላንተም ልናሳውቅህ ይገባል ። አንተ እንደ ገለጽከው ወዳጆቻችንን አሜሪካኖችን ለማሳዘን አንፈቅ ድም ፤ ግን ከዚህ የበለጠ ሌላ አሳሳቢ ነገር ደግሞ አለ ። ከአሜሪካ ወታደሮች ጋር ጐን ለጐን ተሰልፈው በአንድ የጦርነት ቦታ ለተዋጉት ወታደሮቻችን ልዩ የሜዳሊያ ሽልማት የሚሰጣቸው ከሆነ ፤ በጦርነት መሥመር በተሰለ ፈው ኃይል መካከል ጥላቻና ያለመተማመን መፍጠራችን ነው ፤ ወይም ከዚህ ላቅ ያለ ሁናቴም ሊፈጠር ይችላል ። ስለዚህ እኔ በበኩሌ የማስበው አሜሪካኖች በበጎ ፈቃደኝ ነት ስለሚያደርጉት ስጦታ ማመስገን እንጂ መቀበል አያ ስፈልግም ፤ ይህነኑም ልዩነት የሚፈጥርብን መሆኑን በት ክክል ማስረዳት ያስፈልጋል ። የሆነ ሆኖ የጦር ባለሥልጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኖቹ በሚቀጥለው ስብሰባቸው እንዲነጋገሩበት ይቀርባል። የሚሰጠውም ውሳኔ በቅርቡ ይተላለፍልናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ።

መልካም ዕድል እመኝልሃለሁ
ምን ጊዜም ያንተው
አርቾል ነይ ።

I

ከዚህ የተሻለ ሌላ አማራጭ አልነበረም ፤ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበረ አንድ ሰው ስለሚያውቀው ጠቅላላ ጉዳይ ለወዳጁ የሚገልጽለት አጻጻፍ በመምሰሉና ዋናውንም ጉዳይ አጠቃልሎ የሚገልጽ በመሆኑ ተስማማንበት ምክንያቶችን ይገልጻል ። ምክንያትም ይሰጣል ። ጀርመኖችም አውቆ የተደረገ ነው ብለው እንዳይጠራጠሩ ይከለክላቸዋል ። በምሥራቅ ሜዲትራኒያ ጦርነት እንደሚነሳና ግሪክ ለመግባት መታሰቡን ይገልጻል ፤ በሌላው በኩልም በምዕራብ ከሜዲትራኒያ አቅጣጫ ሲስሊን ለመያዝ ሲባል (ይኸውም እውነተኛው እቅድ አልነበረም) ዘመቻ ለማድረግ እንደሚታሰብ ጀርመኖችም እንዲጨነቁበት ይወተውታል ። ደብዳቤው ግላዊ ሆኖ መንግሥታዊ እቅድ ያመለክታል። ቢሆንም መንግሥታዊ ተልእኮ የለውም።

እኔ ግን ሁለት የተጸጸትኩባቸው ምክንያቶች ነበሩኝ። ይኸውም ፩ኛ ጀርመኖችን እንደማወቄ መጠን የምዕራብ ውያን ቁርጥ ያለ ግዴታ ነው ብለው ጀርመኖች ሊተማመኑበት የሚያስችል መሥመር እንዲያብራራ ለማድረግ እስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤ ላለ ፣ የጠና የበላይ ትእዛዝ ሰጭ ግን ሳርዲኒያ በደብዳ
ቤው ላይ መጠራት አያስፈልጋትም ብለው ተቃውመው
ስለ ነበረ ነው ። ቃ ካንያቃቸውም ጀርመኖች የምናደርገ
ውን እንቅስቃሴ ተከታትለው ሲሲሊ ዋናዋ መዳረሻችን
መሆኗን ያወቁብን እንዳሆን ያስቸግረናል ብለው ነበር ።

የሆነ ሆኖ እኔ ስለ ጠቃቀስኩት ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒ
ስትሩ ከአድናቆት ጋር ከተቀበሉት በኋላ ሎርድ ማውን
ትባተን እንዲፈርሙበት ባዘጋጀነው ደብዳቤ ላይ የሳርዲ
ኒያን ጉዳይ ጠቅሼ ስለ ጻፍኩና በአዝል ስላስገባሁበት ፣
ወደፊት እንደምናገኘው ግምት የሚጣልበት ዋጋ አስገ
ኝቷል ።

ሁለተኛው ቅሬታዬ እንኳን አጅግም አሳሳቢ አልነበ
ረም እንጅ እንዲህ ነበር ። በደብዳቤው ላይ አንድ ነገር
እንዲጨመርበት ፈልጌ ነበር ። አንድ ጀርመናዊ አስቀድሞ
የሰማው ጉዳይ በደብዳቤው እንዲሠፍር ፈለግሁ ። ደብዳ
ቤው እውነተኛና እምነት የሚጣልበት እንዲመስል አብዛ
ኛዎቹ ጀርመኖች ስለኛ የውስጥ አሠራርና ግላዊም ጠባይ
አስቀድመው ከሚያውቁብን አንድ ነገር እንዲጨመር አሰ
ብኩ ጉዳትም ሆነ ። ጥርጣሬ የሚያስከትል ነገር ከደብዳ
ቤው ውስጥ እንዲጨመር ያሰብኩትም በጀኔራል ሞንት
ጎመሪ ላይ የሚሰነዘረው የተለመደው ቀልድ በጀርመኖች
ጠባራ አእምሮ ላይ ፈገግታ ይፈጥር ይሆናል ብዬ ነበር ።
ሰር አርችባልድ ለጀኔራል አሌክሳንደር በሚጽፉት ደብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዳቤ ላይ እንዲገባ ያሰብኩትም በረፍተ ነገር "ምንት ነመፊን ምን እንግዳ ነገር አጋጠመው ? እንደ ተለመደው በየቀኑ ሲያስተላልፍ የነበረውን ትእዛዝ ለሳምንት ያህል አቋርጧል !" የሚል ነበረ ።

ይሁንና ያ-የቀልድ ሐሳብ ጠቃሚ ስላልነበረ በመ ቅረቱ ተስማማሁ ። ግን እንደዚህ የመሳሰለውን ቀልድ ጀርመኖች እንደሚወዱት አምንበት ነበር ።

የሰር አርችባልድ ደብዳቤ በራሳቸው የማስታወሻ መጻፊያ ወረቀት ላይ በመኪና ተጻፈ ። አድራሻውም "የማ ፈቅርህ አሌክሳንደር" ተባለና ራሳቸው ፈረሙበት ፤ ወረ ቀቱ ተጣጠፈና በደንበኛው ኢንቮሎፕ ውስጥ ገባ ። ያም መሠረታዊው ደብዳቤያችን ነበር ፤ በዕለተ ጊዮርጊስ ወደ ... ቻም ለመሄድ ሁሉ ነገር ተሰናዳለት ።

## የሺላቃ ማርቲን ፤
## የሮያል ባሕር ኃይል ባልደረባ ።

"መሠረታዊው ደብዳቤ" ብለን የሰየምነውን ጽሑፍ በምናዘጋጅበት ወቅት ይህንኑ ደብዳቤ ይዞ ስለሚሄደው ሰውዬ ደኅንነት እናስብ ነበር ። ሁላችንም እንደ ገመትነው በርሊን የነበሩት ተፎካካሪዎቻችን የመጀመሪያው ጥያቄያ ቸው ደብዳቤው እንደምን ወደ ሂውልባ ባሕር ዳር ሊደ ርስ ቻለ ? የሚል ይሆናል ፤ እርግጥ ነው ደብዳቤው በአ ንድ መኮንን ኪስ እንጂ በመሥሪያ ቤቱ ከረጢት የሚላክ



t.me/OLDBOOKSPDF

አልነበረም። የሆነው ሆኖ የጀርመን የመረጃ ክፍል ደግሞ ዋናው ጥያቄ ደብዳቤውን እርግጥ ያመጣው የመኰንን ነት ማዕረግ ያለው ሰው ነው? በእርግጥስ እውነተኛ የጦር መኰንን ነው? የሚል እንደሚሆን አስቀድመን ተረድተ ነዋል። ስለዚህ የመጀመሪያ ተግባራችን ሬሳው የአንድ የጦር መኰንን የሚመስልበትን ተግባር ማከናወን ሆነ። ለገቢረ-ፍላጎታችን የሚረዳን የደንብ ልብስ አልነበረውም፤ ማንነቱን ለመደበቅም ቃል ገብቻለሁ። በዚህ ሁሉ ምክን ያት አዲስ የደንብ ልብስ ማዘጋጀትየግዴታችን ነበረ።

ሬሳው ወደ አዲሱ ታዋቂነቱ ሲመስል የእግረኛ ጦር መኰንን የማዕረግ ልብስ እንዲለብስና ከጦር ሚኒስቴር ጽ/ቤት ወረቀት ይዞ ወደ ጦሩ ጠ/ጽ/ቤት የሚላክ ለማ ስመሰል ታቅዶ፤ ነገሩን በዝርዝር ካጠናነው በኋላ ግን የእ ግረኛ ጦር የማዕረግ ልብስ ማከናነቡን ተቃወምነው፤ ወደ ዚህ ሐሳብ የመጣንበት ብዙ ምክንያቶች ደግሞ ነበሩን።

ዋናውና አሳሳቢ የነበረውም ነገር ሬሳው በእስፐይን ባሕር ዳር ከደረሰ በኋላ ማድሪድ በሚገኘው የወታደር ጉዳይ ኃላፊና በለንደን መካከል ሊኖር የሚገባው መልእ ክት ምልክትና ሬሳውን የመረከቡ ጉዳዮች ነበሩ።

ጉዳዩ ለሚመለከተው ጽ/ቤት የተለመደውን ቴሌግ ራምና መልእክት ማስተላለፍ ይቻላል። ከዚያ በኋላ እንደ ጉዳዩ ዓይነትና አስፈላጊነት እየታየ መልእክቱ ለየኃላፊ ዎቹ ይታደላል፤ አከፋፈሉም እንደ ማደያው ክፍል ዝር ዝር ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚሁ አሠራር መሠረት በእስፐዩን የባሕር ዳርቻ ላይ ሲንሳፈፍ ስለ ተገኘው ሬሳ ጉዳዩ የሚተላለፈው መል እክት እንደ ተለመደው ከብዙ የክፍል ሹማምንት እጅ ሊደርስ ነው ። በባሕር ኃይሉ ጠ/ጽሕፈት ቤት የአሠራር ደንብ መሠረት ጉዳዩ መፈጸም የሚገባው በኔ ነበር፤ ለኔ ከተላለፈልኝም ወደ ብዙ ክፍል ላይዘመትና ብዙም ወሬ ና ትችት ላይከተል ይችላል ።

በጦር ሚኒስቴሩ ጽ/ቤት አሠራር የውስጥ ደንብ መሠ ረት ደግሞ እንደዚህ የመሰሰለውን ጉዳይ ለኔ ወይም የኔ የሥራ ጓደኛዬ ለሆነው መኰንን በቀላሉና በተቀላጠፈ ዘዴ ለማድረስ አስቸጋሪነት ነበረበት ። በዚህ ምክንያት ሬሳው የእግረኛ ጦር ባልደረባ እንዳይሆን ወሰንን ። በባሕር ኃይሉ የአሠራር ደንብ መሠረት ቢፈጸም ይሻላል አልን። ወዲያው ደግሞ አስቀድመን ያላስተዋልናቸው የችግር ምክንያቶች ተከታትለው ደረሱብን፤ ሬሳው በቀላሉ የባሕር ኃይል ባል ደረባ መኰንን ሊሆን አይቻለውም ። ምክንያቱም አንድ የምድር ጦር መኰንን ከለንደን በሰሜን ፡ፍሪቃ ወደሚገ ኘው ጠቅላይ ጽ/ቤት እንዲላክ ስናደርግ የጦር ሜዳ ል ብስ መልበስ ይኖርበታል ። የባሕር ኃይል መኰንንም እንደዚሁ ተገቢውን የደንብ ልብሱን መልበስ ይገባዋል ። በዚህ አስተሳሰብ የጦር ሜዳ ልብስ ለትክክለኛነት ተስ ማሚ ላይሆን ነው፤ የባሕር ኃይሉ የደንብ ልብስ መዘጋ ጀት የሚገባው ሆኖ ተገኘ ። አንድ አስፈሪ የዐፅም ቅርፅ



t.me/OLDBOOKSPDF

አዘጋጅተን የትጥቅ ክፍላችን እንዲለከው አደረግንና በዚሁ ተገላገልን ። ሬሳው የባሕር ኃይል አባልነቱ እንዲታወቅ ለማድረግ ደግሞ በሮያል ማሪን (የባሕር ኃይል እግረኛ ተዋጊ) ክፍል ውስጥ መመደብ አስፈለገ ። በደንብ ልብስ በኩል ያለው ችግር በዚህ ይቃለላል ብለን አሰብን ። ግን ሌሎች ችግሮችን ደግሞ አዘለብን ።

በመጀመሪያ ነገር የጦርነት ጊዜ የጦር ሠራዊት ብዛቱ በዕጥፍ ስለሚጨመር ፤ በአንዱ ክፍል የሚገኘውን መኰንን በሌላው ክፍል የሚገኘው ስለማያውቀው በአንድ መኰንን ላይ አንድ ነገር ቢደርስ ሌላው ግድ አይኖረውም ። በዚህ አንጻር ደግሞ የሮያል ማሪን ክፍሎች ብዛታቸው የተመጠነ ነው ። በጦርነት ጊዜም ቢሆን መኰንኖቹ አልፎ አልፎ በጭልፍታም ቢሆን ይተዋወቃሉ ።

ሁለተኛ ደግሞ ፎቶግራፍ የማግኘቱ ነገር አስቸጋሪ ሆነ ፤ ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ ሆነብን ። የሞተውን ጉልማሳ ሰው ሬሳ ለሥራ ጉዳይ ለማሠማራት ስናስብ ለመታወቂያው የምናውለው ፎቶግራፍ ማግኘት አስፈለገ ፤ በሌላው በኩል ደግሞ አንድ የጦር ሠራዊት አባል የሆነ መኰንን ወደ ውጭ አገር ሲላክ የመታወቂያ ወረቀት አይዝም ፤ አንድ የማሪን መኰንን ግን ይዞ መገኘት ይኖርበታል ።

በዚሁ ችግር ላይ ደግሞ ተወያየንበት ፤ የሮያል ማሪን መኰንን ነበረ ብለን የምናዘጋጀው ሬሳ የክፍሉ መኰን



t.me/OLDBOOKSPDF

ኖች ጥቂቶች ከመሆናቸው የተነሳ ነገሩ ይገላለጥብንና አደጋ ሊፈጥርብን እንደሚችል ተረዳነው ።

ይህን አስተሳሰብ የፈጠረብን ምክንያትም እስፓንሾች ሬሳውን እንዲቀበር ወደ ጅብራላታር የሰደዱት እንደሆነ፤ ነገሩ እየተገላለጠና አጠራጣሪነቱ እየጐላ ሊሄድብን ይችላል ፤ ግን በሄውልባና በጅብራላታር መካከል ያለው ርቀት ደግሞ ሬሳውን ከመመለስ ያከላክለዋል ብለን ተማመን ። ስለዚህ ፎቶግራፍ ወደ ማግኘቱ አዘነበልን ፤ ግን የቱን ያህል ችግር እንዳጋጠመን የተረዳነው በኋላ ሆነ ።

በመጀመሪያ ከወታደሮቻችን መካከል ተስማሚ ሰው ቢገኝ ፎቶግራፍ ለማንሳት ሞከርን ተስፋ የሌለው ሙከራ ሆነብን ። ለተግባራችን የምናውለው ፎቶግራፍ ለማግኘት በሕይወት ከሚገኙት አንዱን ብንስለው "እንደ ሞትኩ አስመሰለኝ" የሚል ትችት እንደሚነሳብን ተረዳነው ። ቢሆንም ትችቱ እንኳ ሊስተካከል ወይም ላይሆንም ይችላል ፤ ምክንያቱም የምናነሳው ፎቶግራፍ የሰውየውን ሕያውነት አንጂ መዋቲነት የማይናገር ነበር ። የሆነው ሆኖ የሞተ ሰው የሚመስል ፎቶግራፍ ለማግኘት እጅግ በጣም አስቸጋሪና ተስፋ ቢስ እንደ ነበረን ለመግለጽ ያስቸግራል ።

ቢሆንም በተቻለ መጠን ሬሳው በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሊመሳሰለው የሚችል ተድበስብሶ የተነሳ ፎቶግራፍ ለማግኘት ፍለጋችንን በሰፊው ቀጠልን ፤ በእርግጥ እዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋች ሆነብን፤ ቢሆንም በየጉዳናው የምናየውን ሰው ሁሉ እየገላመጥን የሚመሳሰል ሰው ፍለጋ ቀጠልን፤ በመጨረሻ በባሕር ኃይላችን የመረጃ ድርጅት ውስጥ ይሠራ የነበረ አንድ ወጣት መኰንን አገኘሁ። ምን ቃል ተናግሬ ይቅርታ እንደ ጠየቅሁት ትዝ አይለኝም እንጂ፤ ፎቶግራፍ አነሳነው፤ እርግጥ ጥሩ ፎቶግራፍ አልነበረም፤ ቢሆንም ተድበስብሶ የተነሳ በመጠኑ ተቀራራቢነት የሚታይበት በመሆኑ በቂ ሆኖ አገኘነው።

ከዚሀ በኋላ ግን ሌላ ዕድል አጋጠመን፤ ከኛው ጋር እየተሰበሰበ ስለ ብዙ ጉዳዮች ሲነጋገር የነበረ መኰንን የተቀራረበ ተመሳሳይነት የሚታይበት ሆኖ ስላገኘነው፤ እርሱኑ ፎቶግራፍ አነሳንና ዕንቅፋቱን ፈነቀልነው። ይህን ሁሉ ከዘጋጀን በኋላ፤ ለሬሳው የመኰንንነት ማዕርግ ከመስጠታችን በፊት ስሙን መሰየምና የማዕርጉን ደረጃ መወሰን ደግሞ አስፈለገን። የበታች መኰንን የሆነ እንደ ሆነ እንደዚያ ያለውን ብርቱ ምሥጢር ያለበትን ደብዳቤ ለመያዝ የማይቻለው ይሆናል፤ ቢሆንም ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው መኰንንም ለማስመሰል በብዙ ምክንያቶች አልፈለግንም።

በሥራው ውጤት በንቃቱ ገና በወጣትነቱ ግምት የሚጣልበት ማዕርግ ያገኘ ጉልማሳ ለማስመሰል ፈለግን፤ የሻምበልነት ማዕርግ አግኝቶ (ጥብቅ ሻለቃ) እንዲሆን መረጥኩ፤ ወዲያው የባሕር ኃይሉን መኰንኖች የስም



t.me/OLDBOOKSPDF

ዝርዝር አቀረብኩና መመለከከት ጀመርኩ፤ ፍላጎቴም ተመሳሳይ ማዕርግና ስም ያላቸውን ለመለየት ነበር ። በዚሁም መሠረት "ማርቲን" የሚለው ስም ተስማሚ ሆኖ አገኘሁት ።

የሻለቃ ማርቲን ሞትና ሁኔታ በአባሎቹ መካከል የተሰማም እንደሆነ፤ በቅርብ አካባቢ የሚገኙት የማሪን መኰንኖች በቅርብ አያውቁትምና ይደነጋገሩ ይሆናል፤ ያወቁት እንደሆነ ደግሞ ስም ተመልክ ሆኖ የአጻጻፍ ስሕተት መደረጉ ይሰማቸውና ለማንና ወዴት የኀዘን መግለጫቸውን ለመስደድ እንደሚኖሩባቸው ይደነጋገራሉ የሚል እምነት አሳደርን ።

ምናልባትም ደግሞ በዚህ አኳኋን ነገሩ ላይፈጸም ይችላል፤ (እንደ ማውቃቸው የማሪን አባሎች ሁሉ እርስ በእርሳቸው እንደ ወንድማማቾች ናቸው)፤ ስለዚህ ሌላ ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን ። ለሬሳው ያወጣሁለት ስም ምን ጊዜም ቢሆን አደገኛነት የሚያስከትል ነበር ። ስለዚህ አንድ የክርስቲያንነት መታወቂያ ስም አሰብኩና "ዊሊያም" ብዬ ጨመርኩለት፤ ስለዚህ የሬሳችን ስም "የሻምበል (ጥብቅ ሻለቃ) ዊሊያም ማርቲን ክሮያል ማሪን" ተብሎ ተሰየመ ። የክፍሉ አዛዥ ጀኔራልም ሐሳቤነቱን ተቀብለው ለመጨረሻ ጊዜ ደግሞ ምናልባት ነገሩ ጥያቄ ያስከተለ እንደሆነ ብዬ የአድራሻውን ክፍል ሲ. ጅ. አር. ኤም ብዬ ሰጠሁት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

፫ ከዚያ በኋላ ደግሞ የመታወቂያ ወረቀቱን የግል ማስታወሻ መያዣውን እና የመሳሰሉትን አዘጋጀሁለት ። በዚሁ ጊዜ አሁንም ሌላ ሐሳብ መጣብኝ ። ያዘጋጀሁለት የመታወቂያ ወረቀት የተፋቀና የተሻሸ ስለሆነ፤ የፊተኛው የመታወቂያ ወረቀቱ ጠፍቶበት፤ አዲስ እንደ ተሰጠው ለማስመሰል ፈለግሁ ። ስለዚህ አዲስ መታወቂያ አዘጋጀሁና ስሙን ጽፌ በባለሥልጣን አስፈርሜ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ. ም እንደ ተሰጠው አስመሰልኩለት ። በወረቀቱም ላይ የጥንቱ የጠፋው መታወቂያው ቍጥሩ 09650 እንደ ነበረ ጻፍኩት ። አዲሱን ቍጥር ግን የኔ የራሴ መታወቂያ የነበረውን አደረግሁት ። ምክንያቱም ነገሩ ጥያቄና ውዝግብ ያስነሳ እንደሆነ ለመከታተልና ለመከላከል እንዲረዳኝ ብዬ ነው ። ሁሉንም ጥንቃቄ ካደረግሁና ካዘጋጀሁ በኋላ የመታወቂያ ወረቀቱ ጣጣ አለቀለት ።

የትውልድ አገሩንም በደቡብ ምሥራቅ ዌልስ የምትገኘው ካርዲፍ የተባለችው የባሕር ወደብ ነው ብዬ በመታወቂያው ላይ ሞላሁት ።

የሻለቃ ማርቲን ማንነት ተጠናቀቀ፤ ሬሳውን ያገኘው ሁሉ ማንነቱን ከፈቃድ ወረቀቱ ላይ ሊያውቅ ይችላል፤ ግን በሂውልባ በማድሪድና በበርሊን የሚገኙት ወዳጆቼ ጀርመኖች ሻለቃ ማርቲን ስለምን ወደ ሰሜን አፍሪቃ ለመሄድ እንዳሰበ መጠያየቃቸው የማይቀር መሆኑን ተረዳሁት ።

t.me/OLDBOOKSPDF 

ለዚህ ጥያቄያቸው መልሱን ከራሳው ጋር እንዲያ ገኙት ያደረግሁ እንደሆነ ፣ በእርግጥ በመሠረታዊው ደብ ዳቤያችን ላይ እምነት ሊያሳድሩበት ይችላሉ ብዬ ተማ መንኩ ።

አንድ የሮያል ማሪን መኰንን ስለምን ወደ ሰሜን አፍሪቃ ይሄዳል ? ለምን እንደሆነ ዋናው አዛዥ አንድ ደብዳቤ ቢሰጡትስ ? ለምንስ ምክንያት ያገለግላል ? እነ ዚህ ጥያቄዎች እኔኑ አስጨነቁኝ መልስ የሚያስፈልጋ ቸው ጥያቄዎች ነበሩ ።

ጠረፎችን ለመከላከል የባሕር ኃይል እግረኛ ተዋጊ ኃይል ይፈለጋል ፤ ይህ ሲሆን ደግሞ የመጓጓዣ ቀላል መርከብ ያስፈልጋል ፤ በተጨማሪም ጠሩን የሚያሠለጥን የሚረዳ ባለሙያ አካባቢውን መጐብኘቱ የታወቀ ይሆ ናል ፤ በዚህ አስተሳሰብ ስንሄድ ደግሞ ሻለቃ ማርቲን የዚህ ተግባር ባለሙያ ሆኖ ሊገመት ይችላል ፤ ይህንኑ የሚያረጋግጥለትም ሌላ ወረቀት ማስያዝ የተሻለ እንደሚ ሆን ተረዳነው ።

ስለዚህ ሎርድ ሊውስ ማውንትባተን የሚፈርሙበት ወረቀት አዘጋጀሁ ፤ አድራሻውም ለአድሚራል ሰር አንድ ረው ካኒንግሃም ነበር ። እርሳቸውም የሜዲትራኒያ አካ ባቢ ጦር ዋና አዛዥ ነበሩ ፤ ደብዳቤው የሚከተለው ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የመልስ ደብዳቤ ቍጥር 1924/43
የአጠቃላይ እዝ ጠ/ጽሕፈት ቤት
ላ-ሪችምንድ ቴራስ
ኋይት ሆል ኤስ ደብልዩ 1-
ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም.

የተወደዱ የባሕር ኃይል አዛዥ ሰር ኤቢ. ካኒንግሃም-
ሻለቃ ማርቲን ለጀኔራል አሌክሳንደር የሚሰጥ ወረቀት ይዞ ስለመጣ፤ በእርስዎ አማካይነት እንደሚደርሳቸው ለላኪው ክፍል ቃል ገብቻለሁ ። ደብዳቤው በጣም አስቸኳይና የመጨረሻውም ምሥጢር ነው ። ማንም ሰው ሊያነበው ደግሞ አይቻልም፤ በሬዲዮ ምልክትም ሊተላለፍ የማይቻል ነው ።

ይኸው ደብዳቤ ሳይዘገይና ምሥጢርነቱም እንደተጠበቀ ሊተላለፍ እንደሚችል በእርስዎ ላይ እምነቴን ጥያለሁ ።

ማርቲን ደግሞ እርስዎ የሚፈልጉት ዓይነት ሰው ነው፤ ዝምተኛና ከሁሉም ጋር መግባባት የሚችል እንዳደረጉት የሚሆን ነው፤ ዲያፒ በተባለችው የፈረንሳይ የባሕር በር በኩል ስለ ነበረው ችግርና ስለ ተፈጸመው ተግባር ከጥቂቶቻችን የተሻለ ጥናት ያደረገ ሰው ነው ። በእስኮትላንድ ውስጥ በተደረገውም የከባድ መሣሪያ ልምምድ አጥጋቢ ውጤት አስገኝቷል ።

በእናንተ በኩል የሚደረገው ንቅናቄ እንደ ተፈጸመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሻለቃ ማርቲንን እንዲመልሱልኝ በጣም እፈልገዋለሁ።
ሲመለስም ከጣፋጮቹ አሳቦች ይዞ ይመጣ ይሆናል።
እዚህ በታቹው ነውና።

በእውነት አክባሪዎ፣
ሊውስ ማውንትባተን።

ይህ ደብዳቤ በዚያን ጊዜ በሜዲትራኒያ አካባቢ ለነበረው የተባበሩት መንግሥታት የባሕር ኃይል አዛዥ ለነበሩት ለሰር ኤ. ቤ ከኒንግሃም የተጻፈ ነው።
ጠቅላይ ጽ/ቤታቸውም አልጀርስ ነበር። ይህ ደብዳቤ ደግሞ ተጨማሪ ውጤት እንደሚሰጥ በመረዳት ደስተኛ ሆንኩ፣ ሻለቃ ማርቲን ለምን ጉዳይ እንደ ተላከ የያዘውም ደብዳቤ ስለምን በተለመደው አኳኋን እንዳልተላከ በዚህኛው መልእክት ላይ ተገልጿል።

በጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየት ጉዳዩ ግልጽ ሆኖ እንደ ታወቀው ሲስሊን ለመያዝ የምናደርገው ዘመቻ ባይሳካም ወደ ሳርዴኒያ ለማምራት እንደምንችል በዘዴ አጻጻፍ አመልክቻለሁ። ነገሩን ያነሳሁት በቀልድ አስመስዬ ነው። ጀርመኖችም ቀልዱና የዘዴው አጻጻፍ ይገባቸዋል ብዬ ተማምኜባቸዋለሁ። የቀልዱ አጻጻፉ ለዋናው እቅዳችንና የሥራ ክንዋኔያችን ሊያበረክተው የሚችለው ድርሻ ነበረው።

ቢሆንም አንዱ ክፍል ቀልድ እንዲሠረዝ ደግሞ አስፈለገ። ዋናውን መሠረታዊውን ደብዳቤ በርሊን የነበሩት


t.me/OLDBOOKSPDF

የጀርመን ባለሥልጣኖች እንደሚያገኙት እርግጠኛ ነ
ርኩ፤ ሌላው ቢቀር ግልባጩን ያገኙታል፤ ግን ዋናውን
ደብዳቤ የሚደግፈውን ጽሑፍ ለማግኘታቸው ደግሞ
ተጠራጠርኩ፤ ስለዚህ ይህንኑ ደብዳቤ ሙሉውን ሐሳብ
እንዲያገኙት አስፈላጊያችን መሆኑን ተረዳሁት ።

ስለ ሳርዲኒያ የጻፍኩትን ቀልድ በርሊኖች እንዲረ
ዱት መኮንኑም ለምን ጉዳይ እንደ ሄደ የያዘውም ዋና
ው ደብዳቤ ስለምን በእርሱ እጅ እንደ ተላከ ስለ ፈለግሁ
ስለ ዶይፒ የባሕር በር የጠቀስኩትን ሊረዱት ይችላሉ
ብዬ ተማመንኩ ። በዶይፒም በኩል የፈጸምነው ጦርነት
ያልታሳካ መሆኑን እና ለወደፊቱ ግን ተስፋ ያለን መሆ
ኑን የአጠቃላይ እዝ ኀላፊ አምኖበት ደብዳቤ ሲጽፍ
ያንም ጽሑፍ አንድ ጀርመናዊ ሲያገኝ ለአለቆቹ ከማስ
ረዳት አይቈጠብም ብዬ ተማምኜበታለሁ ። በዚህ እቅድ
ቢያምኑ ወይም ባያምኑ በአእምሮአቸው ውስጥ አንድ
እንግዳ ነገር እንዳስቀመጥኩበት ተረድቻለሁ ።

ይህን ደብዳቤና ዋናውን የማታለያ ጽሑፉችንም ከሻ
ለቃ ማርቲን (ሬሳው) ጋር እንዲገኝና የጀርመን የመረጃ
ሠራተኞችም ነገሩን እንዲከታተሉት እንደሚደረግ ተረ
ዳነው ። ሁለተኛው ደብዳቤ በአጠቃላይ እዝ ጽ/ቤታችን
በመኪና ተጻፈ፤ ሎርድ ሊውስም ፈረሙበት ልብ-ወለድ
ቍጥርም ተሰጠው፤ በመዝገብ ቤት ወጪ የሆነ መሰለ ።

ሁሉ ነገር ከተጠነቃቀረልን በኋላም ለሻለቃ ማርቲን



t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ደብዳቤ አስያዝነው ። ቢሆንም ትንሽ መጠራጠር ደርሶብናል ። አንድ መኰንን ሁለት ተመጣጣኝ የሆኑ ፖስታዎች በኪሱ ወይም በግል ቦርሳው ውስጥ ሲይዝ ነገሩ አጠራጣሪነት ይኖረው ይሆን ወይ ? ብለን ተጨንቀን ። በዚህ ሁኔቴ ደብዳቤዎቹ ከሻለቃው ጋር እንዲገኙ ቢደረግም ምናልባት የእስፓይን ሰዎች ሬሳውን ከማስረከባቸው በፊት አያገኙዋቸው ይሆናል ብለን ሰጋን ፤ በሄውልባ የሚኖረውም ቀንደኛውና ቀልጣፋው የጀርመን ሰላይ ወሬ አቀባዮቹን ሬሳውን ሳይፈትሹ በመቅረታቸው ውዝግብ እንዲያስነሳባቸው አልፈለግንም ። ግን ሻለቃ ማርቲን ደብዳቤዎቹን በአንድ ልዩ ከፍ ያለ የእጅ ቦርሳ ይዞ የተገኘ እንደሆነ በጀርመኑ ሰላይና በወሬ አቀባዮቹ መከከል ንትርክ ላይነሳ ይችላል ። ስለዚህ አንድ የደብዳቤዎች መያዣ መካከለኛ ቦርሳ ሬሳው ጋር ማቈራኘት አስፈለገን ።

በዚህ ጊዜ ደግሞ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆነና ሚስተር ሄላሪይ ሳንደርስ ያዘጋጀው መንግሥታዊ ተልእኮ ያዘለው ጽሑፍ ፤ እንግሊዝ አገር ውስጥ ለመታተም ተዘጋጀ ፤ ጽሑፉ ስለ እግረኛ ፈጥኖ ደራሽ ክፍል የሚተርክ ስለ ነበረ ፤ አከታትሎም በአሜሪካ ውስጥ እንዲታተም ሆነ ። የዚያን እትም መቅድም ጀኔራል አይዘንሀወር እንዲጽፉት የሚጠይቅ ደብዳቤ ሎርድ ሊውስ ማውንትባተን የጻፉ እንደሆነ ዋና አጋጣሚና ተቀባይነት የሚኖረው ምክንያት እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚሆን አመንበት ። ስለዚህ የመጠየቂያው ደብዳቤ ረቂቅ ተጻፈ ። የሚታተመው ጽሑፍ የመጀመሪያው የማተሚያ ቤት ለቀማና በውስጡ የሚገቡትም ፎቶግራፎች ተያያዙ። በዚህም ምክንያት ደግሞ ሻለቃ ማርቲን እጅግ ኃላፊነት የተጣለበት መኰንን መሆኑን ለመግለጽ አጋጣሚ አገኘ ንና የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፍን ።

በቍጥር ኤስ አር 198/43 ለተጻፈው
መልስ፤ የአጠቃላይ ዘመቻ ጠ/ጽ/ቤት
ለ-ረችሞንድ ቴራስ
ኋይት ሆል ኤስ ደብልዩ ።

ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፫

ለጀኔራል ዲዋይት አይዘንሀወር
የተባበሩት መንግሥታት ጦር ጠ/ጽ/ቤት
አልጀርስ

የተወደዱ ጀኔራል፤

በኔ እዝ ውስጥ ስላለው ጦር ንቅናቄ የሚያመለክት ሁለት ግልባጭ ጽሑፍ ከዚህ ጋር ልኬልዎታለሁ፤ በውስጡ የሚታተሙም ፎቶግራፎች አጣምሬለዎታለሁ ።

ጽሑፉ የተዘጋጀው ሚስተር ሄላሬይ ሳንደርስ በተባለ እንግሊዛዊ ደራሲ ነው፤ ታሪኩም የኛ ጦር እና የእርስዎ ጦር የፈጸመውን ተጋዳይነት የሚያወሳ ነው ።

ይኸው ጽሑፍ በአሜሪካን አገር እንደገና አንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚሊዮን ተኩል ያህል ኮፒ እንዲታተም ተጠይቋል ። ይህኑም መጽሐፍ የአሜሪካ ባለሥልጣኖች በጦር ሠራ ዊቱ ውስጥ እንዲዳረስ ለማድረግ ማቀዳቸውን ተረድቼዋ ለሁ ። በዚሁ እትም ላይም የእርስዎ መልእክት ቢገኝበት በጣም የሚደሰቱ መሆናቸውን ዋሽንግተን የሚገኘው የእ ንግሊዝ የመረጃ ድርጅት ገልጾልኛል ። ለዚሁም መልእክ ትዎ ከዋሽንግተን ጥያቄ የተላለፈልዎ መሆኑን ሰምቻለሁ ።

የመጽሐፉን የመጀመሪያ እትም ለቀማውን ከዚህ ጋር ልኬልዎታለሁ ። ይህንኑም ይዞት የመጣው የሮያል ማሪን ባልደረባ የሆነው ሻለቃ ዊሊያም ማርቲን የሚባል መኰ ንን ነው ። ይህኑ መልእክትዎን ቢልኩልን እጅግ የምን ደሰትና ታላቅም ክብር ሊሰማን እንደሚችል ልገልጽልዎ እወዳለሁ ፤ እጅግ አስቸኳይና ብርቱ ተግባር ስላለብዎ ፤ ጣልቃ ገብተን በማስቸገራችንም አዝናለሁ ፤ ቢሆንም የእ ርስዎ አስተያየት በዚሁ መጽሐፍ ላይ ቢገለጽ የሁለቱ አገሮቻችን ሕዝቦች ለአንድ ዓላማ የቱን ያህል የተባበሩ መሆናቸውን የሚመሰክር ስለሚሆን ጠቃሚነቱ ከፍ ያለ እንደሚሆን አይጠረጠርም ።

የተሰለፉበት ተግባር እንዲቃናልዎ የዘወትር ምኞታ ችን መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ምክንያት ልገልጽልዎ እወ ዳለሁ ። ሻለቃ ማርቲን እኔ የምተማመንበት መኰንን ስለ ሆነ እርስዎም በሙሉ እምነት ሊያነጋግሩት ይችላሉ ።

በእውነት አክባሪዎ
ሊውስ ማውንትባተን ።

t.me/OLDBOOKSPDF 

ይህን ደብዳቤ ራሳቸው ሎርድ ሊውስ ማውንትባተን ከፈረሙበት በኋላ ከአባሪው ጋር በኢንቨሎፕ ገብቶ ተዘጋ። ስለዚህ እነዚያን ሁሉ የምሥጢር ወረቀቶች ሻለቃ ማርቲንን በእጅ ቦርሳ ለማስያዝ በቂ ምክንያት እንደሚሆነን ተረዳነው።

ቢሆንም የችግራችን መደምደሚያ አልሆነም፤ የእስፔይን ባለሥልጣኖች ሳይሰክላቸው ቀርቶ የምሥጢር ደብዳቤዎቹ ለሌሎች ሊዳረሱ በሚችሉበት መንገድ አቅርበንላቸዋል። ግን ይህን በማድረጋችን ብልጠቱን እጅግ አበዛነው? በአዘጋጀነው የማታለያ ወጥመድ ተደስተን ራሳችንን በምናኰራራበት ጊዜ አንድ ሌላ አጠራጣሪ ሐሳብ ደግሞ ራሳችንን መታው። እንዲያው ለመሆኑስ ሬሳውና ቦርሳው ሂውልባ ለመድረሳቸው እንደምን ልናረጋግጥ እንችላለን?

ምናልባት ቦርሳውን ከሬሳው እጅ ጋር ማቈራኘት ይቻል ይሆናል። በዚህ መሠረታዊ ጉዳይ በኩል ማጥ ውስጥ ለመግባት አንችልም፤ ቦርሳው ከሬሳው እጅ በባሕሩ ንቅናቄ ሊላቀቅ ይችላል፤ ስለዚህ ስለ በድናዊ አካል ጉዳይ ማለት ስለ ጥንካሬውና ስለ መፈራረሱ አጣርቼ ለማወቅ ልዩ ልዩ ጥያቄ አቀረብኩ። ግን ይህን አስቸጋሪ ነገር እንስላስዩ ሬሳው በቅዝቃዜ ምክንያት ሊፈራርስ ይችላል የሚል ጥርጣሬ ባደረብኝ ጊዜ ነገሩ ለብዙዎች ጠበብት በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ተሰማኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላው በኩል ደግሞ ጠቅላላው አቅዳችን የእውነተ ኛነት ምልክት የሌለበት ሆኖ ሳለ ተመልሶ ደግሞ እኛኑ የማያጋልጠን እንዳይሆን መጣጣር ነበር ።

በበኩላችን ያመንበትም አንድ እጅግ ምሥጢራዊና ከፍተኛ ግምት የሚጣልባቸው ደብዳቤዎች በእጅ በርሳ ይዞ በሰንሰለት ታስሮ ላዩ በቆዳ የተሸፈነውን ማንገቻ ከቀበቶው ጋር አስሮ እንደ ባንክ ተላላኪዎች ቢይዝ በቀ ላሉ ሊከሰት ካለመቻሉም ሌላ ከጃቸውም ዘድንገት ሊወ ድቅ እንደማይችል ተረዳነው ።

ይህን የመሰለው ዝግጅት ደግሞ ቀልድ የሚሆን መሰ ለን፤ ከሁሉ በፊት አንድ እንግሊዛዊ መኰንን እንደዚህ የመሰለ ተግባር አይሠራም ። ቢሆንም አጋጣሚያችንን ሞከርነው፤ በርሊን ውስጥ የነበሩት ተቃዋሚዎቻችን የም ናቀርብላቸውን ጉርሻ አኝከው እንዲውጡት መጣጣር የመጨረሻ ውሳኔያችን ሆነ ። ከሁሉ አስቀድሞ እጅግ አስ ፈላጊ የሆነ ጉዳይ ከሌለበት በቀር አንድ እንግሊዛዊ መኰ ንን እንደዚያ ለመሳሰሉት ደብዳቤዎች ያን ያህል ጥንቃቄ እንደማያደርግ ያምኑበት ይሆናል ብለን ተማመንበት ።

ይህን የመሳሰለውን ጉዳይ ካምሰለሰልንበት በኋላ በር ሳው ከሬሳው ጋር ላዩ በቆዳ በተሸፈነ ሰንሰለት እንዲቈ ራኝ ቈርጠን ለመፉ አለቃ ጀዊል በተሰጠው ማብራሪያ ላይ እንደተገለጸውም የሻለቃ ማርቲን ያን ሁሉ ረጅም ጉዞ ቦርሳ በክንዱ አንጠልጥሎ የተጓዘ መምሰል ስለማይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገባው የበርሳውንም አስፈላጊነት ለመግለጽ እንዲረዳ በሰ ንሰለት ከቀበቶው ጋር መታሰሩን ተረዳነው።

በሐሳብ መዋለል ከባድ ነገር ነው። ምናልባት እኛም በብዙው ተጨንቀንበታል፤ እርግጥ ነው ምናልባትም በር ሊን የነበሩት የጀርመን ባለሥልጣኖች ጉዳዩን በከፍተኛ ጥርጣሬ ይመለከቱት ይሆናል፤ ነገሩ ከሆነ በኋላ እኛም ሌላ ትምህርት እናገኝበት ይሆናል፤ ያጋጠመን ዕድል መልካም ነበር፤ የተጠራጠርንበት ጉዳይ ሁሉም ጥያቄ አያስከትልም በቅድሚያ ለማወቅ የጓጓሁት ግን ፈቅደንና አቅደን የምንወስደው ከባድ ነገር የኛ ዓላማ ጉዳዩን እስ ፓንሾቹ እንዲያስተላልፉት ነው፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ ተቃ ዋሚዎቻችን የምናቀርባቸውን ሰነዶች ሳይተማመኑባቸው ቀርተው ከሚደርስባቸው ኃላፊነት ለማምለጥ ሲሉ ብቻ ትክክል ነው ብለው እንዲረዱልንና እንዲተማመኑበትም ማድረግ ነው።

በጉዳዩ ትክክለኞች መሆናችንንና ያለመሆናችንን አላወቅነውም። ምናልባትም እኛም በንሆን ጉዳዩ ልክ ሆኖ ትክክለኛነትን አዝሎ ይገኝልን ይሆናል።

በመጨረሻ እንደ ተረዳነው ደግሞ ሻለቃ ማርቲን በአ ጠቃላይ ጠቅላይ ጦር ሠፈር ውስጥ የሚሠራ ከሆነ ልዩ መታወቂያ ሊኖረው እንደሚገባ ተረዳነው። ስለዚህ አን ድ ብልሀት አዘጋጀንለት። ግን በአንድ በኩል ደግሞ ሻለቃ ማርቲንን ሙሉ በሙሉ በዠለሄ አስመስለን ለማሳየት የም



t.me/OLDBOOKSPDF

ችፈጽመው ሥራ ሁሉ ከአደጋ ላይ የሚጥለን መሆኑን ተረዳን ። ስለዚህ በሰው ልጅ ላይ የሚደርሰው ያለመሳ ካት እንዲታይበትና የይለፍ ፈቃዱንም ጭምር ረስቶት እንደሄደ ለማስመሰል በቃን ። በተቻለ መጠን ስለራሱ ስለግል ጉዳዩና ኑሮው ግዴለሽ መስሎ እንዲታይ ማድረግ አስፈለገን ።

ችሎታ ያለው መኰንንም ቢሆን ፈጽመን ፣ ከውትድ ርና ጠባያት ልናርቀው እንደማይገባ ተገነዘብነው ። ይህ ንም ለማረጋገጥ የሚረዳን በሕይወቱ አንድ ነገር ደርሶ በት የይለፍ ፈቃድ ለማሳደስ እንደረሳ ማስመሰል ነበረ ብን ። ስለዚህ ሁላችንም አልፎ አልፎ እንዳደረግነው ሁሉ የፈቃድ ወረቀቱን ማሳደስ እንደረሳ ለማስመሰል ፈለግን የሰጠነው የይለፍ ፈቃድ ወረቀት ማለቂያው ወይም እን ደገና የመታደሻው ጊዜ እስከ መጋቢት ፴፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ድረስ ብቻ እንዲሆን ወሰን ። ይህም ጉዳይ ጀርመ ኖችን እንደማያስገርማቸው እርግጠኞች ነበርን ፤ (እኛን ግን እንግሊዞችን) ከሁሉ አብልጦ ያስገርመናል ፤ ሻለቃ ማርቲን የይለፍ ፈቃዱን ይዞ ጉዞውን የጀመረው ሚያ ዝያ በገባ በ፫ኛው ወይም በ፬ኛው ሳምንት የሆነ እንደሆነ የይለፍ ፈቃዱ ያለመታደስ በዝንጋታና በችኰላም ሊሳ በብ ስለሚችል ነገሩ ጀርመኖችን ላያጠራጥር እንደሚችል ተረዳነው ። ብቻ የሻለቃ ማርቲን የማዕርግ ልብሱን እንደ ለበሰ የሚያሳይ መሆን አለበት ፤ ከኛ መካከል በተቀራረበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተመሳሳይነት የሽለቃ ማርቲንን መስሎ ለተገኘው ሰው የሚስማማ የጦር ሜዳ ልብስ አገኘንለት ።

ከዚህም ላይ የሮያል ባሕር ኃይል አግረኛ ተዋጊ ክፍል ምልክት ሁሉ ደረደርንለት ። ከወገብ ተለይቶ ከኮቱ ትከሻ ላይ ማዕርጉን አስቀመጥን ፤ ቀጥለን ደግሞ ባት ተሁለት መጫሚያውንና ሸሚዙን እንደዚሁም የውስጥ ልብሱን አዘጋጀን ፤ ሁሉም ልብሶቹ አዲሶች አልነበሩም ፤ በዘመናዊ ልብስ ማጠቢያ ቤት ገብተው የታጠቡት ምልክታቸው ሁሉ ተነሣ ፤ ከዚያ በኋላ ሁሉም ልብሶቹ በአንድነት ወደ ማጠቢያ ቤት ተላኩና ተመሳሳይ ምልክት ተደረገባቸው ።

አንድ ሸሚዝ ጅቢይስ ከተባለው ክበብ ገዛንለትና ደረሰኙም ከኮቱ ኪስ እንዲቀመጥ አደረግን ፤ ይህም ዘዴ እውነትን አስመሰለን ፤ ለማጠንከር ይረዳናል ብለን ነው ። ሸሚዙን የገዛው መኰንን የባሕር ኃይል ባልደረባ ስለ አልነበረ ገንዘብ ከፍሎ ጀቢስ ውስጥ ለመግዛቱ ደግሞ አጠራጣሪ ሆኖብን ፤ በደረሰኙ ላይ ቢል ማርቲን ተብሎ ቢጻፍ እርሱ ደግሞ በዚያ ሥፍራ ሒሳብ ከሌለው ስሙን ካለወጠ በስተቀር በማርቲን ስም ለመግዛት አስቸጋሪ ሆኖ ቀረበ ። የባሕር ኃይል መኰንኖች በጅብቢስ ውስጥ ገንዘብ ከፍለው ዕቃ ገዝተው እንደማያውቁ በመጨረሻው ተረዳሁት ፤ ልናታልላቸው የምንዘጋጀው ጀርመኖችን ነው ። ምናልባት አንዳንድ ለጊዜው ወደዚያ በታ የተዛወሩ መኰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ንኖች እንደ ነባሮቹ መኰንኖች በዚያ መደበር አንዳንድ አስፈላጊ ዕቃዎች ለመግዛት የተፈቀደላቸው መሆኑንና ያለመሆኑን ጀርመኖች ላያውቁ ይችላሉ ። ቢሆንም ይህ ነገር ስሕተትና ጥረት የጐደለው መሆኑን አመንኩበት ። ይሁንና ሬሳው ፍጹም ያልነበረው ሰውዬ አንድ መኰንን ሆነ ፤ የሻለቃ ማርቲንን ሬሳ ያገኘ ሰው ሁሉ ማንነቱን በተገኘበት በታ ለምን ጉዳይ እንደሄደ የሚረዳበትን አስ ረጅ ሁሉ አቀነባብረንለታል ፤ በተጨማሪም የግሉ መሣሪ ያዎችና ዕቃዎች ስለ ሰብአዊ ጠባዩ የሚታወቅባቸው ሌ ሎች ጉዳዮችም አሟልተን እውነተኛ ለማድረግ መጣጣር እንደ ነበረብን ተረዳሁት ።

## ሐሳብ የወለደው ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ ሻለቃ ማርቲን እውነተኛ ሰው መሆኑ ለኛ የተከሠተልንን ያህል ሬሳውን አግኝተው ለሚመረምሩትም ሁሉ እውነተኛ ሰው እንዲመስላቸው ተጣጥረንበታል ። ታላቅ ተስፋ እየመሰለ በተገመተልን ቍጥር ብዙ ጠቀሜታ እናገኝበታለን ፤ ሻለቃ ማርቲንን እኛ እንደካብነውና እንዳስመሰልነው ሁሉ ጀርመኖችም ያለመሆኑን ለማጣራት ጥቃቅኗን ይዘታ ሁሉ እንደሚመ ራመሩ ተረድቼዋለሁ ። ስለዚህ እቅዳችን ሆነ ተብሎ የተ ቀነባበረ ሳይሆን ትክክለኛ መሆኑን ማስረዳት የኛን ጥረት ይጠይቃል ። የነበረኝን የመጠራጠር መንፈስ ደግሞ በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማረጋገጥ በቅቻለሁ ፣ ሌላው ቀርቶ በሻለቃ ማርቲን ኪስ ውስጥ አስገብተነው የነበረውን የትያትር ቤት መግቢያ ቲኬት ወረቀት ሳይቀር አመሳሳይነትን ተማማራት ተቀባ ተቶ እንደ ነበረ ፤ ከጦርነቱ በኋላ ባደረግነው ጥናት ደር ሰንበታል ።

የሻለቃ ማርቲንን ያበጃጀነውና ያሽሞነሞንነው እንደ ጥንት ወዳጃችን አስመስለን ነው ። በዚህ እምነትና አስተሳሰብ ስለሆኑ ፤ የፈጣጠርነው እውነተኛ ወዳጃችን መሆኑ ይሰማን ጀመር ።

ስለዚህ ሊሆን ቢስተካከል የሚችለውን ነገር አሳምረን አቀነባበርነው ፤ ሻለቃ ማርቲን እጅግ ጥበበኛ መኰንንና በአለቆቹም ዘንድ ታማኝ መሆኑን ገልጾንለታል ። የሚገኝበት ስሕተት ቢኖር በጣም ተራ የሆነው የመታወቂያ ወረቀቱን ያለማሳደሱ ነው ።

ይህንኑም የሚያረጋግጥበት ጽሑፍ በኪሱ ውስጥ እንዲገኝ አድርገናል ፤ በዚህ ዓይነት አቀራረቡም ምሉእ በሙሉሄ ያለመሆኑን ጀርመኖች እንዲረዱለት አቀነባብረንለታል ።

አመች ጊዜ አጋጥሞት ደግሞ በአንድ የማታ መደሰቻ ክበብ እንዲገኝ የጥሪ ወረቀት እንዲኖረው ተስማማን በዚሀ ዘዴም ገንዘብ አባካኝ ስለሚሆን ከባንክ ያለበትን ዕዳ ባለመክፈሉ የመጠየቂያ ደብዳቤ እንዲደርሰው ይደረጋል ፤ ለንደንም በቈየባቸው ጊዜያት በልዩ አገልግሎት


t.me/OLDBOOKSPDF

ክበብ ውስጥ እንደ ነበረ ይሆናል፤ ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው የክበቡ የገንዘብ መጠየቂያ በኪሱ ውስጥ ይገኛል ። ይህን የመሳሰለው ጥቃቅን ጉዳይ ሁሉ ተደማምሮና ተቀነባብሮ ከረቂቅ አጠራጣሪነት ወደ ጉልህ ታማኝነት ያደርሰዋል ብለን ተማመንበት ።

ይህን ሁሉ ብናቀነባብርም ቀሉ እንደምን አድርገን ወደ ሕያውነት እናመጣዋለን? የሚለው ጥያቄ ነበር ያስቸገረን ። ቢሆንም ስለ እርሱ ሰብአዊ ጠባይ ልማድና ኑሮ የሚመሰክሩለት ወረቀቶች ከኪሱ ውስጥ ስለ ጨመርን ለት አንባቢዎቹን ሊያሳምንለት እንደሚችል ተረዳነው ።

በሌላው አስተሳሰብ ደግሞ አንድ ሰው ከመንገድ አግኝቶ ኪሱን የሚፈትሸው ቢሆን ስለ ራሱ ምንነትና ጠባይ የሚያስረዳ ጽሑፍ ይዞ የሚገኝ ሰው እጅግ አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝ መሆኑን ሊረዳው ይችላል ።

የነበረብንን ችግር በዚህ ሁኔታ ከመራመርነው በኋላ ወደ አንድ መደምደሚያ ተቃረብን፤ አንድ ሰው ማንነቱን ኑሮውንና ጠባዩን በሚገባ ሌሎች እንዲረዱለት ማድረግ ስለሚያስፈልግ ሻለቃ ማርቲንንም ወደዚሁ መንፈስ ለማቅረብ በቅርብ ጊዜ ለመተጫጨት ከሴት ጋር እንደ ተነጋገረና የፍቅር መለዋወጫ የሆነውን ደብዳቤም ይዞ እንዲገኝ ማድረግ መረጥን ። ስለዚህ ጋብቻው መዘጋጀት አለበት ብለን ከተስማማን በኋላ ወደ ውጭ አገር ከመላኩ ከቅርብ ጊዜ በፊት ከአንዲት ወጣት ጋር እንደ ተዋወቀ አስመሰልነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ መሠረት ሸለቃ ማርቴን በሚያዝያ ወር መጀ
መሪያ ግደማ ፓም ከተባለች የደስ ደስ ካላት ወጣት ጋር
ተገናኘ ፤ ወዲያውም ለመቶሚጨኔት ተስማሙ ። (የጦርነት
ዘመን ፍቅር ችኩላ ነበረበትና ነው) በፍቅር ስሜት ረታ
ችው ዝልፍልፍ ብሎ በእጅዋ ገባላት ፤ የቃል ኪዳን ቀለ
በት አደረገላት ። ስለዚህ እጅግ የሚያስደስቱ ቃላት የሠፈ
ሩበት ደብዳቤዎች ጽፉለት እነዚያን በኪሱ ይዟል ፤ የደ
ብዳቤዎቹም የአጻጻፍ ልዩነት እንዲታወቅ አንዱ በዕረ
ፍት ቀን የጻፉቸው ፤ ሁለተኛው ደግሞ በጽ/ቤቷ ሁና
(አለቃዋ ወጣ ብሎ በነበረበት ሰዓት) የጻፈችለት እንዲ
መስል ሆነ ፤ በደብዳቤዎቹም ላይ በድንገት ወደ ውጭ አገ
ር ለሥራ ታዞ በመሄዱ እንዳዘነችና እንደ ተናደደች መስ
ሎ ተዘጋጀ ፤ የባንኩን ሒሳብ ባለማጠናቀቁም ቀለበቱ
የተገዛበትን ገንዘብ ባለመክፈሉ የመጠየቂያ ጽሑፍ አብሮ
በኪሱ ይቀመጣል ፤ በመጨረሻም በጦርነት ጊዜ ተጣድፎ
የሚደረገውን ጋብቻ የሚቃወም ከጥንታዊ እምነቱ ያል
ተነቃነቀ አባቱ በልጅየው የጋብቻ ችኮላና በቂልነቱም
አዝኖ ከዚህ አስተሳሰቡ እንዲመለስ ይጽፍለታል ።

እንደዚያ አድርገን ኪሱን በወረቀት ሞልተን ስለ እር
ሱነቱ ከመግለጽ በቀር ፤ ሌላ ለማድረግ አልተቻለንም ።
እነዚያም ደብዳቤዎች በሌሎች ሰዎች ተጽፈው የእርሱን
ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነበረባቸው ፤ የባንክ ሒሳብ መጠየ
ቂያ ደብዳቤዎች እንዴት እንደሚጻፉ ገሚሰቻችን እናው


t.me/OLDBOOKSPDF

ቃለን ፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ ብዙ የፍቅር መግለጫ ደብ ዳቤዎች የደረሱን ስለሆነ ፤ ስለዚሁ ጉዳይ ለማብራራት አይቸግረንም ፤ በዚህ አጋጣን በሻለቃው ኪስ የሚገቡት ደብዳቤዎች አንዳንድ ስሕተት እንዳይገኝባቸው በትራ ቀቁ በለሙያዎች ቢጻፉ የበለጠ ውጤት እንደሚሰጡ ተረዳሁ ።

አንዳንዶቹ ጉዳዮች በጣም ቀለል ያሉ ነበሩ ፤ ለምሳሌ አንድ የሥራ ጓደኛችን ወደ አንድ የመደሰቻ ክበብ ተጠ ርቶ ነበር ። በመጥሪያው ወረቀትም ላይ ስም አልተጻፈበ ትም ፤ ስለዚህ በክበብ በኩል የምንፈልገው ነገር በቀላሉ ሊገኝ ተቻለ ፤ የባንክ ሒሳብ መጠየቂያው ደብዳቤ ይል ቅስ በመጠኑ ከበድ ያለ ነበር ፤ በአንድ የሥራ ጓደኛችን አማካይነት ሚያዝያ ፲፬ ቀን ከሊሎይድ ባንክ የተጻፈ ደብዳቤ አገኘን ፤ ደብዳቤው የተጻፈውም የሻለቃ ማርቲን በእላፊ የወሰደውን 79 ፓውንድ እንዲከፍል የሚጠይቅ ነበር ። እንደዚህ በመሳሰለው አነስተኛ ሒሳብ ላይ ሁሉ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ መፈረሙ የተለመደ ጉዳይ መሆ ኑን ለማጣራት ስል ጠየቅሁ ። ያገኘሁት መልስ ግን ይህን የመሳሰለው ደብዳቤ የሚፈረመው በቅርንጫፍ ኃላፊዎች መሆኑን እንጅ ፤ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ እንደማይፈ ረም ነበር ። ስለ ተባለም እንደ ነገሩ ሁኔታ እየተገመተ አነስተኛ ሒሳብም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ እንደሚፈርም ተነገረኝ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የኛው ደብዳቤም የሚጸፈው ለአንድ መኰንን በመሆኑ ነገሩም ሌላ ጉዳይ ያዘለ ስለ ነበር፣ በባንኩ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት እንዲፈረም ቈረጥን። ምንም እንኳን ገንዘቡ አነስተኛም ቢሆን በኛ ሃገር እንደ ተለመደ፤ በጀርመንም የአላፊ የባንክ ሒሳብ የሥራ ልማድ መኖሩን ተጠራጠርኩ። የሻለቃው አባት ጣልቃ ገብነት ግን በጣም አስፈላጊ መሆኑን ተረዳነው። ደብዳቤውን ያዘጋጀልን የሊሎይድስ ባንክ ተ፡ብባሪ ሥራ አስኪያጅ ሚስተር ኋይትሊጅንስ ነበር። በገዛ ጽ/ቤቱ ጽፎ ራሱ ፈርሞ ሰጠን፤ ደብዳቤውም የሚከተለው ነበር።

ሊሎይድስ ባንክ ሊምትድ
ጠቅላይ ጽ/ቤት
ለንደን ኢ. ሲ. 3
ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም.

<u>የግል</u>

ለሻለቃ ዊሊያም ማርቲን አር. ኤም.
የጦርና የባሕር ኃይል ክበብ
ፓል - ማል
ለንደን ኤስ. ደብልዩ 1።

<u>የተከበሩ መኰንን።</u>

ከባንካችን እርስዎ በአላፊ የወሰዱት ሒሳብ 79 ፓውንድ 19 ሽልንግ 2ዲ እስከ ዛሬ አልተከፈለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት ላስታውስዎ የምፈልገው ከላይ የተጠቀሰው ሒሳብና ወለዱ ከመቶ አራት ተጨምሮ ካልተከፈለን ሒሳባችንን ለመጠበቅ የሚረዳንን አስፈላጊ እርምጃ ለመፈጸም የምንገደድ መሆናችንን ልገልጽልዎ እወዳለሁ።

ታማኝዎ

ፌርማ ኢ. ኋይትሊ ጆንስ

ተባባሪ ሥራ አስኪያጅ።

ይህ ደብዳቤ በጦር ሠራዊትና በባሕር ኃይል ክበብ አድራሻ በፖስታ ቤት በኩል ለሻለቃ ማርቲን እንዲላክ ለት ሆነ። ግን የሚላክለት አድራሻ ስሕተት ነበር፤ ፖል ሚል ተብሎ ከፖስታው ላይ ምልክት ተደረገበት በተጨ ማሪም በዚህ አድራሻ ያልተገኘ እንደሆነ ወደ ባሕር ኃይ ልና የጦር ኃይሎች ክበብ 94 ፒካዲሊ ይላክ ተብሎ በተ ጨማሪ ተጻፈበት። ይህም ዘዴ ደብዳቤው እውነተኛ እን ጂ ሆነ ተብሎ ለማስመሰል ያህል ያልተዘጋጀ መሆኑን ያስረዳልናል ብለን ተስፋ አደረግን፤ ስለዚህ በሻለቃ ማር ቲን ኪስ ደብዳቤው ከነ ፖስታው እንዲቀመጥ ሆነ።

ከደርጉ አባሎች አንዳችን ከባሕር ኃይልና ከጦር ሠራዊት ክበብ ጋር ግንኙነት ነበረን፤ ቢዚያው መቀራረ ባችን የተነገ ሚያዝያ ፳፬ ቀን የተጻፈ ደረሰኝ ለማግኘት ችለናል፤ ይህም ዘዴ የረዳን ሻለቃ ማርቲን የዚያው ክበ ብ ጊዜያዊ አባልነት ተሰጥቶት ከሚያዝያ ፲፰ ቀን እስከ



t.me/OLDBOOKSPDF

፳፫ ቀን ድረስ በዚያው መሰንበቱን ለማሳየት ነበር ። በተጨማሪም የሸለቃውን እርሱነት ከማስታወቁም ሌላ እስከ ሚያዝያ ፳፬ ቀን ድረስ ለንደን ውስጥ መሰንበቱን የሚያስተማምንልን ሆነ ።

የቃል ኪዳኑን ቀለበት የገዛበትን ደረሰኝ ለማግኘት ደግሞ በመጠኑ ተቸግረናል ፤ እኔ የኤስ. ጀ. ፊሊፕስን ወኪል በቦንድ ጐዳና የሚገኘውን የዕንቁ ሠራተኛ ለሥራችን ይረዳናል ብዬ መረጥኩት ። ምክንያቱም በመላው ዓለም የተስፋፋ ንግድ ስለ ነበራቸው የሚሰጡን ደረሰኝ በጀርመንም ውስጥ የታወቀ ይሆንና ከመጠርጠር ያወጣልና ብዬ ነበር ፤ ስለዚህ የደረሰኙ ቀን በሚያዝያ ፲፬ ቀን ተጻፈ ፤ ቀለበቱ የተገዛውም ሚያዝያ ፲፭ ቀን መሆኑን ያስረዳል ።

እነዚህን የመሳሰሉትን ደረሰኞች ለማግኘት ችግር ነበረብን ፤ እንደ እውነቱ ደግሞ ደረሰኞቹን ለምን ጉዳይ እንደምንፈልጋቸው መናገር አንችልም ነበር ። ያለ ምክንያት ለማግኘት ፈለግን ሊመስል በሚችል አነጋገር እያዕረዳን ለመሰብሰብ ጥረት ቀጠልን ። እንግዲህ የኔ መሸፋፈኛ ታሪክ ራሱ የመኰንንነት አቋም ያለውና በብዙው አጠራጣሪ የሆነ ሰው መፍጠር ነበር ። ለዚሁም ማረጋገጫ ጥቂቶች ሰነዶች ፈለግን ፤ ያ መኰንንም የገንዘብ እጥረት የነበረበት እንዲመስል አሰብን ፤ የመኰንኑን ኑሮ የግል ጉዳይ ማንም ተመልክቶ የሚገምተው እንዲመስል ማድረግ ያሻናል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠባዩን ደግሞ ማሳወቅ ነበረብን፤ በዚህ አኳኋን ስን መለከተው አጥጋቢ ታሪክ እንደሚሆንልን ተማመንበት። ለዚህ ሥራችን ተባባሪዎች አግኝተናል። ማንኛቸውም ደግሞ ምሥጢራችንን አላሾለኩብንም፤ ከጽሑፎቹ መካ ከልም ስለ ሰውዬው (ሻለቃው) የግል ጉዳይ የተጻፈና ዋናውን እቅድ የሚያጠነክርልን የደብዳቤዎች ኮከብ የሆነ ጽሑፍ ማግኘት ነበረብን።

ከሁሉ አስቀድሞ የሻለቃ ማርቲንን ፍቅረኛ የፖምን እንደ ነገሩ የሆነ ፎቶግራፍ ማግኘት አስፈለገ፤ ለዚህም ፍለጋ ይረዳናል ብለን ያቀድነው ዘዴ አንድ በምሥጢ ራዊ ተግባር የተጠረጠረ ሰው ከብዙ ፎቶግራፎች መካ ከል የሚያውቀውን እንዲመርጥ ለማቅረብ መሆኑን ገል ጸን በመሥሪያ ቤታችን ውስጥ የነበሩት ወይዛዝርት እን ደ ነገሩ የሆነ ፎቶግራፍ እንዲነሱልን ስለ ጠየቅናቸው በቂ የሆነ ፎቶግራፍ አጠራቀምን። ከዚያም ፎቶግራፎች መካከል የደስ ደስ የነበራትን መረጥንና የቀሩትን መለስና ቸው፤ የመረጥነውን ፎቶግራፍ የሰጠችን ሴት በጦር ሚኒ ስቴሩ ጽ/ቤት የምትሠራና ብርቱ ምሥጢር የሚባሉትን ጽሑፎች የምታቀነባብር ስለ ነበረች ፎቶግራፏን አንድ ሰው ለቀልድ ያህል ፍቅረኛው አስመስለን ለማታለል እንድንጠቀምበት ጠይቀናት ተስማማችልን።

ከዚህ ሌላ ደግሞ የፍቅር ወረቀት ለመጻፍ አንዳች ንም የማይሳካልን ሆነ። እኛ ብንጽፈው ሴቶች የሚገልጹ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትን ያህል የወንድ ስሜት ላይቀሰቅስ ይችላል ። ስለዚህ አንዷ ወይዘሪት እንድትጽፍልን ለመጠየቅ ደግሞ በመ ጠኑ አስቸጋሪ ሆኑ ነን ። ቢሆንም የማይቀር ጉዳይ ነበረና በጽ/ቤታችን የነበረች ወጣት ጓደኛዋን ልታጽፋት ትችል እንደሆነ ጠየቅናት ። እነዚያን ደብዳቤዎች የምትጽፈውንም ስም ለማወቅ እንደማንፈልግ አረጋገጥንላት ፤ ከደብዳቤ ዎቹ አንዱ በኔ ወንድም ሚስት የማስታወሻ ወረቀት ላይ እንዲጻፍ ወደድኩ ። ምክንያቱም ጀርመኖች ያን ያህል ጠልቀው ተመራምረው እያንዳንዷን እንግሊዛዊት ለማ ወቅ እንደማይችሉ ስለ ተማመንኩ ነበር ። ለምሳሌም ያህ ል የሚቀጥለውን ደብዳቤ የጻፈችውን ልጅ አድራሻ ለማ ወቅ ለጀርመኖች ታላቅ የራስ ምታት ይሆንባቸዋል ።

የማኖር ቤት
አግቦረን ቅዱስ ጊዮርጊስ
ማርበሮፍ ዊልትሻር
ስልክ 242
እሑድ ፲፰ ቀን ።

እንዳንተ የመሳሰሉ ሰዎች በባቡር ተሣፍረው ሲሄዱ ማየትን ያልታሰበ ጅምላስቲክ እንደሚሰጥ ስለማውቅ በጣ ም አወደዋለሁ ፤ ባቡር ሲሄድ መንገደኞችን ለመሰናበት አንዳንድ ሰው የሚያሳየው ስሜት እንደ ዕብድ የሚያስገ ምተው ነው ፤ ይህንም ሁሉ የሚያስታውሰኝ ከአምስት ሳምንታት በፊት የነበረን አስደሳች ጊዜ ነው ። ያ በአንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነት ሆነን ያሳለፍነው ወርቃማ ጊዜ እፎይ እንዴት ይናፍ ቃል! ጊዜ ለደቂቃ ዕድሜ ከሩጫው ቀጥ ብሎ ቢቆም የሚባለው አነጋገር የስሜት ፍላጎትን ፈጽሞ ስለማያረካ ቁም ነገርነቱ አይታየኝም ።

ደብዳቤህ በመጠኑ አርክቶኛል ተጫጭኖኝ ከነበረው ሰመመን አንቅቶኛል። ግን ስለኔ ነገር እንደዚያ ብለህ ብጻ ፍከው ጉዳይ የምትቀጥልበት እንደሆን! እጅግ አድርጌ ከሁሉ ነገር አብልጬ የምመለከተው ጉዳይ ነው። ቀ[illegible] በት ንገራቸው፤ እነርሱ ግን አይወዱኝም፤ ምክንያቱንም ትደርስበታለህ ይህን ማስታወሻ የጻፍኩልህ ለሳምንቱ መጨረሻ ዕረፍት መጥቼ ከቤተ ሰቦቼ ጋር ሆኜ ነው። ለሰ ኞም ወደዚያው ከባድ ሥራዬ እመለሳለሁ፤ እንደምን ያለ የሚቀፍ ቀን ነው! የምናፍቅህ ቢል ማርቲን! እባክህን ስለ ወደፊቱ ጉዳያችን ሐሳብህን ደግሞ ግለጽልኝ? በተ ጨማሪም በአሁኑ ጊዜ ማንንም ከባሕር ማዶ እያሻገሩ እንደሚሰዱት ሁሉ አንተንም እንዳይልኩህ ብተቻልህ ታገልበት፤ ይህን አድራጎታቸውን እንቃወማለን፤ እኔም ልታገሠው የማይቻለኝ ነገር ነው።

ፍቅርህ

ፓም ።

ከዚህ ደብዳቤ ሌላ ደግሞ ሁለት [illegible] ተጻፈ ለት። ሁለተኛው የተጻፈበትም ቀን ሮብ በ[illegible] ሆኖ፤ ምክን ያት የነበረው ደብዳቤም ነበረ። ግን መጨረሻው የተድበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰበሰ እንዲሆን አደረግነው ፤ ምክንያቱም አሰቃዋ ሲደር ሰባት ቸኩላ ከጽሕፈት መኪናው ያወጣችው መሆኑን ለማስረዳት ነበር ።

በጽሕፈት ቤቴ
ሮብ ፳፩ ቀን ።

፱ ስሎግ አሰቃዩ ለግማሽ ሰዓት ያህል ወጣ ስላለ ፤ አንዳንድ ቀላል ጉዳዮችን ልጽፍልህ ፈለግሁ ። እንደ ተለ መደው ረፍዶብኝ ወደ ሥራ ለመሮጥ በምጣደፍበት ሰዓ ት ጥዋት ደብዳቤህ ደረሰኝ ፤ አጻጻፍህ መርዶ ሆኖብኛል ። ለመሆኑ ወደ የት አገር ነው እሄዳለሁ ብለህ ከሐሳብ ላይ የጣልከኝ ? እስከዛሬ ድረስ የነገርከኝን ሁሉ ለማንም ተን ፍሼ አላውቅም ። ለመሆኑ ወደ ውጭ አገር አይደለም የምትሄደው ? ግዴለህም ጻፍልኝ ለማንም አልናገርም ።

ስማኝ ፍቅሬ እንደምን ያለው አጋጣሚ ዕድል ነው ? በዚህ በጦርነት ጊዜ ያገናኘን አሰቃቂው የጦርነት ጊዜ ባይሆንብን ኑሮ በአሁኑ ጊዜ እንጋባ ነበር ፤ የፍቅርን ወ ለላ የምንመገብበት ጊዜ ይሆንልን ነበር ። እኔም በመንግ ሥት መሥሪያ ቤት ቁጭ ብዬ ፍሬ ቢስ የሆነውን ነገር ሁሉ ሳመሳቅል ባልዋልኩ ነበር ። አዎ የጋብቻችንን ቀን እጅግ ብናፍቀውም የጦርነቱን ጊዜ ለአንዲት ሴኮንድ ላሳ ጥረው አልችልም ።

የምናፍቅህ ቢል ? ማርቲን የገዛህልኝ ቀለበት የቱን ያህል ያስደሰተኝና የማረከኝ መሰለህ ? ዓይኔ ከቀለበቴ ላይ ተነቅሎ አያውቅም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዛሬ ማታ ከነጀከና ሄዜል ቤት ግብዣና የዳንስ ጨዋ ታ ስላለ እሄዳለሁ ። የሚመጣ እንግዳም ሳይኖርባቸው አይቀርም ። በእነርሱ ቤት ምን ዓይነት ጣፋጭና አስደ ሳች ነገር እንዳለ ታውቃለህ ። ግን ለኔ አያዝናናኝም አል ደሰትበትም ። ምክንያቱን ታውቀው የለም ?

ስማኝ ናፍቆቴ የሚመጣው እሁድና ሰኞ ለፋሲካ በዓ ል ዕረፍት እናገኛለን ፤ ወደ ቤተ ሰቦቼም እሄዳለሁና የተ ቻለህ እንደሆነ ብትመጣ በጣም በተደሰትኩ ወይም ደግ ሞ የተቻለህ እንደሆነ ከለንደን ውጭ ለመሄድ ብትችል በፍጥነት እመጣና አብረን በዓሉን እናሳልፈዋለን (በዚህ አጋጣሚም ጊዜ አክስቴ ማርያ ራት ጋብዛኛለች ። ደግ ነው ትዝ ያለኝ ፤ ግን የሚቻል ይሆናል ? ስማኝ ያ አል ቃዱ ያ ሰለግ ውሻ ሲመጣ ከቲውን ሰማሁት ፤ ብዙ ልጅ ፍል!! ነበር በስሜቴ ስሜሃለሁ ።

ክፍቅርህ

ፓም ።

ሽፍንፍኖቻችንን እንደዚህ እያደረግን ካበቃነው ፤ ይህም ደብዳቤ ለሐሰባችን ተስማሚ እንደሚሆን ቆረጥነው ። የሻለቃው አባት አስመስሉን ደግሞ አንድ ሐሰተኛ የሆነ የጦር ሚዳዎችን የጕበኘ መኰንን መረጥን ፤ ስለዚህ ሜጀር ቂያ ደግሞ ሚያዝያ ፲፫ ቀን የተጻፈ ደብዳቤ ከነአባሪው ለሻለቃው የደረሰው እንደሆነ ጣፋጭ መኝዝ እንደሰጣለን ተረዳነው ፤ እነዚያ ሆሬተኞቹ የኢድዋርድ ቤት ሰዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚሰነዝሩትን አስተያየት የጥንት መምህራን ካልሆኑ በ
ቀር ሌላ ሊጽፈው የማይቻል ሆነብን፤ በዚያው ልማድ
የጻፍነውም ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ነበር ።

ጥቁር አንበሳ ሆቴል ሞልድ
የስልክ ቊጥር 98
ሰሜን ዊልስ
ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.
የምናፍቅህ ዊሊያም ።

በአሁኑ ጊዜ ይህ ሆቴል ከጦርነቱ በፊት እንደ ነበር
ኩበት ሆኖ ምቹነቱ አይሰማኝም ። ቢሆንም በዚህ ለመሰ
ንበት የመረጥኩት አክስትህ ቁጠባ እንዲደረግ ስለ አስገ
ደደችኝና እኔም በዛሬው በጦርነት ሰዓት ነገሩ ተገቢ መሆ
ኑን ስላመንኩበት ራሴን በራሴ ለመግታት ስል ነው ።
ቤቱ ግን በኔ ዕድሜ ለደረሰ ሰው እጅግ አስቸጋሪ ነው ።

በሚያዝያ ፳ እና ፳፩ ቀን እዚሁ በከተማው ውዬ
ለማደር አስቤያለሁ፤ በነዚሁ ሁለት ቀናትም ውስጥ ካንተ
ጋር ተገናኝተን እንደምንጨዋወት አልጠራጠርም ።

ስለ አንተው ጉዳይ ለሚስተር ግዋት ኪን ኪና የጻፍ
ኩትን ደብዳቤ ግልባጭ እንድትመለከተው ከዚህ ጋር
ልኬልሃለሁ፤ በደብዳቤው ላይ መረዳት እንደምትችለው
ካርልቶን ጅረል (እስከ ዛሬም ክፍት ይሆናል ብዬ እተማ
መናለሁ) በተባለው ሆቴል ተገናኝተን ምሳ እንዲደረግ
ለት ጠይቄዋለሁ፤ ቀኑም ሚያዝያ ፳፩ ሮብ ለሰባት ሰዓት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሩብ ጉዳይ ይሆናል ፤ አንተም በዚሁ በምሳ ሰዓት ከኛ ጋር ለመገናኘት ብትችል በጣም በተደሰትኩ ፤ ለምሳ እንደማንጠብቅህ እወቅ ፤ ለመምጣት ከቻልክ የምሳውን ሰዓት ማክበር አለብህ ።

የእኅትህ ልጅ ፕሪስስላ አድጋለች ፤ አንተንም ታስታውስሃለች ፤ ጠባይዋ ሁሉ ወታደራዊ ሥርዓት ያለው ስለ ሆነ ከአባቷ ቀጥላ የቤቱ ሰቡ አዛዥ እርሷው ሳትሆን አትቀርም ብዬ እገምታለሁ ።

ናፋቂ አባትህ
የስልክ ቊጥር 98
ጥቁር አንበሳ ሆቴል
ሆልድ
ሰሜናዊ ዌልስ ።
ሚያዝያ ፲ ቀን

ለኤፍ ኤ. ኤስ. ግዋትኪን እ.ስኪዮ
ማክብና እና ኩፓንያው
ዋተርሎ ቊጥር 14
ለንደን ኤስ ደብልዩ
የማክብርህ ግዊትኪን ።

በዊሊያም የጋብቻ ሥርዓት ላይ ሊፈጸም ስለሚገባው ጉዳይ የጻፍክልኝ ደብዳቤ ደርሶኛል ፤ በደብዳቤው ላይ ያሠፈርካቸውን ነጥቦች ካንዱ ጉዳይ በቀር እስማማባቸዋለሁ ። ለጋብቻቸው የሚስቲቱ ቤተሰቦች ምንም ዓይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነት ድጋፍ (የጕጆ መውጫ) ማድረጋቸውን አልስማማ በትም ። እንዲሁ ያስቀምጡት አይበለውና ዊሊያም ቢ ሞት (ጊዜው የጦርነት ስለ ነበረ) ለቤተ ሰቡ የኔ ርዳታ ይበቃል ፥ ይህንም ማድረግ የምችለው ልጆች የተወለዱ እንደሆነ ነው ።

ስለዚህ የልጆቹ ዕድሜ ለዐቅመ አዳም ከደረሱ ድረ ስና እናቲቱም ሌላ ለማግባት እስከ ቻለች ድረስ እኔ የም ችላቸው መሆኑን ገልፀህ የውሉን ደብዳቤ እንደገና ማር ቀቅ ይገባሃል ፤ እናቲቱ ካገባች በኋላ ግን ባለጥቅሞቹ ልጆቹ ብቻ ይሆናሉ ።

ሚያዝያ ፳ እና ፳፩ ቀናት ለንደን ለመዋልና ለማደር አስቤያለሁ ። ስለዚህ ሚያዝያ ፳፩ ቀን ሮብ ለሰባት ሰዓት ሩብ ጉዳይ በከርልቶን ጅረል ሆቴል ተገናኝተን ምሳም በአንድነት ብንሳተፍ በጣም እደሰት ነበር ። ከላይ በጠቀ ስኩልህም መሠረት ውሉን እንደገና ጽፈህ ይዘኸው ብት መጣ እንነጋገርበታለን ፥ ዊሊያምም በዚሁ ቀን እንዲመ ጣና እንድንገናኝ ጽፌለታለሁ ።

ያንተው

ፌርማ ጂ. ጂ. ማርቲን ።

የጥቁር አንበሳን ሆቴል የመረጥንበት ምክንያት ለነ ገሩ የእውነት ማጥበቂያ ይሆናል ብለን ብቻ ሳይሆን ከር ዲፍ በተባለው ከተማ የሚገኝ በመሆኑ የሻለቃ ማርቲን የትውልድ መንደር ስላደረግነው ጭምር ነበር ።


t.me/OLDBOOKSPDF

በሆቴሉ የማስታወሻ ወረቀት ላይ በመጻፋችንና በተለይም ሆቴሉ በምቹነቱ የታወቀ ሆኖ ሳለ በመንቀፋችን ባለቤቶቹ ይቅርታ እንደሚያደርጉልን ተስፋ አለን ።

የሚቀጥለውን ደብዳቤ ደግሞ አስመስሎ የሚጽፍልኝ ወዳጅ አገኘቻለሁ የተጻፈውም በማክከናና ካምፓኒ የማስታወሻ ወረቀት ላይ ነበር ።

ማክከናና ካምፓኒው
ጠበቆች ዋቲርሎ መን. ቍ. 14
ለንደን ኤስ ደብልዩ 1.-
ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ-ም ።

ለሻለቃ ዊሊያም ማርቲን
የጦርና የባሕር ኃይል ክበብ
ፒካዲሊ 94.-
ለንደን ደብልዩ 1.-
የተከበሩ ወዳጅ ።

<u>የግልዎ ፤</u>

የላከንልዎን ረቂቅ ጽሑፍ ተመልክተው የውል ትስማሚነትዎን ገልፀው በትላንትናው ዕለት ስለ ጻፉልን እና መሰግንዎታለን ። ከእርስዎ ጋር ለሚሠራው ወታደርም ፮ ፓውንድ ከፍለነዋል ። የኩፓንያችን የሕግ ክፍል ተጠሪ ሚስተር ጊዋትኩን በ፳፩ ወደዚያው ለምሳው ግብዣ ሲመጡ ዋናውን ደብዳቤ ይዘው እንዲመጡ ስለ ምናደርግ በዚያው ሰዓት እርስዎ ይፈርሙበታል ። የአገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ የገቢዎች ተቈጣጣሪ ክፍል ከ፲፱፻፵፩ እስከ ፵፪
ዓ-ም ድረስ ላበረከትንለዎ አገልግሎት ግብሩን ጠይቆናል ።
ይህም ለእርስዎ የሚከፈለውን ሒሳብ ያዘገይብዎታል ።
ስለዚህ በጉዳዩ እንዲያስቡበትና ሁኔታውንም እንዲያስታ
ውቁን እንጠባበቃለን ።

ከአክብሮት ጋር
የማክ-ኪና ኩባንያ ።

እነዚህን ደብዳቤዎች ሁሉ እንደገና ስናነባቸው እው
ነተኛነትን እንደሚሰጡ ተረዳን ። የሰውዬውን እውነተኛ
ነት አረጋገጡልን። አንድ ሰው በኪሱ ዘወትር ሊይዛቸው
የሚገባቸውና የሚያስችሉም ደብዳቤዎች ነበሩ ።

ይሁንና ደብዳቤዎቹን ሁሉ ከሻለቃ ማርቲን ኪስ ከመ
ጨመራችን በፊት ሌላ ጥንቃቄ መውሰድ ነበረብን ። ፍቅረ
ኛው ከላከችለት ሌላ የአዘጋጀናቸው ደብዳቤዎች ትክክ
ለኛውን ቀንና ጉዳይ የሚያስረዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ
ነበር ። የፍቅረኛው ወረቀቶችም ቢሆኑ እስቾጋሪነት ነበረ
ባቸው በተለይም በስስ ወረቀት የተጻፈው አስቾጋሪነት
ነበረበት ።

እርግጥ ነው ደብዳቤዎቹ ተደጋግመው ይነበባሉ እን
ደ ቀላል ጉዳይም አይገመቱም ይህን እናውቃለን ። አቀራ
ረቡ ደግሞ ጠላቶቻችንን በጥርጣሬ የሚያዋክባቸው አይ
ደለም ፤ (ይህም ማለት አንዳንድ ሰው በቂልነት አስተሳ
ሰብ ተነስቶ የተሻለ አስተያየት ነው እያለ እንደሚዘባር



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀው የመሰሰለ ነበር) አንደኛዋ ወረቀት ጥርጣሬ ካስከተ ለች የሆነውን ያህል ማጋነን ቢጨመርበትም እውነትን ሊደባብቅ አይችልም ። ስለዚህ የሻለቃ ማርቲን ማድረግ የነበረበት ወረቀቶቹን በግደለሽነት መያዝ በመጠኑም በመናደድ መንፈስ ጭብጥብጥ አድርጎ መያዝ ነበረ ። በዚህ ዘዴ እርሱ የሚያደርገውን እኔ ሠራሁለት፤ ወረቀቶ ቹን በጨርቅ በጥንቃቄ ፈጋፈግሁዋቸውና በመጠኑም እጅ ነክ አስመሰልኩዋቸው ።

## ሻለቃው ለጦርነቱ ተዘጋጀ ።

ዝግጅታችንን በጥንቃቄ አቀነባብረናል ፤ የሻለቃው የዘመቻ ዕለት ደግሞ አልተወሰነም ነበር ። ከሰር አርች ባልድ ነይ የተጻፉትን ደብዳቤዎች በጥንቃቄ ካጠናናቸው በኋላ በመሠረተ ሐሳቡ የጦሩ የበላይ ተጠሪ ተስማማበት። ከዚያ በኋላ ዝግጅታችንን ጀርመኖች እንዲቀምሱልን ዘመቻው እንዲጀመር ውትወታችንን ቀጠልን ። ቢሆንም በነገሩ እኛም ብንጓጓበት አጨቃጫቂ ጉዳዮች በባለሥል ጣኖች መካከል አልጠፉም ነበር ።

የጦሩ የበላይ ተጠሪ እቅዳችን ምናልባት ቢለወጥም ለጀርመኖች ወሬ የማቀበላችንን መሥዋዕትነት አልፈቀደ ውም እቅዳችን ቢለወጥ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ አይሆ ንም ነበር ። በሌላ አስተሳሰብ ግን ዘመቻችን ዋጋ የሚሰጥ ከሆነና ይህንኑም ካመንበት በግንቦት ወር መጀመሪያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገደማ ላይ ያዘጋጀነውን ወሬ ለእስፔይን ባለሥልጣኖች ለማቅረብ ወደድን ። ያም ወሬያችን ለጀርመን የመረጃ ሠራተኞች መቅረብ ነበረበት ፤ ወሬውን መሠረት አድርገው የሚያደርጉት ቊጥጥርም ቢኖር ወሬው ትክክለኛ መሆኑን ማስረዳት ነበረብን ። ከተቀበሉንም ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበን ውጤቱ ለጦሩ የዘመቻ ኃላፊዎች መቅረብ ነበረበት ። ነገሩን ካጠኑና ካምሰለሰሉትም በኋላ የጦር ኃይላቸውን ጠላት ወደማይገኝበት አቅጣጫ ያዘምቱታል ። ሲስሊ ላይ እንዲመሽጉ የማንፈቅድ ከሆነም የጀመሩትን ምሽግ መሥራትና ኃይል ማደርጀት እስኪአገባድዱ ድረስ መቆ ገል አልነበረብንም ።

ይህን ሁሉ ጉዳይ የጦሩ የበላይ መኰንኖች ከተገነዘቡ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔያቸውን ሰጡበት ። በሻለቃው ዘማችነት ተስማሙበት ። የእነርሱም ስምምነት በጀኔራል እስማይ አማካይነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀረበላቸው ።

የሚደረገው ዘመቻ በአንድ ምክንያት ስሕተት የተፈጠረበት እንደሆነና ዋናዋ ግባችንም ሲስሊ መሆኑዋ የተሰማብን እንደሆነ ከፍተኛ ችግር የሚደርስብን መሆኑን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲነገራቸው "....ጉዳዩ አሳሳቢና ምክንያታዊ መሆኑ አይታየኝም ። ማንም ቂላ-ቂል ቢሆን ዋናዋ ዒላማችን ሲስሊ መሆኑዋን ያውቃል" ብለዋል ፤ በተጨማሪም ያዘጋጀነው ሬሳ ምናልባት ከጀርመኖች ጋር ተባባሪነት በሌለው ሰው የተገኘና ጀርመኖች ሳይደርሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

በት የቀሩ እንደሆነ ድክማችን ሁሉ የከንቱ ከንቱ እንደ ሚሆንብን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅድሚያ ነገርናቸው ።

ስለዚህም ነገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዒላማው ቢከሸፍም እጅግ ከባድ ጉዳይ እንደማይደርስብን እያሾፉና ጊዜያችንን በከንቱ ማጥፋት እንዳልሆነ እያስረዱን ቡሰጡት መልስ፤ "... ይህም ነገር ቢሆን አሳሳቢ ነው ብዬ አልገምተውም ።

ለአሁኑ የከሸፈብንም እንደሆነ ደግሞ እንደገና እንሞክራለን" ብለው አበረታቱን ። ከዚህ በኋላ ጉዳዩን ጀኔራል አይዘንሃወር እንዲያውቁት ያህል ሲወሰን እኛም በእቅዳችን እንድንቀጥል ሐሳቡ ተፈቀደልን ።

አስቀድሞ ግን ሬሳው ወደ ዘመቻው ከመወሰዱ በፊት ጀኔራል አይዘንሃወር ሌላ እቅድና ሐሳብ እንዳላቸው ወይም ዒላማቸውን ለውጠው እንደሆነ እንዲገልጹልን አስፈለገ ። ከዚያም በኋላ የኛው እቅድ በትእዛዝ ቍጥር ፰ በተገለጸውና ለመቶ አለቃ ጀዊል በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት እንዲሰረዝ የሚደረግ መሆኑ ታመነበት፤ ቢሆንም መልሱ እስከሚደርሰን ድረስ ሬሳውን ለዘመቻው ማዘገጃጀታችን እንደቀጠለ ነበር ።

ያን ከባድ ኃላፊነት ከልባችን ጠልተነዋል፤ የሬሳው መንገላታት አሳዝኖናል፤ እርግጥ ነው ከሃገሬቱ የተወለደ የሃገሬቱ ዜጋ የሆነ ሁለንትናው ለሃገሬቱ ጥቅምና ግልጋሎት መዋል አለበት፤ ቢሆንም ያ-መዋቲ ሥጋ ያን ያህል ጊዜ በቅዝቃዜ መጋደሙ ከብዶናል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያን መዋቲ አካል የሻለቅነት ማዕርግ አልብሰን እንደ ቀዋሚ ሰው ቄጥረነዋል፤ ለኛ እቅድና ለሚጠበቅበትም ውጤት ሕይወታዊ መስሎ ነበር የታየን፤ እንደ አንዳችን የግል ወዳጅ መስሎን ነበር የገመትነው፤ በኪሱ ውስጥ ያስቀመጥናቸውን ወረቀቶች ሁሉ ያቀነባበርናቸው ልክ ከሕፃንነቱ ጀምረን አብረነው እንዳደግንና ጠባዩን እንደ ምናውቅ በሴት ፍላጎት በኩል ያለውን ዝንባሌ የተረዳን እንደዚሁ ደግሞ የገንዘብ ችግር ያለበት መሆኑን የምን መሰክር መስለን ነበር። ያን ሁሉ በማቀነባበራችንም አንድ አባት የልጁን ጠቅላላ ጉዳይ እንደሚያውቅ መስ ለን ስለሆነ የተሳሳትን መስሎ ታየኝ። እንዲያውም ከአንዳ ንዶቹ ወላጆች በልጠን ነበር ያወቅነው የመሰልነው፤ ስለ ዚህ በሕይወቱ ሳለ በደረሱበት አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ስለ ነበረው አስተሳሰብ ደግሞ ማወቅ ነበረብን።

ሬሳው ከተጋደመበት ቀዝቃዛ ክፍል እንደነበረ ነው እንጅ እኛ ተመልሰን ስለ አልተመለከትነው እኔና ጆርጅ ሆነን ቢያንስ ቢያንስ ፫ ጊዜ ያህል መጐብኘት እንደሚ ገባን ተረዳነው፤ በዚህ መሠረት ወደ ቀዝቃዛው ክፍል ገባ ንና የ[illegible]ጀመሪያ ፎቶግራፍ ለማንሳት ስንል አስቸገርነው ቁመቱን [illegible]ትም ነበ[illegible]። በተለይም የባት - ተሁለቱን (ጉንባሴ) ቊጥር ማወ[illegible] [illegible]ረ[illegible]ን። ሁለተኛ ደግሞ እቅዳ ችን በአልታወቀ ድንገተ[illegible] ምክንያት እንዲሰረዝ ያልሆነ እንደሆነ ሻለቃው ጉዘውን እንዲቀጥል ልብሱን ለማልበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስና ለማስነዳዳት ወደ ቀዝቃዛው ክፍል ገባን፣ ስለዚህ ረስተነው የነበረውን ጥቃቅን ነገር ሁሉ አሳከነው።

በቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ የሚኖር ሬሳ እንስቶ አቁሞ ሙሉ የመከ፦ንንነት ትጥቁን ለማልበስ አስቸጋሪ እንደ ሆነም ተረዳነው፤ ልብሱን እንደምንም አለባብሰን ፎቶግ ራፍ ለማንሳትም ተቸገርን፤ቢሆንም ተሳክልን፤ግን ሁሉን ነገር ካጠነቃቀርንና ፎቶግራፍ ከነሳነው በኋላ ደግሞ ባት ተሁለቱን ጫማ ሳናደርግለት መርሳታችንን አወቅን።

ስንታገልበት የነበረውን ነገር ለማድነቅ ከስፈለጋችሁ ቊርጭምጭምታችሁንና ጫማ እግሮቻችሁን ሳታጥፉ ባት ተሁለት ጫማ ለመጫማት እስቲ ሞክሩት፤ ፈጽሞ አስቸ ጋሪ ነገር ሆነብን።

እጅግ አድካሚና የሚያሰለች ጉዳይ ነበር። ሬሳውን ሙቀት እንዲያገኝና የገረረው አካል መታጠፍና መዘር ጋት እንደሚችል እናውቃለን፣ ግን ይህን ብናደርግ እንደ ገና ደግሞ ስናቀዘቅዘው ቢፈራርስስ? ስር በርናርድ ከነገ ረን ጠቅላላ ገለጻ ሁሉ ማፈንገጣችንና ነገሩን ሁሉ ማበለ ሻሻታችን ሆነብን። እታዲያ ምን ማድረግ ይገባን ኑሮዋል?

በጉዳዩ አጥብቀን ስለ አሰብንበት አንድ ዘዴ ተከሠ ተልን፤ በኤሌትሪክ ሙቀት እግሩንና ቅርጭምጭምቱን ብቻ ማሞቅ አስፈለገን፣ ከዚያ በኋላ ጫማውን ሰከተን ልብሱን ማለባበስ ይህ ከተከናወነልን ወዲያ እንደዚያ ያንገላታነውን ሬሳ ጥፋታችንን ከልብ ተረድተን የሕሊና



t.me/OLDBOOKSPDF

ይትርታ ጠይቀን መልሰን ከነበረበቱ ቀዝቃዛ (የበረዶ ቤት)
ወስደን ማጋደም ነበር ።

ለ፫ኛ ጊዜ ሬሳውን የጐበኘነው ደግሞ ሚያዝያ ፲፯
ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ·ም ቅዳሜ ወደ ማታ በ፲፪ ሰዓት ነበር ።
በዚያም ሰዓት የጐበኘነው ሻለቃ ማርቲን ለመጨረሻው
ጊዜው ልናዘገጃጀው ነበር ። በዚያም ጊዜ የግሉ የሆኑትን
ወረቀቶችና አንዳንድ ነገሮች በኪሱ አስገባናቸው ቀጥለን
ደግሞ የተለመዱትን አንዳንድ የማይረቡ ዕቃዎች በየ
ኪሱ ጨማመርናቸው በዚያ ሰዓት ለመጨረሻ ጊዜ በየ
ኪሱ ያስቀመጥናቸው ዕቃዎች አስደናቂዎችም ነበሩ ።
እነርሱም የመታወቂያ መያዣ በርሳ የሻለቃ ዊሊያም ማር
ቲን ክብር የተሠራ ያንገት መስቀል ። የ፳ ሰዓት ፤ የፍቅ
ረኛው ፎቶግራፍ ፤ መጻሕፍት (ሁለት ያረጁ) ፤ ሁለት የፍ
ቅረኛው ደብዳቤዎች ፤ አንድ ጥላክ የከበብ ጥሬ ወረቀት
ወደ መ| ቤት የይለፍ ፈቃድ ፤ የባሕር ኃይሉ መታወቂያ ፤
አንድ ባለ ፭ ፓውንድ ኖት ልዩ ገንዘቦች ፤ የአባቱ ደብ
ዳቤ ፤ አባቱ ለማክከና ኮምፓኒ ነገረ ፈጅ ያጻፈው ከሊሎ
ይድ ባንክ የተጻፉ ደብዳቤዎች ።

ከባሕርና ከጦር ሠራዊት ክበብ የተቀበለው ደረሰኝ ፤
ከጅቢስ ኮምፓኒ የተቀበለው ደረሰኝ ፤ ቀለበቱ የተገዛበት
ደረሰኝ ፤ ፪ የአውቶቡስ ቲኬቶች ፤ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፵፫
ዓ·ም በዊልስ ልዑል ትያትር ቤት የገባበት ቲኬት
ቍራጭ ። ከብሬት ሲጃራዎች የመክፈቻዎች መያዣ እር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳስ፣ ከግክከና ከምፓኒ ነገረ ፈጅ የተጻፈለትን ደብዳቤ እነዚህን ሁሉ በመልክ በመልካቸው እየለየን በየሥፍራቸው አስቀመጥንለት ።

ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ-ም በዊልሶች ልዑል ትያትር ቤት ስለ አገኘነው፤ የመግቢያ ቲኬት ቁራጭ ጉዳይ ላብራራ የምፈልገው ነገር አለኝ። ከላይ እንደተገለፀው ሚያዝያ ፲፯ ቀን ሻለቃ ማርቲን ተዘገጃጅቶ መገኘትና በ፲፱ ጉዞውን መቀጠል ነበረበት። በዚህም መሠረት በሂውልባ ባሕር ዳር ቀበሌ ሚያዝያ ፳፱ ወይም በ፴ኛው ቀን መድረስ ሊኖርበት ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ ጀርመኖች እንዲያምኑን ለማድረግ ከፈለግን ሬሳው ተጓዘ የምንለው በአይሮፕላን ነው። ይህም ጉዞው የአንድ ቀን ጉዞ ይሆናል። እነዚህን የቀናት መለያየት አሰብንና የጊዜውን ጉዳይ ለመለዋወጥ ፈለግን፣ ሬሳው ሚያዝያ ፴ ቀን ገደማ በሂውልባ አካባቢ እንዲገኝ የምንፈልግ ከሆን ለአምስትና ለስድስት ቀናት ያህል ሬሳው በባሕር ሞገድ እየተገፋ ወደ ዳር የወጣ መምሰል ይኖርበታል (ይህም እንደሚሆን የአየሩንና የጊዜውን ሁኔታ አጥንተነው ነበር)። ስለዚህ ሻለቃ ማርቲን ከለንደን ጉዞውን በአይሮፕላን የጀመረው ሚያዝያ ፳፬ ቀናት ገደማ መሆን ይኖርበታል፤ በዚህ ምክንያት ከባሕርና ከጦር ሠራዊት መኰንኖች ከበብ የተገኘው ደረሰኝም ልክ በዚሁ ቀን መጻፍ ይገባዋል። በዚህ ነገር ጆርጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ የአስተዋይነት አስተሳሰቡን አክፊለን ፡ በእርሱ ብሩህ
አእምሮ የፈለቀውን ነገር በሬሳው ኪስ ውስጥ የሚገኘው
የትያትር ቤቱ ቁራጭ ቲኬት ሬሳው ከለንደን ከወጣ
በኋላ የሚገዛበት ምክንያት ሊኖር አይገባም ሲል አሳሰበ
ንና ያን ከባዱን ድካማችንን ከንቱ ሊያስቀረው የነበረ
ውን የትያትር ቤት ቲኬት ቀደን ጣልነው ።
ከዚህ ፈንታ ሻለቃ ማርቲንና ፍቅረኛው የመሸነበበቻ
ቸውን እንዲያደርጉ ወሰን ፤ ሁለቱም ፍቅረኛሞች ከላይ
በተጠቀሰው ትያትር ቤት ውስጥ የሚያስደስታቸውን ትዕ
ይንት እንደተመለከቱ ለማስመሰል አራት ቲኬቶች ገዝንና
በገሚስ ቀደን በሻለቃው ኪስ ጨመርንለት (ቲኬቶቹን
የገዛንበት ምክንያት በኋላ ይገለጻል) እንደገና ደግሞ
በዚያ የማታለል እቅድ ውስጥ ሌላ ዝርዝር ጉዳይ ማጠ
ናቀቅ አስፈለገን ፣ ከሁሉም ይልቅ የከበቡ ደረሰኝም
ቢሆን በእስፓንሾችና በጀርመኖች ዘንድ እጅግም ከፍ
ተኛ ግምት እንደማይጣልበት እናውቃለን ።

በመጨረሻም በቦርሳው ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን
ደብዳቤዎች ጨመርንበትና ጉዳዩን ለመቶ አለቃ ጀዊል
ገለጽኩለት ፣ በኛ አስተሳሰብ ቦርሳው ከሬሳው ተለይቶ
ለመቶ አለቃው እንዲሰጥና ሂውልባ አካባቢ ከደረሱ
በኋላ ሬሳው ወደ ባሕር ሲጣል ቦርሳውንም መልሶ እንዲ
ያያይዘው ብለን ነበር ፤ ግን በዚያ ጥድፊያና ስጋት በሚያር
በተብታቸው ሰዓት ሬሳውን ከባሕሩ ላይ ጥለው ቦርሳውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ረስተውት ቢመለሱስ? በዚህ ፈራንና በርሳው ከሬሳው ጋር ተቈራኝቶ እንዲጓዝ ወሰን ።

በተለይም ደግሞ ጊዜው የባሕር ሞገድ የበዛበት እንደሆነ ለመርከቢቱ አዛዥ ለሙቶ አለቃ ጀዊል አስቸ ጋሪ እንደሚሆንበት ግልጽ ነው ። በዚያ ሰዓት አእምሮው የሚያስበው ስለ መርከቢቱ ጠቅላላ ደህንነት ብቻ ይሆ ናል ፤ ስለዚህ በርሳው ከሙቶ አለቃው ጋር እንዳለ ሻለቃ ማርቲን ብቻውን ያለበርሳው በባሕር ላይ ሲንሳፈፍ ቢገኝ ብርቱ ኀዘን እንደሚሆንብን ተረዳነው ።

በዚህ ምክንያት በርሳና ሬሳ ተቆራኝተው እንዲጓዙ ሆነና ሬሳው በጉዞው ላይ እንዳይጐዳ በጥንቃቄ በብርድ ልብስ ጠቀለልነው ። ሬሳው የነበረበትን ሣጥንም አቆም ንና በጫፍ በኩል በረዶ ጨመርንበት ። ያ በረዶ ሲቀልጥ ደግሞ ሌላ ጨመርንበት ። ከዚያ በኋላ ሻለቃ ማርቲንን በጥንቃቄ መልሰን አጋደምንና የሣጥኑን ዙሪያ በረዶ አስ ታቀፍነው፤በሚገባም ታሸገና ተያዘ። ከዚያ ሁሉ ዝግጅት በኋላ የሻለቃ ማርቲን ለጦርነት ተዘጋጀ ።

## የሰሜኑ ጉዞ ።

እኔ ራሴ ጆርጅ እና የታወቀው የሞተር ተሽቀዳዳሚ ጆከክ ሆርሰፎል (እርሱም በጦር ሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት በልዩ ሥራ ተመድቦ ነበር)፤ሆነን አንድ የተሸፈነ ተሽከርካሪ የዕቃ መጫኛ ተውሰናል፥ በዚያ ተሳቢ ሠረገላም ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘማቹን ሻለቃ ማርቲንን የያዘው ሣጥን ይገኝበት ነበር።

ሬሳውን ከቀዝቃዛው ቤት አውጥተን በተጐታቹ ሠረገላ ጭነን ወደ ጆርጅ ቤት ይዘን እንሄዳለን፤ የእርሱም ቤት ከዚያው ለንደን ውስጥ ነበር። እግረ-መንገዳችንን ከአንዱ ስኒማ ቤት የሰላይ ፊልም ለማየት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ቲኬት ለማስቈረጥ ሲጋፋ ተመለከትን፤ በዚህም ጊዜ አንድ ነገር ትውስ አለን፤ "ይህን ፊልም ለማየት አትቸገሩበት፣ ከዚህ የተሻለ እውነተኛ ታሪክ እንነግራችኋለን፣ ከዚህ ሠረገላ ውስጥ ያለውን ሣጥን ከፈቱና ተመልከቱ" ብለን ብንናገር ያ-ሁሉ ሕዝብ ምን ነገር ይሰማውኑሩዋል? የሚል አስተሳሰብ መጣብን ይህም ነገር እኛኑ ራሳችንን በሳቅ ፈነቀለን።

በመልካም ሁኔታ ምንም ፅንቅፋት ሳያጋጥመን ከጆርጅ ቤት ደረስን ከዚያም ራታችንን ራሳችን ሠርተን ብላን። ቢሆንም ከውጭ የተውነውን ተጐታች ሠረገላ እንመለከከት ነበር፤ አንድ ጭልፊት ሌባ ሣጥኑን ቢወስደውስ? እርግጥ ነው ሲከፍተው ድንጋጤና ተስፋ መቍረጥ ይደርስበታል ግን የእርሱ ተስፋ መቍረጥ ለኛ ምናችንም አይደል። ለኛ የበለጠ አደጋ መሆኑ ተሰማንና ተጐታቹ ሠረገላ ወደ ሰሜን በሚጓዝበት ሰዓት ከርሱ መለየት ስለማይገባን ቀላል ምግብ ብቻ አዘጋጅተን ጐራረስንና ወደ ሠረገላችን ተመለስን።

ዝግጅታችን ሁሉ ስለ ተጠናቀቀ እኔና ጃከክ ሆነን



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ግሪንአክ ጉዞአችንን ቀጠልን። አድካሚና አታካችም ጉዞ ነበር። ከዚያ ሌላ ደግሞ ነገሩ ጥንቃቄና ድብቅብቆሽም የሚያስፈልገው ነበር። ሠረገላው ተሸከርካሪም የሚሳብ ነበርና ቀስታ ያስፈልገዋል በላያችን ላይ አይሮፕላን ሲበር ብርቱ ፍርሃት አሰጠመን።

"ሣራፍ" የተባለችው መርከብ እስከ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ድረስ በወደቡ ስለምትቈይ በቂ ጊዜ ይኖረናል፤ ስለዚህ በበንብ በተደበደበው መንገድ የምናደርገው ጉዞ በማንኛውም ነገር እንደማያዘገየን ተረድተናል፤ የመርከቢቱ አዛዥ ግን ምናልባት አንድ ነገር ቢገኝም ችግር እንዳይደርስ ከሚያዝያ ፲፰ ቀን እኩለ ቀን በፊት እንድንደርስለት ነግሮናል።

ስለዚህ ተጐታቹን ሠረገላ በፍጥነት እንዳልጐተት ነውና በላያችን ላይ ሲያንዣብቡ የነበሩትም አይሮፕላኖች ጠላቶቻችን እንዳልሆኑ ተረድተነዋል፤ በዚህ ምክንያት ጕዞአችንም በጨለማ ስለ ነበረ ሬሳው ከተጫነበቱ ሠረገላም ላይ ሌሊቱን ተኝተን ለማሳለፍ ችለናል። ሚያዝያ ፲፰ ቀን ከንጋቱ ላይ ግሪንአክ ከተባለው ቦታ ደረስንና ወደ ወደቡ አመራን፤ በዚያም ወደብ ላይ ዕቃችንን የምናስረክባት (የሻለቃው መዝሙቻ) የባሕር ውስጥ ለውስጥ መርከብ ቁማ ነበር።

በዚያም ወደብ ዕንቅፋት ነበረብን። ሬሳ የያዘውን ሣጥን ከሠረገላው አውርደን ከመርከቧ ለማስገባት እስቸ


t.me/OLDBOOKSPDF

ጋሪ ጉዳይ እንደሚሆንብን ተረድቼው ስለ ነበረ ለባሕር ኃይሉ የመረጃ ድርጅት ነገሩን በልዩ መልእክት አስተላልፌላት ነበር ። ይኸውም ፀ፻ ኤል ቢ - ዕቃ በልዩ ልዩ ሣጥኖች ተከፋፍሎ እንደሚጫን መስሎዋቸው ነበር ።

በዚህም አስተሳሰብ ጥቅሎቹን ዕቃዎች ለመጫን የም ርከቦቹን መሸጋገሪያ ደረጃና መሰላል ስንመለከት እንደም ንውል ተገምቶ ነበር ። እንዲረዱን የተመደቡት ሰዎችም ሲጠባበቁን የነበረው በዚሁ ገለጻ ነበር ። ስለዚህ ሬሳውን የያዘውን ሣጥን ከሠረገላው አውርደን ከመርከቢ ለማስገባት የሚያስችለው መሣሪያ ስላልተዘጋጀልን ያልጠበቅነው ዕንቅፋት አጋጠመን ። ችግርና መዘግየት ተደራርበው እንደሚመጡብን ተረዳሁና ወደ ወደቡ አዛዥ ፅሕፈት ቤት በሩጫ ሄድኩ ፤ እዎ የዕድሌ በር ፈጽማ አልተዘጋችም ነበር ። ተረኛ መኰንን የነበረው እኔ በኩል በተባለው ሥፍራ ስሠራ በነበረበት ጊዜ በዚያው ውስጥ ሲሠራ የነበረና የማውቀው ስለ ሆነ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ችግሩን ለማቃለል ጥረት ጀመርን ፣ ወዲያውም ሬሳውን የያዘውን ሣጥን ከተሽከርካሪው ሠረገላ አውርደን ወደ ጠላቂዋ መርከብ የምንጭንበትን መሣሪያ አሰናዳን ። ከዚያም በኋላ ወደ ወደቡ ተመለስኩና ሬሳውን ለመቶ አለቃ ጀዊል አስረከብኩት ከሬሳው ጋር አቆራኝቶ የሚያንሳፍፈውንም ልዩ መሣሪያ ሰጠሁት ፤ ሲደክምበት የኖረው ዝግጅት ተጠናቀቀና ሬሳው ለዘመቻ ተሰለፈ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያ-በባሕር ላይ እንዲንሳፈፍ የተፈረደበት ሬሳ የእስቴይን ዓሣ አጥማጆች ጠቃሚያቸው እንደማይሆን እናውቃለን፣ ግን አብሮት የሚገኘው ማንሳፈፊያ መሣሪያ ያለ ጥርጥር አስፈላጊያቸውና ጠቃሚያቸው ስለሆነ፤ ከጊዜ በኋላ ባደረግነው ጥናት የት እንደ ደረሰ እንኳ አላወቅነም ። በመጨረሻ ደግሞ አንድ ቀላልና ፈጣን በራፊ መሣፈያ የሰመጠ ለማስመሰል ከተፈለገ ስብርባሪውም እየተንሳፈፈ መገኘት እንደሚኖርበት ሰዎች አማክረውናል፤እኛ ግን ይዘን ጉድ ደግሞ አስቀድመን ስለ አላሰብንበት ለመቶ አለቃ ጄዊል የሰጠነው የማስመሰያ ስብርባሪ አልነበረም ።

ሬሳውን የያዘው ሣጥን ከጠላቂዋ መርከብ "ሣራፍ" ላይ ከወጣ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ከመ/አ/ጄዊል ጋር ውይይት አደረግን፤ በዚያም ጊዜ ሬሳውን ከመርከቢቱ አውርዶ ከባሕሩ ላይ ሲጥል ከሥራ ጓደኞቹ መኰንኖች አንዱ እንዲረዳው ቢያደርግ መልካም መሆኑን ገለጽኩለት፤ይህንም ያልኩበት ምክንያት ከመርከቡዋ ውስጥ የተመደቡት ሠራተኞች ምንም እንኳ ጥቂቶች ቢሆኑም ቅሉ ከእነርሱም መካከል ቢሆን ሬሳ ወስደን እስፔይን ባሕር ዳር ላይ መጣላችንን እንዲያውቁና የጨዋታ መጀመሪያ የሆነውም የሹክሹክታ ፍንጭ እንዳይፈተልክ ስለ ፈራሁ ነበር ። ሬሳውን በዚህ ዘዴ የጣለው እንደሆነ ለመርከቢቱ ሠራተኞች አንድ የማስመሰያ ወሬ ለመፍጠርና እውንተ

ኛውን ነገር እንደያውቁት መደበቅ እንደሚችል አስረ ዳሁት ።

የመርከቢቱ ሠራተኞች እርግጥ ነው የተጠቀለለውን ዕቃ ያዩታል፤ ግን በእስፔይን ባሕር ዳር በኩል ወደ ሞልታ የሚሄድ ልዩ ዕቃ ነው ብለው አምነዋል ። እንዲያውም ተሰብሮ መስታወታዊ የሆነ መሣሪያ እንደሆነ አስመስሎ ለጭፍሮቹ እንዲነግራቸው አዋየሁት፤ ወደዚያ የሚወስ ደውም የአየሩን ሁኔታ እየተከታተለ እንዲያስተላልፍ የሚጣል መሆኑም እንዲገለጽላቸው አሳሰብኩት፤ መቶ አለቃው ሬሳውን ከመርከብ አውጥቶ ባሕር ላይ በሚጥል በት ጊዜ በማዕበል ወይም በሌላ ምክንያት ችግር ደር ሶበት ረዳት ወታደር ያስፈለገው እንደሆነ በዘመቻው ትእዛዝ በሰጠሁት መመሪያ መሠረት የማስመሰያውን ዘዴ እንዲጠቀምበት ነገርኩት ።

ያዘጋጀነው ጉዳይ ሁሉ ተሳካልን ወደ ለንደንም ስን መለስ የሠራነውን ሁሉ ዘርዝረን ማመልከቻ ማቅረብ ነበረብን፤ በዚያም የሥራ ማመልከቻችን ላይ "ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፵[illegible] ዓ. ም. በ1800 ሰዓት የግርማዊነታቸው ጠላቂ የጦር መርከብ ሣራፍ ከሆሊሎች ወደብ ተነስታ ለች ብለናል ።

መርከቡዋ የያዘችው ዕቃ ምን እንደሆነ ለምን ጉዳ ይም እንደምትሄድ እያሰብን የተቃና ውጤት እንደምታ ስገኝ የመጨረሻው ጸሎቴና ምኞቴ አብሯት ተጓዘ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሬሳው ሥራ ጀመረ።

የሚያጓጓው ሰዓት ደረሰ፤ ዘመቻው የተቃና ውጤት እንዲሰጥ የተማመንበት ነበር፤ ግን የውጊያው ስልት ከጀ ስለወጣ ምናልባት አንድ ዓይነት ድንገተኛ ስሕተት ይፈጠርና ይጨናገፍ ይሆን እያልኩ በሐሳብና በጥርጣሬ ተውጫለሁ። በቀረብንላቸው የማስመሰያ ወጥመድ ጀር መኖች ስለ መግባታቸውና ስለማምለጣቸው ግን ምንም አላስብምና አልጨነቅም ነበር። እንደማያመልጡን እርግ ጠኛ ነበርኩ። ጉጉቴ ግን ስለ ሬሳው እባህር ላይ አጣ ጣልና አወዳደቅም ነበር። ሬሳው ከባሕር ሲጣል በእርግጥ ይንሳፈፍ ይሆን? ወይስ የተቻለውን ያህል ከሞከርን በኋላ ሬሳው ቢሰጥም የኛ ጥፋት አይደለም ብለን እንጥ ናና? ከዚህ ሌላ ደግሞ መንፈሴ የተሸበረው አእምሮዬ የተጨነቀው በኔ እቅድና ውትወታ መሠረት የጦር መር ከቡዋ ወደ ሂውልባ ባሕር መዳረሻ ስትሄድ ያልተጠበቀ ውጥንቅጥ ቢያጋጥማትስ? እያልኩ ነበር።

በዚህ አስተሳሰብ ሰውነቴን ማኮራመቱ አእምሮዬን ማስጨነቁ ከሆነ በኋላ የሚሰጠው ጥቅም እንደሌለ ተረዳ ሁትና በየቀኑ አንዳንድ ተግባር በመፈጸም ሌላም ለሃገር ጠቃሚ የሚሆን እቅድ በማውጣት የሬሳውን ዘመቻ ለመ ርሳት ለመዝናናትና ደስተኛ ለመሆን መጣጣር ጀመርኩ።

በሻለቃ ማርቲን ኪስ ውስጥ አስቀምጠናቸው የነ



t.me/OLDBOOKSPDF

በሩትን የቲኬት ቊራጮች መጣላችን የቂልነት አድራ ጎት እንደሆነብን ተሰምቶኛል ። በማስታወሻ እንደያዝ ኩት አራት ቲኬቶች ገዝተን ነበር ። ለሻለቃ ማርቲንም ሁለት ወንበሮች እንደተሰጠው ለማመልከት ሁለት ቁርጥ ራጮች ከኪሱ አስገብተን ነበር ። የሚያስፈልጉን ከሆነ እኛ ልንጠቀምባቸው ፈለግን ፤ በዚህ መሠረት እኔና ጆርጅ ሆምናጅየል የተባሉ ሁለት ልጃገረዶች ጋበዝን ። እነርሱም የፍቅር መግለጫ ደብዳቤዎቼን የጻፉልን ናቸው። የጋበዝናቸውም "የቢል ማርቲንን የመሰናበቻ ቀን ለማ ዘከር" ብለን ነው ፤ ስንብቱንም ከዊልስ ልዑል ትያትር ቤት ጀምረናል ። የትያትር ቤቱ ተቈጣጣሪ ቲኬቶቻችንን ሲመለከት አንድ ሰው "ለቀልድ ሲል" የቲኬቶቹን ጫፍ ቀዶ እንደጣለብን ስንነግረው እውነት መስሎት ወደ ውስጥ አስገባንና መቀመጫ ሰጠን ። ግን ቀልዱ በጀርመ ኖች ላይ የተፈጸመ መሆኑን አልነገርነውም ። ከትያትር ቤቱ ወጣንና ወደ ጋርጕያል ክበብ እራት ለመመገብ ሄድን ፤ ከዚያም በጥግ በኩል ወደ ነበረ ጠረጴዛ ተወሰ ድን ፤ ከፊት ለፊቱም ሁለት ራት የሚመገቡ ሰዎች ነበሩ ። ሁለቱ ሴቶቻችን በምቹዎቹ ወንበሮች እንዲቀመጡ ሐሳብ አቀረብኩ ። በዚህ ጊዜ ጅየል ወደ ጆርጅ ዘወር አለችና "ቢልና ፓም እንደተጫጩ እናውቃለን እጅግም የማይዋደዱ መሆናቸውን እኔ አውቃለሁ ። ሌላው ቀርቶ እርሱ ወደ ውጭ ሃገር ለመሄድ በሚሰነባብቱበት ቀን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንኪ አብረው ለመቀመጥ አይፈልጉም . . ." አለች ።
እንደዚህ ብላ ስትናገር ከፊት ለፊታችን የነበሩት ወንድና ሴት ዙሪያውን ተመለከከተው ነቃ ነቃ ብሰው ማዳመጥ ጀመሩ፤ እኔም በዚህ ጊዜ ለአርሷ ንግግር በሰጡሁት መልስ "እኔና ፖም ብንተጫጭም ቅሉ በአጭር ጊዜ እንደተዋወቅን ያህል እንጅ (በጦርነት ጊዜ ጋብቻ ተቃ ዋሚ የሚበዛበት መሆኑን ከሚቀጥለው ጠረጴዛ የነበሩት ሰዎች እንዲረዱት በማስመሰል) ሁለታችን የብዙ ጊዜ እውቂያ እንደሌለን ለአለቃዬም እንደተነገረው (ሎርድ ሉይስ ማውንትባተን ለአድሚራል ከኒንግሃም በጻፈው ላይ እንደተገለጸው ራሱዋ አይታዋለች) በመጀመሪያ ዝምተ ኛና አፋራም ግን ማንነቴን የማውቅ ነኝ" አልኳት። በዚህ ጊዜ ከአጠገባችን የነበሩት ተፋቃሪዎች ነገሩን በይበልጥ ናቁትና ተነሥተው ዳንስ ጀመሩ።

እንደ ቢል ማርቲን ሆኜ ወይም ተመስዬ ሳደርገው በነበረው ጉዳይ ሌላ አዲስ ጉድ ደግሞ ተጨመረበት። በቢል ማርቲን የግል ቦርሳ ውስጥ ሆኖ ወደ እስፔይን ሲጓዝ የነበረውን ከፍ ያለ ፎቶግራፍ ፖም ስትሰጠኝ "እስከ ሞት ድረስ አትለያየን አፍቃሪህ ፖም" ብላ ፈረ መችበት በዚያ ጊዜ ከእናቴ ጋር እኖር ነበርና የምትለ ውን ለማወቅ ብዬ ያን ፎቶግራፍ ከመኝታ ክፍሌ ከነበ ረው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩት። ግን ምንም ስለ አልተ ናገረችን ብሽቅ አልኩ። ለመረጃ ሥራ ጉዳይ አሜሪካ



t.me/OLDBOOKSPDF

የነበረችው ሚስቱ ከአንድ ዓመት በኋላ ስትመለስ ፎቶ ግራፉን ሳሳያት "ለካ ለዚህ ነሩዋል ሥራዬን እንዲፈጸ ምኩ በቶሎ ወደ ቤቱ እንድመለስ እናትህ ወረቀት እየ ጻፈች ስትወተውተኝ የነበረችው? አለችና እጅግ አስገ ረመችኝ።

ለንደን ውስጥ ሆነን ስንጠባበቅ "ሣራፍ" የተባለችው ጠላቂ የጦር መርከብ ወደ እስፔይን የባሕር ጠረፍ ተጠ ጋች። አስቀድመን ባዘጋጀነው የመልእክት ምልክት መሠረት ሚያዝያ ፴ ቀን "የማስመሰያው ዘመቻ" ተፈጸ ሟል የሚለው የመጀመሪያው ዜና ተላለፈልን። ወዲያው አከታትሎ ደግሞ የመቶ አለቃ ጆዊል ከጅብራላታር የሚ ከተለውን ደብዳቤ ጻፈልን።

## ብርቱ ምሥጢርና የግል።

ከሳራፍ የጦር መርከብ አዛዥ መኰንን
ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም
ለባሕር ኃይል የመረጃ ክፍል
ግልባጭ ለመረጃ ክፍል ዳይሬክተር
ለሌ. ኮማንደር ሞንታጉ (የግል)
ስለ የማስመሰያው ዘመቻ።

፩ ፦ አየሩ ፤ ከደቡብ ምዕራብና ከደቡብ ምሥራቅ በኩ ል ተለዋዋጭ ነበረ። ግምታችን ግን አስቀድሞ እንደነበ ረው ይሆናል የሚል ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

የባሕሩ ሙላት ጨምሮ ነበር ። በጉምም በመሸፈኑ የማየት ኃይላችን የተወሰነ ሆኖብናል ።

፪ - ብዛት የነበራቸው የዓሣ ማጥመጃ ጀልባዎች በአካባቢው ነበሩ፤ እስከ አንድ ማይል ርቀት ተጠግተናቸዋል፤ ግን የባሕር ውስጥ መርከብ በአካባቢያቸው እንደነበረች አልተመለከቱም ።

፫ - ንቅናቄው የውኃው መጠን ዝቅ የሚልበት ጊዜ በ0430 እንደሚሆን ታውቋል፤ በዚያን ሰዓት የንጋት ውጋጋን ስለሚያይል ጠላቂዋ መርከብ ትከሠታለች ። በ0415 ሰዓት ሣጥኑ ተከፍቶ ሬሳው ወጣ ። ተጠቅልሎበት የነበረው ብርድ ልብስ ተገለጠና ሬሳው ተፈተሸ ። በርሳውም በሚገባ ተያይዞ ነበር ። መንሳፈፊያው መሣሪያ በቂ ሆኖ ስለ ተነፋ ተጨማሪ አየር አያሻውም ነበር ። በ0430 ሬሳው በታለመው ሥፍራ ከባሕሩ ላይ ተጣለ ። ወዲያውም በነፋስ እየተገፋ ወደ ባሕሩ ዳር ጉዞ ቀጠለ ። መንሳፈፊያው ልዩ መሣሪያ ደግሞ ተገልብጦ በግማሽ ማይል ርቀት ከሬሳው እልፍ ብሎ ተጣለ። ሬሳው የነበረበቱ ሣጥንና ሌላም አስፈላጊ ያልነበሩት ዕቃዎች ወደ ባሕሩ እንዲሰጥሙ ተደረገ ። የባሕር ውስጥ ለውስጥ መርከቡዋም ወደ ኋላዋ ተመለሰች፤ ዘመቻው በትእዛዙ መሠረት መፈጸሙን የሚያረጋግጠው ምልክትም በ0715 ሰዓት ተላለፈ ። ስለ ባሕሩ ሁኔታ የሚያስረዳ መግለጫ አብሮ ይገኛል ።

ኤን. ኤ. ጀዊል
የመቶ አዛዥ



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ድብዳቤና በተጨማሪ በተላከውም መግለጫ ላይ እንደተረዳነው የሬሳው መንሣፈፍ ፍጥነት በመጠኑ ተለውጧል ። ቢሆንም ከገመትነውና ከአሰብነው እምብዛም አልተለወጠም" ።

ቈይቶ ግን ከመርከብዋ አባል ከሆነ ሰው ዝርዝር የወሬ ወሬ ሰማሁ ። ይህንም ወሬ የደረስኩበት እንደ ጋዜጠኛ ተመስዬ ነበር ። ሰውዬው ነገሩን በሚገባ ያጠናውና የደረሰበት መሆኑን በአገላለጹ ተረድቻለሁ ። እኔ ግን ለራሴ እንደ ተላለፈልኝ አድርጌ ነበር ያስተላለፍኩት ።

ነገሩም እንዲህ የሚል ነበር ።

"ሣራፍ" የተባለችው ጠላቂ የጦር መርከብ ከመርከበቹ መቆሚያ ደርሳ በጥላቸው ተከልላ ብቅ ጥልቅ በምትልበት ሰዓት አዛዡዋም ሃያ ዘጠኝ ጊዜ የመርከበኞች ሰላምታ ከሚጮህ መርከብ ተቀብሷል (ተደርጎለታል) ። ከዚያ በኋላ ወደ ውስጥ ወደ ባሕሩ ወረደ ። አብረውት ከነበሩት አምስት መኰንኖችና ሃምሳ አባሎች መካከል ስለ ሣጥኑ ምሥጢር የሚያውቅ እርሱ ብቻ ነበር ።

## ፲ ዘ ።

ሬሳውን ይዞ የነበረው ሣጥን በመርከቡዋ ወለል ላይ ተጋድሞ በነበረበት ሰዓት ምሥጢሩን ከሚያውቁት ባለሌላ ማዕረጎች አንደኛው "የጠይሙ ዮሐንስ ሬሳ" ብሎ ሲናገር ሌላው ደግሞ "አዲሱ የመርከባችን አጃቢ" ብሎ አፌዘበታል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዛሬ ከብዙ ዓመታት በኋላ በሣራፍ መርከብ ላይ የነበሩት ሃምሳ ሠራተኞችና አባሎች በዚያን ጊዜ የነበሩበትን ሁኔታ ከጊዜ በኋላ ሲሰሙ ይንቀጠቀጣሉ ። በዚያን ጊዜ በባሕር ጠላቂ መርከባቸው ሲጓዙ የተነገራቸው ያ-ሬሳውን ይዞ የነበረው ሣጥን በውስጡ ልዩ ረቂቅ መሣሪያ ስለ ያዘ በእስፔይን ባሕር ዳር በኩል ተጥሎ እየተንሣፈፈ የአየሩን ሁኔታ እየመዘገበ እንዲያስተላልፍ የሚጣል መሆኑ ነበር። ይህንም እውነት ለማስመሰል በላዩ ላይ "የባሕር ኃይል ልዩ መሣሪያ ስለ ሆነና ተሰባሪም በመሆኑ በጥንቃቄ እንዲያዝ" የሚል ጽሑፍ ነበረበት ።

ለዐሥር ቀናት ያህል ሣራፍ በባሕር ውስጥ ስትጓዝ በላዩዋ ላይ የነበሩትም አባሎች የፀሐይ ጨረር አላዩም። ከጥልቀት ወደ ባሕር ትወጣ የነበረውም ሌሊት ሌሊት ነበር። በተወሰነላት ጊዜ ማለት ሚያዝያ ፴ ቀን ማንም ሳይከታተላትና ሳያውቃት መልእክቷን ፈጽማ ከሂውልባ ባሕረ-ጠረፍ ወደ ደቡብ ምዕራብ እስፔይን ጉዞዋን ቀጠለች ።

ሻለቃ ማርቲን እንዲንሳፈፍበት የተመረጠው ሥፍራም ከሂውልባ ባሕር መዳረሻ 1600 ያርድ ያህል ብቻ ርቀት ነበረው ።

በዚሁ ቀን ከሰዓት በኋላ ሣራፍ ከተወሰነው ሥፍራ ደረሰች። ፡ልዩ መሣሪያም ሃምሳ የሚሆኑ የዓሣ ማጥመጃ ጀልባዎች መኖራቸውን አረጋገጠች። ግን እርሷን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመታየት የሰወራት ጭጋግ ነበር ። ከዚያ በኋላ ወደ ባሕሩ ወለል ዘቅዝቃ ወረደችና በዚያው ተደበቀች ።

<u>ለማመን ያስቸገረ ጉዳይ ።</u>

ሰዓቱ ከሌሊቱ 10·30 ነበር ። ሣራፍ ወደ ላይ ስትወጣ ጨለማው እንደተጫጫነ ነበር ። ጨረቃ ታይታለች ፤ ግን ብርሃን ሰጭነቷ ተድበስብሷል ።

ለመርከቦች ምልክት በሚሰጠው ሰቀላ ቤት ሥር አምስት የሣራፍ መኰንኖች ተጠርተው ተሰናዱ ። ጠላ ቂዋ መርከብ ጥቂት ዝቅ ብላ ከባሕሩ ስትወርድ ውሀው እየተንቦጫረቀ ይፈናጠር ጀመር ። ከዚያ በኋላ ለማመን አስቸጋሪ የነበረው ሬሳ ለመንሣፈፍ ይዘጋጃል ።

የመቶ አለቃ ጀዊል መኰንኖቹን ብቻ ለብቻቸው ጠራቸውና በእግራቸው ሥር የሚገኘው ሣጥን ወታደር እንዳለበት ነገራቸው ። ጠላትን ለማታለል የተባበሩት መንግሥታትም ጦር በሚዲትራኒያ ባሕር አካባቢ የሚያ ደርገውን ወረራ ለመጀመር ያ - ሬሳ ለከፍተኛ ዘመቻ መመ ረጡን ነገራቸው ፣ ሻለቃ ማርቲን የሚል የፈጠራ መጠ ሪያ ተሰጥቶት አይሮፕላኑ ከባሕር ላይ ወድቆበት እንደ ሞተ ተመስሎ በባሕሩ ላይ እየተንሳፈፈ እንዲገኝ ለዚህ አስቂኝ ዘመቻ ሬሳው መመደቡን ገለጸላቸው ።

ሬሳው በሂውልባ ባሕር ዳር እንዲንሣፈፍ የተመረጠ ውም በዚያው ሃገር የሚገኝ ቀንደኛ የጀርመን ሰላይ ነገ ሩን ደርሶበት ለጀርመን ባለ ሥልጣኖች እንዲያስተላልፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። መርከባችሁ በውቅያኖስ ተከበ እኩሉ ሌሊት ላይ ይህን የመሰለ ታሪክ ስትሰሙ የቱን ያህል ያስገርማችኋል! ቢሆንም መኰንኖቹ አዛገሮቻቸው በቈራጥነትና በልበ ሙሉ ነት የሚፈጽሙትውን ለመከላከልና ለማስቀረት አይችሉም ። ከመካከላቸው አንዱ መኰንን ብቻ "ሬሳ ተሸክሞ መዘር በእርግጥ ያለመታደል አይደለምን?" ብሎ ሲያጕረመ ርም ተሰምቷል ።

## ኃይለኛ ስሜት ።

አምስቱ ሰዎች በፀጥታና በርጋታ ከባዱን ተግባራቸ ውን ጀመሩ ። ፫ቱ በተጠባባቂነት ላይ ተመድበው ሲመለ ከቱ ፣ ሁለቱ ደግሞ ከመቶ አለቃ ጀዊል ጋር እየተረዳዱ ሬሳውን ከሳጥኑ ማውጣት ጀመሩ ። ይህም ሥራ ዐሥር ደቂቃ ያህል ፈጀባቸው ።

ሬሳውን በቀስታ ከሳጥኑ ሲያወጡት መኰንኖቹ ኃይ ለኛ የሆነ የመንፈስ ድንዛዜ ተጫጫናቸው ። ተጠቅልሎ በት የነበረውን ብርድ ልብስ ከላዩ ላይ ገፈፉትና ሬሳው ከአስፈላጊዎቹ መሣሪያዎች ጋር በሚገባ የተቈራኘ መሆ ኑን መመርመር ቀጠሉ ። የሻለቃው ልብስና ምልክት በሚገባ ነው? እጅግ አስፈላጊ የሆኑት ጉዳዮች ሁሉ እንደተደከመበት ተያይዘዋል? ቦርሳው ከቀበቶው ጋር ተሳስሯል? ሁሉን ነገር ራሱ የመቶ አለቃው በጥንቃቄ መረመረው ። ከዚያ ቀጥሎ አራቱ መኰንኖች በዚህ ከፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቱኛ ምሥጢር ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ቃለ መሐላ መፈጸም ጀመሩ ።

"ያየሁትንና ሰማሁትን ነገር እስከ መጨረሻው ድረስ ለማንም ቢሆን በምንም ዓይነት ዘዴ ላልናገር በውጁታዬ ቃሌ ገብቻለሁ ። ነገሩ ከባድና አስቃቂም ቢሆንብኝ ለሃገሬ ፍጹም ነዋሪነት የሚውል ሥራ ስለሆነ ይህንኑ ለማንም አልናገርም" ቃለ መሐላው ተፈጸመ ።

ከዚያ በኋላ በቀስታ ወደ ባሕሩ ላይ ገፉ ተደርጎ ተጣለ ከወገኖቹም ተለያየና ሻለቃው ወደ ጦርነቱ ጉዞ ቀጠለ ።

የሙቶ አለቃ ጀዊል ያለምንም ማወላወልና ስጋት ወደ ባሕሩ ዳርቻ ተጠግቶ የፈጸመው አስደናቂ ሥራ እቅዳችንን የተቃና ውጤት አስገኝቶለታል ። ከዚያ ቀጥሎ የነበረን ሥራም የሻለቃ ማርቲን ሥራውን በምን ሁናቴ ግከናወን እንደሚችል ነበር ።

## ሻለቃ ማርቲን እስፔይን ደረሰ ።

ግንቦት ፫ ቀን ማድሪድ ውስጥ ተቀማጭ የነበረው የባሕር ክፍል ተጠሪያችን አንድ የሬዲዮ መልእክት ደረሰን ። በዚያም መልእክት ውስጥ ሚያዝያ ፴ ቀን የሮያል ባሕር ኃይል አግረኛ ተዋጊ የሆነ የሻለቃ ማርቲን ሬሳ በሂውልባ ባሕር ዳርቻ ላይ ሲንሳፈፍ ዓሣ አጥማጆች ያገኙት መሆኑን ማድሪድ የነበረው ም/ቆንሲላችን የነገረው መሆኑን ገልጾ ጻፈልን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሬሳው በጽሞናና በጊዜው ለእንግሊዝ ም/ቆንሲል ተሰጠና በወታደር ሥነ ሥርዓት የቀብሩ ግባት-መሬት ተፈጸመለት። የእስፐይን የጦርና የሰላማዊ ባለሥልጣኖችም ተገኝተው በቀብሩ ላይ ኀዘናቸውን ገልጸዋል። ይህም የሆነው ሬሳው በተገኘ በማግሥቱ ነበር። የተቀበረውም ሂውልባ ውስጥ በሚገኘው የመቃብር ሥፍራ ነው። በተላከልን መልእክት ላይ ስለ ቦርሳው ወይም ስለ ወረቀቶቹ የተገለጸልን ነገር የለም።

ወዲያው በባሕር ኃይላችን ጽ/ቤትና ማድሪድ በነበረው የባሕር ኃይል ተጠሪ መካከል የቴሌግራም መለዋወጥ ተጀመረ። ደብዳቤዎቹ የተላኩበትን ዲላማ እንዲመቱ አስፈላጊ እንዲሆን የሻለቃ ማርቲን ሞትና ሬሳውም እስፐይን ውስጥ መድረሱ በኅብረት የጦር እዛችን ጠቅላይ መምሪያ መገለጽ ስለሚኖርበት እጅግ አስፈላጊና ብርቱ ምሥጢር የያዙት ደብዳቤዎቻችን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይዛመቱ መጣጣር ነበረብን። ሰር አርችባልድ ነይ የጻፉትም ደብዳቤ ብርቱ ምሥጢር የያዘ ስለሆነ፤ ወሬው እንዳይዛባና ከፍተኛ ውድቀት እንዳያስከትልብን መጣጣር ነበረብን። በዚህ ምክንያት በእስፐይን ዋና ከተማ ማድሪድ ውስጥ ለነበረው የባሕር ኃይላችን የተደጋገመ መልእክት ባስቸኳይ ማስተላለፍ ተገቢ ሆነ። በነዚያም መልእክቶቻችን የባሕር ኃይላችንን ተጠሪ የወተወትነው የሆነውን ያህል ክፍሉ ምሥጢራቸው ከመባከኑ በፊት ወረቀቶቹን እንዲያስመልስልን ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደብዳቤዎቹ እንዲመለሱለት የተቻለውን ያህል የትግ ጣሬ እንደሆነ የእስፐይን ባለሥልጣኖች ጉጉት ያድርበ ቸውና ደብዳቤዎቹን ከፖስታ እያወጡ ሊመለከቱዋቸው ወይም ጠፍተዋል እንዲሉ ለመገፋፋት ስንል ተጠሪያችን ውትወታውን ችላ ሳይል እንዲገፋበት አስጠነቀቅነው ። የኛ ጥረት ጠቅላላው ጉዳይ እውነት መስሎ እንዲገመ ትልን መጣጣር ስለ ነበረ ፣ ስንለዋወጣቸው የነበሩት ቴሌ ግራሞችም በዚሁ አስተሳሰብ ላይ ያረፉ ነበሩ ። ግንቦት ፱ ቀን ቴሌግራም ማስተላለፉን ስንጀምር ሻለቃ ማርቲን እጅግ ብርቱ ምሥጢር ያለባቸው ደብዳቤዎች ይዞ ስለ ነበረ እነዚያኑ ደብዳቤዎች የባሕር ኃይል ተጠሪያችን የእ ስፐይን ባለሥልጣኖች ጠይቆ እንዲያስመልስ ጠየቅነው ። ምናልባት ደብዳቤዎቹ ከሬሳው ጋር አልተገኙም እንደ ሆነ ፣ በሂውልባ የባሕር ጠረፍ በኩል ፍለጋ እንዲደረግና ሁኔታቸውንም እንዲገልጽልን ጠየቅነው ። ያገኛቸውም እንደሆነ ፣ ለባሕር ኃይላችን የመረጃ ክፍል እንዲያስታ ውቅ እንጅ ፖስታውን ራሱም እንኳ እንዳይከፍት ሆኖ በተቻለ ፍጥነት ወደ ባሕር ኃይላችን እንዲመልሳቸው በጥብቅ አስጠነቀቅነው ። ከዚህ አከታትለን ደግሞ የሮያል ባሕር ኃይል አርማ ባለበቱ ቦርሳ ውስጥ እጅግ ብርቱ ጉ ዳይ ያለባቸው ፫ ደብዳቤዎች ስለ ነበሩ በተቻለ መጠን ፈልጎ እንዲያገኛቸው አስታወቅነው ። እንደገናም ደብዳ ቤዎቹ የያዙት ጉዳይ በምንም ስለምንም ቢሆን የእስፐ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶንን ጉዳይ የማይመለከቱ መሆናቸውን አረጋግጥንለት ።

የባሕር ኃይል ተጠሪያችንም በመጀመሪያ ላስተላለፍ ንለት ቴሌግራም በሰጠው መልስ ውስጥ ደብዳቤዎቹ ለ ልዩ ጥናት ጉዳይ ወደ እስፐይን የባሕር ኃይል ጠ/ሠፈር የተወሰዱ መሆናቸውን የባሕር ክፍል ሚኒስቴር ያረጋገ ጠለት መሆኑን ገለጸልን ። ካዲዝ በሚባል ቀበሌ የነበረ ውም የእስፐይን የባሕር ኃይል ደብዳቤዎቹ እስኪደርሱ ትና እስኪአጠናቸው ድረስ ጥቂት ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑን አስታወቀን ።

በሄውልባ የነበረውም ም/ቆንሲላችን በበርሳው ውስ ጥ የነበሩትን ወይም ሌሎች ደብዳቤዎች ለማግኘት ያል ቻለ መሆኑን የባሕር ክፍላችን ተጠሪ አረጋገጠልን ። ከዚህ በኋላ ግንበት ፲፫ ቀን ያው የባሕር ክፍል ተጠሪያ ችን ባስተላለፈልን መልእክት የእስፐይን የባሕር ክፍል ሚኒስትር በሌለበት የባሕር ኃይሉ የበላይ መኰንን ከሻ ለቃ ማርቲን ሬሳ ጋር የተገኙትን ዕቃዎች ሁሉ የደብዳቤ መያዣ በርሳውንም ጭምር የሰጠው መሆኑን ገለጸልን ። ደብዳቤዎቹም ተከፍተው ያልታዩ መሆናቸውንና የበላይ መኰንኑም "ሁሉ ነገር እንዳለ ነው" ብሎ የተናገረው መሆኑን እርሱም ልባዊ ምስጋና እንዳቀረበለት አስታወ ቀን ። በተጨማሪም የእስፐይን የባሕር ኃይል የበላይ መኰንን ደብዳቤዎቹን የተመለከተና ስለ ምሥጢርነታ ቸውም ያወቀ ፤ ግን ለማንም ሰው መናገር የማይችል



t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን የኛው ተጠሪ ያመነበት ለመሆኑ አብራርቶ ጻፈ ልን ። እርግጥ ነው ስለ ደብዳቤዎቹ ጉዳይ አንድ የእስፐ ይን መኰንን ከወቀ ሌላውም እንደሚሰማ ስለምናውቅ ነገሩ እየተጓተተና ምስጢርነቱም እየሾለከ እንደሚወጣ ተረዳነው ።

የባሕር ኃይል ተጠሪያችን በላከልን መልእክት ደግሞ በይበልጥ ተማመን ። ተስፋችን ለመለመ ። ግንቦት ፲፭ ቀን ቀዳሚ የእስፐይን የባሕር ክፍል ሚኒስትር የኛን የባ ሕር ኃይል ተጠሪ ሲያነጋግረው ደብዳቤዎቹ ስለ ያዙት ጉዳይ የጠቃቀሰለት መሆኑን ገለጸልን ።

ሚኒስትሩ ቫለንችያ በተባለች ሃገር በነበረበት ወቅት የደብዳቤዎቹን ማድሪድ መድረስ እንደሰማ ወዲያውኑ እንዲመለሱልን ለባሕር ኃይሉ የበላይ መኰንን ትእዛዝ አስተላልፎ እንደ ነበረ ፣ ለኛ ተጠሪ ገለጸለት ። ግን አንድ ያልተፈቀደለትና ሥልጣን የሌለው የክፍሉ ሠራተኛ ደብ ዳቤዎቹን ምናልባት ተመልክቶአቸው እንደሆነ ከባድ ጉዳይ የሚፈጠር መሆኑን እንደገለጸለት ጻፈልን ።

በዚህ መሠረት በቦርሳው ውስጥ የነበሩት ብርቱ የም ሥጢር ደብዳቤዎች ተከፍተው የተነበቡ መሆናቸውን አረጋገጥን ። በዚህም መሠረት ደብዳቤዎቹን አንድ እስፐ ይናዊ ከነበባቸው ለጀርመኖች እንደሚነግርልን ተማምነን በታል ። በሁለቱ መካከል የነበረውን መተሳሰብና መቀራ ረብ ግን ጠርነቱ አለቀ ፣ ድረስ አላረጋገጥንም ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህም ሆኖ በሺውልባ የባሕር ዳርቻ የሆነውን ጉዳይ ሁሉ በዝርዝር ለማወቅም ችለናል። ነገሩም እንዲህ ነበር። አንድ ዓሣ አጥማጅ አንድ የሚንሳፈፍ ነገር በሩቅ ይመለከታል። ወዲያውም እየጐተተ ወደ ውጭ ይወስደዋል። ተንሳፋፊው ነገር ሬሳ ሆኖ ስለ አገኘው ይደናገጥና በባሕሩ ዳር እግረኛ ወታደሮችን የውጊያ ስልት ሲያለማምድ ለነበረ የጦር መኰንን ያስረክበዋል። ከዚያ በኋላ አንድ የእስፐይን የባሕር ኃይል መኰንን ይጠራና ሬሳውንና መረቀቶቹን ሁሉ ይረከባል። ሬሳው ወደ ሐኪም ቤት ከተላከ በኋላ፤ ሐኪሙ ይመረምረውና ከአምስት ወይም ከስምንት ቀናት በፊት ከባሕር ላይ ወድቆ የሞተ ነው ብሎ ያረጋግጣል። ከዚያ ቀደም ብሎ ሚያዝያ ፳፮ ቀን አንድ አሜሪካዊ አይሮፕላን አብራሪ አይሮፕላኑ ከባሕር ላይ ሲወድቅ በጃንጥላ ወርዶ በዚያው ስለ ነበረ፤ የሻለቃ ማርቲንን ሬሳ ያውቅ እንደሁ እንዲመረምረው ተሰጥቶት ነበር። ግን ሊያውቀው አልቻለም። እንዳሰብነውና ተስፋ እንዳደረግነው የሬሳውን ወሬ ያ-ቀንደኛ የጀርመን ሰላይ ይሰማል። ወዲያው ከሬሳው ጋር የተገኙት ደብዳቤዎች ሁሉ እንዲሰጡት ውትወታውን በፍጥነት ይጠይቃል። ይህን ስንሰማ ያቀድነው ነገር ሁሉ በመሳካት ላይ መሆኑን ተረዳን። የሚሆነውን ሁሉ በትዕግሥት መጠባበቅ ጀመርን፤ ወረቀቶቹም እንዲመለሱልን ውትወታችንን ቀጥለናል። የመጨረሻውን ምርመራም ለማድረግ ጓጕተናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደብዳቤዎቹ ወደ ለንደን እንደ ተላኩልንም የረቀቀ ምርመራ ተደረገባቸው። በተራቀቀ የሳይንስ መሣሪያ አማካይነት ባደረግንላቸውም ምርመራ ሁለቱ ደብዳቤዎች ከየፖስታዎቹ ተከፍተው ወጥተው እንደገና በረቀቀ ዘዴ መታሸጋቸውን አረጋገጥን። በሂውልባ የባሕር ዳር በተፈጸመውና የባሕር ኃይላችን ተጠሪ በላከልንም መልእክት ላይ በተረዳነው ጉዳይ ሁሉ ተደስተናል። በኛ ግምትና ጥርጣሬም መሠረት እስፐዩናውያን ጋር የተገኙትን ደብዳቤዎች ቅጅ ያስቀራሉ። የተራቀቁት ጀርመኖች ደግሞ ጉዳዩን ይደርሱበትና ደብዳቤዎቹ ከማንኛው ባለሥልጣን ዘንድ እንደሚገኙ ካረጋገጡ በኋላ፤ በተቻለው ሁሉ ዘዴ ያቸው ደብዳቤዎቹን ያገኙና ወደየአለቆቻቸው ያስተላለፉሉ። ቀልጣፋዎቹ የጀርመን ሰላዮች ይህን እንደሚያደርጉ ተማምነንባቸዋል። ከዚያ በኋላ የበኩሏን ሁሉ መፈጸም የነበረባት በርሊን ነበረች።

ሻለቃ ማርቲንን በሕሊና አክብሮት እንሰናበተዋለን። ሃገሩን በሚገባ አገልግሏታል። በመዋቲነቱም ቢሆን ሬሳው ለታላቅ ቁም ነገር ውሏልና ለመጨረሻ ጊዜ ያረፈባትን መሬትና የቀብሩ ሥነ ሥርዓት በተገቢው አኳኋን መፈጸሙን ማረጋገጥ ነበረብን።

ሬሳው ምንም አሰቃቂ አደጋ ሳይደርስበት ከታሰበው ቦታ ደርሶ መሠረታዊውን መልእክት አድርሶ በሚገባ ግባተ-መሬቱ ስለ ተፈጸመለትም እጅግ ደስተኞች ነበርን።

t.me/OLDBOOKSPDF

እርግጥ ነው አእምሮአችን ያፈለቀውን ሐሳብ በሥራ ላይ አውለነዋል ። ባደረግነው ዘዴም የእስፐይን ዶክተር ውሳኔ ተስማምቶበት ለኛ ተስማሚውን ውሳኔ ሰጥቶበታል።

የሻለቃ ማርቲን መቃብር በእብነ በረድ ከመዘጋቱና ከማጌጡም በፊት ምናልባት ጀርመኖች ወይም እስፓን ሾች ቈፍረው እንዳያወጡት እንግሊዛውያን በየጊዜው የመቃብሩን በታ እንዲጐበኙና አበባም እንዲያስቀምጡ ብት ተደረገ ።

በመጀመሪያ በሻለቃው የፈጠራ እጮኛ በፓምና በ ቤተ-ሰቧ ስም የአበባ ጉንጉን በመቃብሩ ላይ እንዲቀ መጥ የባሕር ኃይል ተጠሪያችንን አዘዝነው ። ቀጥሎም መቃብሩ በሚገባ እንዲሠራና ምክትል ቆንሲላችንም ስለ ፈጸመው ጥረት የባሕር ኃይላችን ተጠሪ በቤተ-ሰቡ ስም ሆኖ እንዲያመሰግነው ጻፍኩለት ። የመቃብሩ በታ ፎቶግራፍ ተነስቶ ለእጮኛውና ለቤተ-ሰቡም እንዲላክ እንዲያደርግ ለባሕር ኃይላችን ተጠሪ ጻፍኩለት ።

በሂውልባ አካባቢ ተቀማጭ ከነበረ አንድ የማዕድን ኩምፓኒ ከሆነ የእንግሊዝ አጥር ጓሮ ውስጥ በሬሳው ላይ የሚቀመጠው አበባ ተለ~መ ። በእብነ በረዱም ላይ “ዊሊ ያም ማርቲን መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፯ ዓ. ም. ተወለደ ። ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ሞተ ። አባቱ ጆን ጅለየ ንድዋየር ማርቲን ይባላል ። እናቱም አንቶኒያ ማርቲን ትባላለች ። የትውልድ ሃገሩም ካርዲፍ ዊልስ ነው” የሚ ል ቃል ተጻፈበት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ ሌላ ልናደርግለት የምንችለው ምንም አልነበ ረንም ። በሽሕ የሚቈጠሩ የሃገሩ ወታደሮችና የቃል ኪ ዳን አገሮች ወታደሮች አሜሪካውያንም ጭምር ከቃሰበ ችው ሲስሊ ያለምንም እልቂትና ጉዳት ሲደርሱ የእርሱ ባለ ውለታዎች እንደሚሆኑ ተሰምቶኝ ነበር። እርግጥ ነው የነበረኝ ግምት አልተቀጨም ። ዛሬ የእርሱ ባለ ውለታ ዎችና የእርሱን አገልግሎት የሚያደንቁ ብዙዎች ናቸውና።

የመቶ አለቃ ጀዊል የፈጸመው ጥረት ሁሉ ከፍተኛ ውጤት ማስገኘቱንም ገልጨ ደብዳቤ ጻፍኩለት ። ምናል ባት በቴሌግራም ነገሩን ገላልጨ የጻፍኩለት እንደሆነ ሌላ ነገር እንዳይነሳ ፈራሁና "ሻለቃው ምቹ በሆነ ሁኔታ ላይ ይገኛል" ብዩ ጻፍኩለት ። ይህን ስለውም ነገሩን ይረዳ ዋል ብዩ በመተማመን ነበር ። ይህንም የጻፍኩለት ተራ በሆነ የፖስታ ካርድ ነው ። የጦራችን የበላይ አዛዥ ደግ ሞ በዚያን ጊዜ ዋሽንግተን ለነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትራ ችን ባስተላለፉት መልእክት ላይ "አስመሰዩ ዘማች ጉዳት ሳይደርስበት ሁሉንም ነገር ውጦታል" (ሰልቅጦታል) ብለ ዋል ።

## ጉጉትና ትዕግሥት ።

እኛ (ሁላችንም የባለቃል - ኪዳን መንግሥታት ማለቴ ነው) ልናደርገው የሚገባንን ሥራ አከናውነናል ። የፈጸ ምነውን ተግባር ውጤት የምናገኘውም ሲስሊይ ለማረፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

እስከተቻለን ድረስ ነበር ። እዚያ ለመግባት የሚያበቃን ንም ዕድል የምናገኘው ጀርመኖች ቀበሌዋን ለቀው የመ ጡልን እንደሆነ ብቻ ነበር ።

ስለዚህ የጀመርነው ሥራ ውጤት እስኪሰጠን ድረስ በጉጉት ተውጠን ትዕግሥትን ተከናንበን መጠባበቅ ነበረ ብን ። በዚሁ ጊዜ ደግሞ በየጊዜው የሚሞቱትንና የሚቈ ስሉትን ወታደሮቻችንን ዝርዝር "ዘ-ታይምስ" የተባለው ጋዜጣችን ይገልጸው ስለ ነበረና ፤ ጋዜጣውም ሊዝቦን ይደርስ ስለ ነበረ ፤ ጀርመኖች ነገሩን እንዲከታተሉት ብር ከፍተንላቸዋል ። እኔም ወታደሮቹ የሞቱበትንና በጋዜጣ የተገለጸበትን ቀን ለማወቅ ያህል ልዩነቱን መረመርኩት ። እንደ ቀዋሚ ትእዛዝ ሆኖ የተሰጠው መመሪያም ከአም ስት ሳምንታት የማይበልጥ መሆኑን አወቅሁ ። ይህም ነገ ር ከሚያዝያ ፳፬ ቀን እስከ ሰኔ ወር መጀመሪያ ሳምንት ድረስ የነበሩት ቀናት ለኛ እቅድ አንድ ተልእኮ የምናስ ተላልፍባቸው እንደሚሆኑ ተረዳሁ ።

እዚህ ላይ ስንደርስ ያፋጠጠን ጥያቄ ደግሞ በመጥቲ ዎቹ ወታደሮቻችን የስም ዝርዝር ውስጥ የሻለቃ ማርቲ ንን ስም እናስገባው ወይ ? የሚል ነበር ። ጉዳዩስ ዋጋ ይኖረዋል ወይ ? ሲሲሊይን እንይዛለን ብለን ያወጣነው እቅድ እስከ ሐምሌ ፫ ቀን ድረስ ነበር ። ጀርመኖችም ይህነኑ ጉዳይ በጥብቅ መከታተላቸው የማይቀር ነበርና ጠቅላላውን ጉዳይ እውነተኛ ለማስመሰል የሻለቃው ስም



t.me/OLDBOOKSPDF

መገለጹን አምነንበታል ። ያቀረብነው ማታለል አንድ ዓይነት እርምጃ የሚያስወስድ ከሆነ ከሰኔ ወር መጀመሪያ ሳምንት ላይ መሆን ነበረበት ። እኛ ሲ.ስ.ሊ.ይ ከመግባታችን አስቀድሞ ማነኛውንም ነገር መጀመር ነበረብቸው ። በሌላው በኩል ነገሩን ያጠናነው እንደሆነ ደግሞ የሲ.ስ.ሊ. ጦርነት ወይም ወረራ ባልታወቀ ምክንያት ሊዘገይ ይችላል ። ነገሩን ብንጠላውም ከተጨቃጨቅንበት በኋላ፣ ሳና ደርገው ቀርተን ከሚቈጨን አድርገነው፣ የሚሰጠውን ውጤት መጠባበቁ እንደሚሻል ተረዳነውና የሻለቃው ስም መዋቲነቱ ታምኖበት በጋዜጣ እንዲገለጽ ተስማማን።

የመጨረሻውን ውሳኔ ስናጸድቅም በውሸት ላይ ውሸት በመጨመራችን ተከዝንበት ። ይሁንና ይኸው ውሳኔያችን በኛ ላይ ያልተጠበቀ ችግር እንዳያደርስብን እንጅ፣ ሌሎችን የሚጎዳ ሆኖ አይደለም ። እንደ ተመኘነው የማታለያው እቅዳችን ሁሉ ቀስ በቀስ ይከሄድ ጀመር ። ዕድላችንም እያማረ መጣ ።

በባሕር ኃይላችን ጠቅላይ ጽ/ቤት የዕለት ሁኔታ ክፍል ሄደን በጦርነት ከተጐዱ አባሎች ስም ዝርዝር ጋር የሻለቃ ዊሊያም ማርቲን ስም አብሮ እንዲገለጽ ለማድረግም በጣም ቀላል ነበር ፡ ይህን በማታለልና በቀልድ የተጠቃለለ ታሪክ በተከታታይ የስም ዝርዝር እንዲገለጽ ለዕለት ሁኔታው ክፍል ሳስታውቅ ምን ብዬ ይቅርታ እንደ ጠየቅሁና እንደ ተናገርኩ ረስቼዋለሁ ። ማስታወቂያውም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. በዕለተ ዓርብ በወጣው ዘ - ታይ ምስ ጋዜጣ ላይ ተገለጸ ። ግን ይህን ስም አስታውሰው ጀር መኖች የሚከታተሉት መሆናቸውንና ያለመሆናቸውን አላ ውቅንም ። ቢከታተሉት ግን በዚያው ዝርዝር ውስጥ የአድ ሚራል ፒ. ጀ. ማክንና የሰር ቲ. ኤል. ቢ. ሶርን ስም ያገ ኙት ነበር ። እነዚህ መኰንኖችና ሌሎችም ስማቸው በጋ ዜጣ ያልተገለጸ አባሎች የሞቱት ይበሩበት የነበረው አይ ሮፕላን በውቅያኖስ ውስጥ በመውደቁ ነበር ።

እንግዲህ ሻለቃ ማርቲንም የሞተው ከነዚሁ ሰዎች ጋር ነው ቢባልስ ምን ጉድ ይወለዳል ? ከዚህም ሌላ ደግ ሞ በዕለት ሁኔታው መዝገብ ላይ በጋዜጣ ሊገለጽ ተዘጋ ጅቶ የነበረው አጋጣሚው ዕድል ይኸው ነበር ። ጀርመ ኖች በጋዜጣ ላይ የሚገለጸውን ዝርዝር እንደሚያገኙትና በተለይም የሻለቃ ማርቲንን ስም እንደሚያጠኑት ተስፋ አደረግሁ ። ነገር ግን ችግሩ ደግሞ ወዲያው ጀመረ ። በጦርነቱ የተጐዱት ሰዎች ስም ደግሞ ለካ በሌሎች ክፍ ሎች ይጠናና ክትትልም ይደረግበት ኑሩዋል ። ማድሬድ በነበረው የባሕር ኃይል ተጠሪያችንና በኛ መካከል ሲጐ ርፍ የነበረውን መልእክት ሲፈቅድ የነበርኩና መልእክቶ ቹም ዘወትር በሚሠራው አኳኋን እንዲታደሉ ስከታተል የነበርኩ እኔ ነኝ ።

የባሕር ኃይላችን የዕለት ሁኔታና የሕይወት ታሪክ አቀናባሪ ክፍላችን የሻለቃ ማርቲን ተናዘ እንደሆነና ኑዛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዜውስ የት እንደሚገኝ ይጠይቃል ። በተጨማሪም የሠራ ዊቱ ሕክምና ክፍል የሻለቃ ማርቲን የሞተው በውጊያ ላይ እንደሆነ፣ ቈስሎ የሞተም እንደሆነ፣ ወይም በሥራ ላይ ሳለ ሙቶ እንደሆነ የሞተበት ሁኔታ ተገልጾላቸው፣ ማኅደራቸውን በተገቢው ሁኔታ ለመያዝ ይፈልጋሉ ።

እንደ መታደል ሆነልኝና ስለ ሻለቃ ማርቲን የኑዛዜ ወረቀት ወይም ስለ ራሱ ማንነት ጥያቄ ይመጣብኝ ይሆ ናል ብዬ የወሰድኩት ጥንቃቄ በሚገባ ተሠራና አጥጋቢ ውጤት ተገኘበት ። ጥያቄው እንደሚመጣ ቀደም ብዬ ስለ ሰማሁና ራሴም ስለ ተጠራጠርኩ ነገሩ ከመዛመቱና ሌላ ጥርጣሬ ከማስነሳቱ በፊት ለመከላከልና ጉዳዩን ከሚመለከተው ክፍል ጋር ልወያይበት ቻልኩ ። ለጥያ ቄው መልሱን እንዲያፈልቅ አእምሮዬን አስጨነቅሁት ። የሻለቃውን የኑዛዜ ቃል የማክከና ከምፖኒ እንዲያቀርብ መወከል ወይም አሳልፎ መስጠት አልችልም ። እርግጥ ነው የከምፖኒው ነገረፈጅ ሻለቃ ማርቲን ጉዞውን ከመ ጀመሩ በፊት ኑዛዜውን ጽፎታል ። ይህ ዕንቅፋት በተደነ ቀረብኝም ጊዜ "ለማታለል ነገሩን በጀመርነው ሰዓት ምን ዓይነት ምስቅልቅልና 'ማዕበል አስነስተን ነበር" የሚለውን ምሳሌያዊ ጥቅስ ከልቤ አደነቅሁት ። ስለ ሻለቃ ማርቲን ምንነትና ሞት ብዙም እንዳይጨነቁ ለየክፍሉ ኃላፊዎች ነገርኳቸው ። ስለ እርሱም ጉዳይ የባሕር ኃይል ባለሥል ጣኖች ፈቅደውለት፣ ልዩ ማዕረግና ልዩ ሥራ ተሰጥቶት

t.me/OLDBOOKSPDF 

የተላከ መኰንን መሆኑን ገለጽኩላቸው ። ይህም ደግሞ እውነተኛው ጉዳይ ነበረ ። ግን የተላከበትን ጉዳይ ከመፈጸሙ በፊት መሞቱን ሳልነግር "ረሳሁት" እያልኩ አስታ ወስኩ ። የባሕር ኃይሉ የመረጃ ክፍል ባለሥልጣኖች በነገሩ ገቡበትና ጉዳዩ ከፍተኛ ምሥጢር ያዘለ ስለሆነ፣ ጥንቃቄ እንዲደረግ ለየክፍሎቻቸው አስጠነቀቁ ። የጉዳዩ ምሥጢርነት እያፈተለከ ለመውጣት ተቃርቦ የነበረበቱ አቅጣጫም ተዘጋልን ።

እዚህ ላይ አንድ ጉዳይ በተጨማሪ ለማውሳትም ደግሞ እወዳለሁ ። ከውትድርናው አገልግሎት ከወጣሁ ከጥቂት ዓመታት በኋላም አንድ አስቸኳይ ጥያቄ ቀረበልኝ ። ያም ጥያቄ ወደ ባሕር ኃይላችን የመረጃ ድርጅት ሄጄ ጉብኝት እንዳደርግ ነበር ። በዚህም ጊዜ ስለ ሻለቃ ማርቲን ጉዳይ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው የጠየቁ ክፍሎች ስለ ነበሩ፤ ያን መዘዘኛ ጉዳይ እንደምን አድርጌ አመሰቃቅለው እንደ ነበረ ጠየቁኝ ። በዚሁም ጊዜ ቢሆን ያለፈውን መልስ ሰጠኋቸው ። ስለዚህ ያው የበፊቱ መልስ እንደገና የሕይወት ታሪክና የዕለት ሁኔታ ያቀነባብሩ ለነበሩት ክፍሎች ተሰጠ ።

ዳሩ ግን ከዚያ ከዕለት ሁኔታ በጦርነት ከተጐዱ ወታደሮች ስም ዝርዝር ሌላ "የማስመሰያው ዘመቻ" ጉዳይ ከኛ እጅ ወጥቷል ። እኛም ሆን የመቶ አለቃ ጆዊልና ሻለቃ ማርቲን ድርሻችንን ፈጽመናል ። ጀርመኖችስ ምን ይሠሩ ኑረዋል ?



t.me/OLDBOOKSPDF

## የጀርመን ሰላዮች ጥረት ።

ከግንቦት መጨረሻ፥ እስከ ሰኔና ሐምሌ ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ድረስ በጠጣነው ዘዴ የተቃና ውጤት የምናገኝበት ለመ ሆኑ ምንም ማረጋገጫ አልነበረንም ። ብቻ ውስጣዊ እም ነት ነበረን ። ጀርመኖች እስፐይን ውስጥ በመሥሪያቤታ ቸው ልክ በትክክለኛነታቸውና በቅልጥፍናቸው ብርታት የኛም ጉጉት መወሰኑን እምነንበታል ። ያዘጋጀነው የይ ምሰል ጽሑፍ ሁሉ ከእጃቸው እንደ ገባ እርግጠኞች ሆነናል ። ይህም አንድ የሥራ ርምጃ ነበረ ። ያቀረብን ላቸውን ሥዕላዊ መረጃ ተመልክቶ ዳር - እስከ ዳር የሚያ ስተጋባ ድል ለመጐናፀፍ የማይጓጓ የጀርመን ሰላይ ይኖ ራል ብለን አልተጠራጠርንም ነበር ።

የመረጃ ክፍል ኃላፊዎች እንደ ጲላጦስ እጃቸውን ሲታጠቡ በሐሳብ ታይቶናል ። እስፐይን ውስጥ ያደረጉት ክፍላቸውን የስለላ ትጋትና ጥረት ውጤት ችላ ሊሉት እንደማይችሉ አረጋግጠናል ። የጀርመን የመረጃ ክፍል ኃላፊ የነበረው አድሚራል ካናሪስም የሚመከበቱ ሙያ ውና ከእስፐይን ባለሥልጣኖች ጋር የነበረው ወዳጅነቱ እንደ ጥዋት ጤዛ እንዲረግፍ እንደማይገባ አትኩረን አስ በናል ። ባለፉት ዓመታትም ቢሆን የእንግሊዝና የአሜሪካ የጦር መርከቦች እንቅስቃሴ በሰላዮች እየተቀነባበረ ለበር ሊን ሲቀርብላት የነበረው በማድሪድ በኩል ነበር ። ሌላው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንኳ ቢቀር በጅብርላታር አካባቢ በኩል የነበረን የባሕር ኃይል ንቅናቄ ሁኔታ ማደራጀ ይደርስ እንደ ነበረ እናው ቃለን ። ይህን የመሳሰለው አገልግሎት በዚያ አካባቢ ከነበረው የስለላ ቅርንጫፍ ሁሉ የሚጠበቅ እንደ ነበረ ግልጽ ነው ። ይሁንና ከዚያ ጊዜ ቀደም ብሎ ፣ የሰሜን አፍሪቃን ጦርነት ከመጀመራችን በፊት የጀርመኖች የመረጃ ድርጅት በስሕተት የፈጸመው ጉዳይ ነበረው ። የሰሜን አፍሪቃ ጦርነታችን በጀርመኖች ዘንድ ድንጋጤ እንደ ፈጠረባቸው ተረድተናል ። በመጨረሻ ግን የድል ክብር የሚቀዳጁበት አጋጣሚ ቀርበላቸዋል ። ከምክትል የጦር የበላይ አዛዥ በጦር ግንባር ለነበረ የጦር አዝማች የተጻፈ ከፍተኛ ምሥጢር የያዘ ጽሑፍ አግኝቶ ለጦር ኃይሉ እዝ ክፍል ማቅረብ ለማንም ሃገር ሰላይ ቢሆን ሀልውናውን የሚያስምርበት የሃገር ወዳድነቱን የሚገልጽበትና ታታሪነቱን የሚያስመሰክርበት መሆኑ የማይካድ ነው ። እኛ እንደ ጻፍነው ያለ ወሬ ተገኝቶ እርምጃ ሲወሰድበት ወደ ጥፋት ወይም በተባበሩት መንግሥታት ጦር ላይ በዚያ በአወዛጋቢው የውጊያ ሰዓት ጠቅላላ ውድቀት ማስከተሉ የማይካድ ነው ። ይህም ነገር ጠቅላላውን የዓለም ሁኔታ የሚለዋውጠው እንደሚሆን አይካድም ነበር ።

ስለዚህ ነበር በጉዳዩ ያን ያህል ስጨነቅበትና ስሠቃይበት የነበረው ዝቅተኛ ማዕረግና ሥልጣን በነበራቸው መኰንኖች አማካይነት ወረቀቱ እንዲጻፍና ወሬው አፈት



t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ ለጀርመን ሰላዮች እንዲደርስ የታሰበውን እቅድ አጥ
ብቄ የተቃወምኩት ውጤቱን አትኩሬ በመመልከት ነበረ።

የሸለቃ ማርቲን ይዘት የዘመተው ወረቀት በበታች መኰንኖች ተጽፎና ተፈርሞ ቢሆን ኑሮ ነገሩን በመጀመሪያ እስፓንሾች ችላ ይሉትና ለጀርመኖችም አያስተላልፉትም ነበር። ቢደርሳቸውም እንኳ ኑሮ፤ የጦር ስልታቸውን በሚያቀነባብሩበት በዚያ ሰዓት በዚያ ደብዳቤ ላይ እምነት አሳድረው ከውሳኔ ላይ መድረሳቸው አጠራጣሪ ሊሆን ይችል ነበር። ግን ሰር አርችባልድ ነይ ለጀኔራል አሌክሳንደር የጻፉት ከሆነ፤ እውነተኛ መስሎ መገመት ነበረበት። የእንግሊዝ መንግሥት የጦር ኃይል ም/ኃላፊ ሆኖ የተባበሩት መንግሥታት ጦር የነበረውን እቅድና ሐሳብ ወለል አድርጎ ማወቅ ነበረበት። ራሱም "በማስመሰያ ዘመቻ" እንዳይደናቀፍ መጠንቀቅ ይገባው ነበር።

እነዚያን ደብዳቤዎች የጀርመን ሰላዮች አኝከው የዋጡልንም እንደሆነ በትክክለኛ ማስረጃነትም የተቀበሉን እንደሆነ፤ ማነኛውም የጦር አዛዥና የውጊያ ስልት አቀነባባሪ ቢሆን በነዚያ መረጃዎች ላይ እምነቱን አሳርፎ የጦርነት ዘዴውን ከማቀነባበር አቅጣጫውን ከመቀየስ ችላ እንደማይልና የራሱን የመረጃ ሥራ ውጤት የማይቀበል ይሆናል ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ነበረ። በዚህ እምነት መሠረት እኛም በትዕግሥት መጠባበቅ ጀመርን። ትዕግሥታችን ጣፋጭ ፍሬ መስጠት ጀመረች፤ "የሐስኪ ዘመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቻ" ቀን መጣች ። ውጊያውም በተቃና ሁኔታ መካሄድ ጀመረ ።

ሲሲሊይ ገሚስ አካባቢዋ ሐምሌ ፲ ቀን በጥዋት በተ ጻበሩት መንግሥታት ጦር ተያዘ ። ግሥገሳው እየተቀላ ጠፈ ሄደና ማእከላዊ ግዛቷ ሁሉ ተወረረ ። ለዚህ እርምጃ ያበቁን ሌሎች ብዙ አስደናቂ ጉዳዮችም ነበሩበት ። ለም ሳሌ እንደ ባሕሩ ሞገድና የጨረቃዋ ብርሃን የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሁኔታዎችም ከዘመቻው እቅድ ውስጥ ተደም ረዋል ። ግን "የማስመሰያው ዘመቻ" ውጤት በሥራ ላይ ሲገለጥና የኛም አነስተኛው ድካማችን ፍሬ ሲያስገኝ ያቀ ነባበርነውን የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሁኔታ ሁሉ በዘመ ቻው ድልን የተጐናጸፉት የጦር ኃይሎች ምንም አልመ ሰላቸውም ነበር ።

ይህም እየተረጋገጠ የሄደው የመረጃ ክፍል ሪፖር ትና የተገኘው ጽሑፍ ሲስሊይ ውስጥ መጣራት ከተጀ መረ ወዲህ ሆነ ። ጀርመኖች የሲስሊን የጦር ሠፈራቸውን በማደራጀት ላይ ይገኛሉ የሚልም ጥርጣሬ ብጤ ነበረ ። ይህም ይሆናል የተባለው (እኛ በገባንበቱ) በደቡብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ነበር ። ያም ሠፈራቸው እኛ ሳርዴኒያን ለመውረር በዘመቻ ላይ ሳለን አቅጣጫችንን ለውጠን ቢ ሆን ኑሮ በእርግጥ አሰቃቂ እልቂት ሊያደርሱብን ያስችላ ቸው ነበረ ። በጠቅላላው አገላለጽ ግን በሲስሊ ውስጥ የነበረው የጀርመኖች ኃይል ከአሰብነው በታች ያነሰ ሆኖ ነው ያገኘነው ።


t.me/OLDBOOKSPDF

በመረጃ በኩል የሆነ እንደሆነ ግን የኛው የማታለሉ ዘዴ ሙሉ ለሙሉ ውጤት እንደሰጠ ተረጋገጠ። ይህን ኑም ነገር አድሚራል ካኒንግሃም "እጅግ እስገራሚውና በከፍተኛ ጥንቃቄ የተቀነባበረው የማስመሰያ እቅድ የተፈለገውን ውጤት ሰጥቷል" ብለው አረጋገጠዋል።

የፈጸምነው ረቂቅ የማታለል ዘዴ ሁሉ ጦርነቱ ካለቀም በኋላ፤ ቢሆን አልተገለጸም ነበር።

አንድ ቀን ጧት በክፍሌ ውስጥ ሆኜ የሠራሁትን ተግባር እያስታወስኩ እንሰላስላለሁ። ማንሰላሰል ብቻም ሳይሆን የፈጸምነውን ነገር በማስታወሻ እጽፋለሁ። ሐሳቤም ተተኪዎቼ ወራሾቻችን ችኩሎችና ያለፈ ነገር ለማንበብ ጊዜ የማይኖራቸው (ወይም ዋጋ ቢስ ነው ብለው እያነቡት ይሆናል)፤ የጦር መሪዎቻችን እንዲያነቡትና ዕውቀታችንንም እንዲወርሱ አቀነባብራለሁ በተራችን የሃገሪቱን የመከላከያ ኃይል ያገለገልነውም ከየክፍላችን ተሰናብተን በአንድ ላይ ሆነን የምንጫዋወትበትን ጊዜ በመናፈቅ ላይ እንዳለሁ ስልኩ አቃጨለ። የደወለውም የባሕር ኃይላችን ም/የመረጃ ዲሬክተር ነበር። አነጋገሩ በሳቅ ተውጦ ስለ ነበረ፤ ምን እንደሚል ሊገባኝ አልቻለም ነበር። ግን ወደ ጽ/ቤቱ እንድሄድ መፈለጉን ተረዳሁ።

ወደዚያም ስሄድለት ሰውዬው አሁንም በሳቅ ሞቅታ ተውጦ ይንከተከታል። ቢሆንም ጽሑፎች ሰጠኝ። እነዚያንም ጽሑፎች ስመለከታቸው የኛዎቹ "የማታለያው



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዘመቻችን" ወረቀቶች ሆነው አገኟቸው። ጀርመኖች አግኝተዋቸው ኑሮ ከእንግሊዝኛ ወደ ጀርመንኛ ተርጉመዋቸዋል። እዎ ደብዳቤዎቹ ረጅሙን ጉዞአቸውን ፈጸሙ። ም/ዳሬክተሩ በሳቅ የሰከረበትን ምክንያትም ገለጸልኝ።

ታምበች በምትባለው የጀርመን መንደር ውስጥ የተያዘውን (የተማረከውን) ቤተ-መዛግብት አንድ የኛ መኰንን ይመረምር ኑሯል። ያም መኰንን አንድ ቀን ጧት በጭንቅና በኀዘን ተውጦ ወደ ም/የመረጃ ዳሬክተር ጽ/ቤት ይሄዳል። ያገኘውን መረጃ ለማቅረብ ፈቃድ ጠየቀና እንደሚከተለው ይገልጽለታል።

ሲፈትሻቸውና ሲያገላብጣቸው በነበሩት መዛግብት ውዕጥ ሁለቱን መሠረተ ምሥጢር ጽሑፎች ያገኛል። በዚህ ጊዜ ምሥጢሮቻችን በሙሉ ሲባክኑ እንደ ኖሩና ፀጥታችን እንዳልተጠበቀ ያህል ይገምታል። ጠላቶቻችንም በጦርነቱ ጊዜ ምሥጢሮቻችንን ሁሉ እያስሾለኩ ሲያግዙዋቸው እንደኖሩ ይረዳል። ስለዚህ ማናቸውንም የምሥጢር ሰነድ ሁሉ የባሕር ኃይላችን የመረጃ ኃላፊ ወይም በእርሱ ደረጃ ያሉ ከፍተኛ መኰንኖች እንዲጠብቁ ሐሳብ ያቀርባል።

የመረጃው ክፍል ኃላፊም ደብዳቤዎቹንና ታሪካቸውን ስለሚያውቀው በጭንቅ ሐሳብና ስጋት ተውጦ የነበረውን መኰንን ያጽናናዋል። ከዚያ በኋላ ሁለቱ የምሥጢር ደብዳቤዎች በተገኙበት መዝገብ ቤት ውስጥ ፍለጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ችንን በመቀጠላችን ሌሎቹን ማስረጃዎች ጭምር ስለ እ?
ኝን በጀርመን የመረጃ ድርጅት አቋም ላይ ድል ተጐናጽ
ፈን እንደ ነበረ ተረዳነው ። አስቀድመን ተስፋ እንዳደረግ
ነውና እንዳቀድነው እነዚያን መሠረታውያን የምሥጢር
ደብዳቤዎቻችንን ጀርመኖች ካገኙዋቸው በኋላ፣ እንደ
እውነተኛ ማስረጃ ይቈጥሯቸውና ጊዜ ሳያባክኑ ለጦር
ኃይላቸው አቅርበው የዘመቻ ስልታቸውን ያቀነባብራሉ ።

በግንቦት ወር መጀመሪያ ሳምንት ላይ ማድሪድ የነበ
ረው ሰላያቸው ስለ ደብዳቤዎቹ መገኘትና ስለ ምሥጢር
ነታቸውም ዝርዝር ወደ በርሊን ቴሌግራም አስተላልፎ
ኑሯል ። ይህንም ለማረጋገጥ ያስቻለን የዋናዎቹ የምሥ
ጢር ደብዳቤዎች ቅጅ በርሊን ከመድረሱ በፊት ግንቦት
፱ ቀን ለጀርመን የጦር ድርጅቶች ሁሉ ስለ ተባበሩት መን
ግሥታት ጦር የንቅናቄ ዝንባሌ የሚገልጹ ቴሌግራሞች
ተላልፈው እንደ ነበረ ማስረጃ በማግኘታችን ነበር ።

በርሊን የነበረው የጀርመን የመረጃ ሥራ ድርጅት
የደብዳቤዎቻችን ዜና እንደ ደረሰው፣ ወዲያውኑ እኛ
ስንጠባበቅ በነበረው መሠረት በቂ ማስረጃ እንዲላክለት
ወደ ማድሪድ ጥያቄ ካስተላለፈ በኋላ ዝርዝር ጉዳዩ ተከ
ታትሎ ይደርስለታል ። ይህም የሚያመለክተው ተጨማ
ማሪ የማስረጃ ማስረጃ ለማግኘት ጥረትና ፍላጎት ነበረ
ማለት ነው ። ግን ጊዜው የተወሰነ ስለ ነበረ፣ ከማድሪድ
የተላለፈውን ዜና በርሊን እንደ አጥጋቢ ማስረጃ ትቀበለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋለች ። በዚያም መሠረት የጦርነት እቅዳቸውን ያወጣሉ ። በመጀመሪያ እንደ ትክክለኛ ማስረጃ የተቈጠረው ሰር አርችባልድ ነይ ለጀኔራል አሌክሳንደር የጻፉት የምሥጢር ደብዳቤ ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ይተረጐምና ከአባሪ ጋር ይያያዛል ። ቀኑም ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ተብሎ ይጻፍና በላዩም ላይ "እጅግ ብርቱ ምሥጢር" ተብሎ "በግል የሚሰጥ እንጅ በማደያ ክፍል በኩል የማይተላለፍ" ተብሎ ይጻፍበታል ። እንዲሰጥ የተጻፈበትም ለጀርመን የበሕር ኃይል ዋና አዛዥ ለአድሚራል ዶንቲዝ ነበር ። ስለዚህ ግንቦት ፲፫ ቀን የአድሚራሉ ም/አዛዥ የነበረው በሰማያዊ ቀለም ምልክት ያደርግበትና አድሚራሉ ብቻ እንዲመለከተው ያስተላልፈዋል ።

አድሚራሉ ሙሶሊኒንና ሂትለርን አነጋግሮ ወደ ጠቅላይ ጽ/ቤቱ እንደ ተመለሰ ደብዳቤውን እንዲመለከተው ሁኖ ይቀመጥለታል ። ተያይዞ የነበረው ደብዳቤ ደግሞ የሚከተለው ነበር ። ጉዳዩ በሜዲትራኒያ ንቅናቄ ከጠላት የተያዘ ጽሑፍ ።

ከዚህም ጽሑፍ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘው ፤

ሀ) ከእንግሊዝ መንግሥት የጦር እዝ ጽ/ቤት ለጀኔራል አሌክሳንደር የተጻፈ ።

ለ) እንዲያውቁት ለጀርመን ጦር አጠቃላይ የበላይ መኰንን ።

ከምሥጢር ጽሑፎቹ ጋር የተያዙት ሌሎች ጽሑፎች

t.me/OLDBOOKSPDF

አስፈላጊያችን አይደሉም ። መሠረተ ሐሳቡ እንደሚከተ ለው ነው ።

፩ኛ የተያዙት የምሥጢር ደብዳቤዎች ትክክለኛነት የማያጠራጥር ነው ። ሆን ተብሎ በኛ እጅ እንዲገቡ ታስቦ የተጻፈም ይሆናል ፣ የሚለውን ሐሳብ ሙሉ ለሙሉ ለመ ቀበል አዳጋች ነው ። እነዚህ የምሥጢር ጽሑፎች በኛ እጅ መግባታቸውን ወይም በባሕር ላይ መጥፋታቸውን ጠላቶቻችን ተረድተውት እንደሆነ በማለት ክትትል ተደ ርጎበታል ። እነዚህም ደብዳቤዎች በኛ እጅ ለመግባታቸው ጠላት ለማወቅ አይቻለውም ። በዚህ አንጻር ደግሞ ደብ ዳቤዎቹ ወደ ተላኩበት ቦታ ያለመድረሳቸውን ጠላት ሊያውቅ ይችላል ።

፪ኛ ጠላት አስቀድሞ ያወጣውን የዘመቻ እቅድ ለመ ለወጡ ወይም በሥራ ላይ ለማዋል እንቅስቃሴውን ለመ ጀመሩ በጥብቅ የሚታሰብበትና የሚጠና ጉዳይ ነው ። ግን የሚሳካለት አይመስልም ።

፫ኛ የዘመቻው አሻሚ ቀን ።

ጉዳዩ በአስቸኳይ ተጠንቶ ውሳኔ የተሰጠበት ነው ። ቢሆንም እስከ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ድረስ ጊዜ ስለ ነበረ ፣ በምሥራቅ ሜዲትራኒያ በኩል ጦርነቱን ለመጀመር እን ዲቻል ሲስሊን የማስመሰያ የዘመቻ ቦታ አድርጎ ማሳየት ያስፈልጋል ሲል ጀኔራል ዊልሰን ያቀረበውን ሐሳብ ጀኔ ራል አሌክሳንደር እንዲያውቀው መልእክት በአየር ለማ ስታላለፍ ይቻላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሌክሳንደርም በዊልሰን ሐሳብ የሚስማማ ለመሆኑ መልስ እንዲሰጥ ተጠይቆበታል ። በዚያም ደብዳቤ ላይ "ጉዳዩን ማራዘምና ቀኑን ማስተላለፍ አንችልም" ተብ ሏል ። በዚህ መሠረት የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ እዝ የበ ላይ መኰንን በምሥራቅና በምዕራብ ሜዲትራኒያ በኩል የውጊያ እቅዱን ለማውጣት በአማራጩ መሥመር ላይ ገና ያስብበታል ለማለት ያመቻል ።

፩ኛ ተከታታይ ጦርነት ።

ጦርነቱ በሁለቱም ግንባር ይከፈት ይሆናል ። ሲስሊ ለማታለያ እቅድ ምቹ ካልሆነችላቸው በአንድ ጊዜ ሁለት የጦር ግንባር እንደሚከፈቱ ይታመናል ።

፩ኛ በምሥራቅ ሜዲትራኒያ በኩል ጦርነቱን ለመጀ መር ሲባል የቱብሩክ ቀበሌ ጉዳይ እንደሚታሰብበት አይ ከድም ። በዚህ ምክንያት ሲስሊ የማታለያው እቅድ መሸ ፋፈኛ እንድትሆን አሌክሳንደሪያ የሠፈረው ጦር ላይ ለማ ሳሰብ ወይም ምክንያት አድርጎ ለማቅረብ አይቻልም ።

፪ኛ የማታለያው እቅድ ዘመቻው እስኪጀመር ድረስ የማስመሰያ ዘዴ በማቅረብም ብቻ እንደሆን አይታወቅም ወይም ደግሞ የማስመሰያው ዘመቻ እንደ ዋናው ጦርነት ይገመትም እንደሆን ለመለየት አስቸጋሪ ነው ።

፫ኛ ተያይዞ ከተገኘው ጽሑፍ ላይ ለመረዳት እንደ ሚቻለው ፩ኛውና ፻፷ኛው ክፍለ ጦር በምሥራቅ ሜዲ ትራኒያ በኩል ለመግባቱ በሚገባ ተብራርቶ አልተገለ

t.me/OLDBOOKSPDF 

ጿም ። (በታምቹም አራክሰስና ከላማታ) ናቸው ። ቢሆንም እነዚህ ሁለት ክፍለ ጦሮች ለውጊያው ተጨማሪ ኃይሎች መሆናቸው ነው ። ስለ ተባለም የውጊያው ተከፋይ የሚ ሆኑት የጦር ኃይሎች የእነዚሁ ክፍሎች ተጨማሪዎች ለመሆን ይችላሉ ።

፰ኛ ከተያዙት ጽሑፎች ላይ ለመረዳት እንደሚቻ ለው በምሥራቅ ሜዲትራኒያ አቅጣጫ ከፍተኛ የጦር ኃይ ል ዝግጅት እንደሚደረግ ታውቋል ። ዋናው አስፈላጊው ጉዳይም ይኸው ነው ። ምክንያቱም ከአልጀሪያ ይልቅ ከዚሁ ቀበሌ ግምት ያላቸው መረጃዎች ስለሚደርሱን የሠፈራቸውን ጠቅላላ ሁኔታ ለመረዳት እንችላለን ።

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ንባብ የጀርመን የመረጃ ክፍል ጠበብት የሰጡት ትንተና ነው ።

በዚህ መሠረት የጀርመን የመረጃ ክፍል ባዘጋጀን ለት የማታለያ ዘዴ ላይ ራሱን እንደሠዋበት ሊያስረዳን የቻለው "የተያዙት ደብዳቤዎች ትክክለኛነት የማያጠራ ጥር ነው" ሲል መተቸቱ ነበር ። ነገሩን በይበልጥ ለመከ ታተል ማሰባቸውን ከገለጹ በኋላ ፣ ደግሞ "የማታለል ነገ ር ሆነ ተብሎ የተጠመደ ተንኰል ይኖራል ብሎ ለማሰብ አጠራጣሪ ነው" ብለው ሐሳባቸውን ውድቅ አድርገው ታል ። እኛም እቅዳችንን ለመለወጥ እንደማይቻለን የጦር ነቱንም ቀን ለማራዘም እንደማንፈልግ ግምት አሳድረዋል ።

የጦርነት እቅድ በማውጣትና ያን እቅድ በሥራ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

በማቀል ረገድ ያለውን የተወሳሰበ ጉዳይ የሚያውቅ ማን ኛውም ሰው ቢሆን በመጨረሻ በጀርመን የመረጃ ድርጅት ትንተና እንደሚስማማ አይክድም ።

ይህን የመሰለ የማታለል ተግባር ለመፈጸም ሲፈለግ እንደ ሥዕላዊ ነጥብ ሆኖ የሚቀርበው ሌላው ጉዳይ ደግሞ አታላዩ በጠላቱ አእምሮ ውስጥ ሊቀረፅ የሚችል ፍሬ ነገር ማቅረብ እንደሚኖርበት በተራ ቊጥር ፫ የተገለጸው ትንተና ጥሩ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ። አሌክሳንደሪያ ላይ የሠፈረውን ጦር ወደ ሲስሊ እንደሚዘምት አስመስሎ ለማቅረብ የሃገሩ ርቀት ችግር እንደሚሆንብን ጀርመኖች ገምተዋል ። ግን አሌክሳንደሪያ የነበረው ጦራችን ሲስሊን ለመውረር ርቀቱ እንደማያሰናክለው ለኛ የጦር ስልት አቀነባባሪዎች ግልጽ ነበር ። እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ ይኸው ጦር ነበር ዘመቻውን ያከናወነው ። በዚህ ዓይነት የጀርመኖችን ግምት ወይም ውሳኔ መዘርዘር አያስፈልገኝም ። በሚቀጥለው ንባብ የምናገኘው ነውና ። ግን የምሥጢር ደብዳቤዎቻችን ቃል በቃል ሲጠኑ እንደ ነበረ ለማረጋገጥ ወደፊት እንደርስበታለን ።

ግንቦት ፲፫ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. የጀርመን የመረጃ ድርጅት ያስተላለፈው ሪፖርት የሚከተለው ነበር ።

ጉዳዩ የእንግሊዝ መንግሥት የምሥጢር ጽሑፍ በሂውልባ አከባቢ በባሕር ላይ ስለ መገኘቱ ።

የሚቀጥለውን ፍሬ ነገር ከብዙ ዓመታት ጀምረን ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ኙነት ከነበረን የእስፐይን የጦር መኰንን ከሆነ ፤ በለሥል
ጣን ጋር ተነጋግረንበት ያጣራነው ነው ።

፩ኛ ከሬሳው ጋር ከነበረው ቦርሳ ውስጥ የሚከተ
ሉት ጽሑፎች ተገኝተዋል ።

ሀ) በአንድ ተራ ወረቀት ውስጥ ተጠቅልለው የነበሩት
ወረቀቶች ለጀኔራል አሌክሳንደርና ለአድሚራል ኳኒንግ
ሃም የተጻፉ ናቸው ። ደብዳቤዎቹ ተጠቅልለውበት በነበ
ረው ወረቀት ላይ ግን ፤ ምንም አልተጻፈበትም ። ሦስቱም
ደብዳቤዎች በ፫ ፖስታዎች ውስጥ ነበሩ ። በያንዳንዳቸ
ውም ላይ የባለ አድራሻዎቹ ስም ተጽፎባቸዋል ። የላኪዎ
ቹም ምልክት አለበት ። ምልክቶቹ ተለይተው የሚታወቁ
ነበሩ ። ደብዳቤዎቹን ራሴ አግኝቻቸው ተመልክቻቸዋ
ለሁ ። በሚገባም ሁኔታ ተመልሰው በየፖስታዎቹ ገብ
ተው ታሽገዋል ። ደብዳቤዎቹን ለመገልበጥ እንዲመቹን
ብለው የእስፐይን ባለሥልጣኖች በሰው ሠራሽ ሙቀት
ከፖስታዎቻቸው አውጥተው እንደገና በጥንቃቄና በሚያ
ጣብቅ ቅመማ ለማሸግ ፳፬ ሰዓት ፈጅቶባቸዋል ። እንደገና
ተጣጥፈው ወደየፖስታዎቹ ሲገቡም በከፍተኛ ጥንቃ
ቄና እንደ ነበሩ ሆነው ነው ።

ለ) በቦርሳው ውስጥ ደግሞ የተገኘው የአትም እር
ማት ሚያዝያ ፳፱ ቀን ማውንትባተን ስለ ጠቅላላው የጦር
ኃይል ጠቅላላ እንቅስቃሴ የጻፈው ለመሆኑ ተጠቅሶበ
ታል ። ፎቶግራፍም ነበረበት ። የአትሙ እርማት በመል



t.me/OLDBOOKSPDF

ከም ሁኔታ ላይ ሲገኝ ፎቶግራፉ ግን የተድበሰበሰ ነበር ።

፪ኛ ሰውዬው (መንገደኛው) በደረት ኪሱ ልዩ ልዩ የግል ወረቀቶችን ይዟል ። የራሱም የውትድርና መታወቂያዎች ነበሩበት ፤ (ከዚህም ላይ መረዳት እንደ ተቻለው ማውንትባትን ሚያዝያ ፳፱ ቀን በጻፈው ደብዳቤ ላይ የመንገደኛው ሰውዬ ስም የሻለቃ ማርቲን መባሉን ጠቅሶታል) በተጨማሪም ከፍቅረኛውና ከአባቱ የተጻፉለት ደብዳቤዎች ሚያዝያ ፳፯ ቀን ለንደን ውስጥ ከማታ ክበብ የተሰጠው ደረሰኝ ሁሉ ናቸው ።

ሻለቃ ማርቲን ከለንደን የተነሳው ሚያዝያ ፳፰ ቀን ሲሆን በዚሁ ቀን ከባሕር ላይ አይሮፕላኑ በመውደቁ ሬሳ ውም እየተንሳፈፈ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ወደ ሂውልባ የባሕር ዳርቻ ደርሷል ።

፫ኛ ሬሳው እንደተገኘ የእንግሊዝ ቆንሲልም ተጠርቶ ሁኔታው ተነግሮታል ። ከሬሳው ጋር የተገኙት ደብዳቤዎችና ግላዊ ጉዳዮች እንዲመለሱለት ቆንሲሉ ያቀረበው ጥያቄ በምክንያታዊ ዘዴ ችላ ተብሎ ደብዳቤዎቹ ለእስፐይን ባለሥልጣኖች እንዲቀርቡ ተደርጓል ።

ደብዳቤዎቹ ከየፖስታዎቻቸው ወጥተው ከተገለበጡ በኋላ፤ እንደገና ታሽገው ሲሰጡ ፖስታዎቹ እንደ ተከፈቱ ሆነው፤ ጥርጣሬ እንዳያሳድሩ ለመደረጉ ራሴ አረጋግጫለሁ ። ደብዳቤዎቹንም የእስፐይን የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች ለእንግሊዞች በዛሬው ቀን ይመልሳሉ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በባሕር ላይ እንደ ወደቀ የታመነበቱን አይሮፕላን ሲያበር የነበረው ፓይለት (አብራሪው) የት እንደ ደረሰ እንዲጣራ የአስፐይን የጦር ኃይሎች እዝ ክፍል ጠይቋል። ምናልባትም በአይሮፕላኑ ውስጥ ሌሎች መንገደኞችም ይኖሩበት ይሆናል ተብሎ ፍለጋውና ክትትሉ ቀጥሏል። (ይላል ሪፖርቱ) ይህን ጽሑፍ ስንመለከተው እጅግ ተደ ንቀንበታል። ስለ ሻለቃ ማርቲን የፈጸምነውን ጥንቃቄ ሁሉ መርምረው ጀርመኖች ተቀብለውናል።

እንግዲህ የመኰንኑ እውነተኛነትና አብሮት የነበረ ውም ደብዳቤ ትክክለኛነት በጀርመኖች ዘንድ ተረጋገጠ ልን ማለት ነው። ከደብዳቤዎቹም ውስጥ አስፈላጊ የነበ ሩትንና ያልነበሩትን ለይተው አውቀዋቸዋል። እምነታ ችን የቱን ያህል ተስተከከሎ ከዒላማው እንደ ደረሰ ያመ ለክታል። ጠቅላላው የዘመቻው አቋዋማችንም ያረፈው በዚያው በእምነታችን ላይ ነበር። ጀርመኖችን ከሙሉ ልባቸው የሚያሳምንልንም ሆኖ ተገኝቷል። ከእስፔይን ተወላጅ እጅ ከገባ ጀርመኖችን እንደሚያባብልልን አስቀ ድመን ተረድተነው የነበረው ጉዳይ ሁሉ ተቀላጠፈልን።

ከሻለቃ ማርቲን ሬሳ ጋር በሰንሰለት እንዲቄራኝ ያደ ረግነው ቦርሳ የሚታመንም ሆነ አልሆነ እኛን የሚያስጨ ንቀን አልነበረም። ብቻ ከሬሳው ጋር በርሳ ለመገኘቱ ጀርመኖች እንዲሰሙልን (እንዲያውቁልን) እንፈልጋለን። እዚህ ላይ ለአሰብነው ጉዳይ መቃናት ምክንያት ከሆኑት

t.me/OLDBOOKSPDF 

ነገሮች አንዱ የእስፔናውያንና የጀርመኖች ወዳጅነት የተቀለጣጠፈ ያለመሆኑም ነው።

በተራ ቍጥር ፩-ሀ ክፍል የተገለጠው "ፖስታዎቹ ተጠቅልለውበት በነበረው ነጭ ወረቀት" ጉዳይ የማውቀው ነገር አልነበረኝም። በዚያ ነጭ ወረቀት ፖስታዎቹን የጠቀለሉበት እስፓንኞች ሳይሆኑ አይቀሩም። ምክንያቱም ከቦርሳው ውስጥ የነበረው የእትም እርማት እንዳይቃወስ ብለው ይሆናል። የሆነ ሆኖ ፖስታዎቹን እኛ አልጠቀለልናቸውም። ፖስታዎቹ ሲታሹ የታተመባቸው ምልክትም የሮያል የጦር ኀይል ማኅተም ነበር። የሻለቃው የግል ደብዳቤዎችም ተመርምረው ኑሯል። ከእጮኛውና ከአባቱ የተጻፉለት ደብዳቤዎች ባለ መጥፋታቸውም ተደስተናል። በተራቀቀ ችሎታ የተከናወኑት ሥራዎች ከንቱ አልቀሩምና። እንደዚሁም ደግሞ ሎርድ ማውንትባትን ለአድሚራል ከኒንግሃም የጻፉት ደብዳቤ የሻለቃ ማርቲንን ማንነት ለጀርመኖች በትክክል አስተዋውቆልናል። ይህ ሥዕላዊ ሪፖርት የሚታለሉን ነገር ሲመረምር ከፍተኛ ችግር ሊደርስበት ተቃርቦ ነበር። ምን ጊዜም ቢሆን አታላዩ ወገን ማስረጃዎች ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች አቅርቦ ተታላዩ ወገን በራሱ ምርጫ እንዲቀበለው መጣጣር አለበት። ምን ጊዜም ቢሆን ቅልጥፍናና አስተዋይነት ያለበት ችሎታውን አቅርቦ ተታላዩን ወገን ማባበል ይኖርበታል። ስለዚህ ለጀርመን የመረጃ ክፍሎች



t.me/OLDBOOKSPDF

ያቀረብንላቸው ማስረጃም ሁሉ የእነርሱን ምርጫ የሚጠ ይቅ እንደ ነበረ ተሰምቶኛል ። ግን ችሎታቸውን እጅግ በከፍተኛ ደረጃ መዝነነው ነበር ፤ ይህን ለመናገር ያስደፈ ረኝም ሁለት ጉዳዮች በግዴለሽነት ተሳስተው በመፈጸማ ቸው ነው ። ሁለቱም ስሕተቶች ስለ ቀናት ጉዳይ ነበሩ ። ጀርመኖች በተረጐሙት ሎርድ ማውንትባትን ሚያዝያ ፳፬ ቀን ለአድሚራል ካኒንግሃም በጻፉት ደብዳቤ ላይ ቀኑ ተለውጧል ። ይህም የሆነው ሲተረጐም ወይም ሲገለበጥ ሊሆን ይችላል ። በ፳፩ የተጻፈው የተለወጠውም ሚያዝያ ፳፬ ቀን ተብሎ ነበር ።

ይህ እንኳ ቀላል ነው ተብሎ ቢታሰብም ሁለተኛው ስሕተት ግን ከባድ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነበር ። በማስረጃነት ተጠቅሶ በቀረበው ትችታቸው ላይ "ሚያዝያ ፳፯ ቀን የለንደን የማታ ክበብ ሒሳብ መጠየቂያ" ይላል ። ይህም የሆነው የትያትር ቤቱን ቲኬት ሲያነቡ በግዴለሽ ነት የታለፈ ነው ለማለት አስችሎናል ። ወደ መደሰቻው ክበብ እንዲሄድ የተጠራበቱ ወረቀት የሒሳብ መጠየቂያ ነት ቀርቶ ቀንም እንኳ አልተጻፈበትም ነበር ።

ሻለቃው በባሕር ኃይልና በጦር ሠራዊት ክበብ ብዙ ቀናት ለመቈየቱ የሚያረጋግጥለት ሚያዝያ ፳፬ ቀን የተ ጻፈለት የሒሳብ መጠየቂያ ሊሆን አይችልም ነበር ። ያ ወረቀት የማታ ክበብ ሒሳብ መጠየቂያ ሆኖ ሊቈጠር እንደማይቻል ሁሉ እስፓንሾችም እንኳ ቢሆኑ የማታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከበብን መግባትና መውጣት ሊሳሳቱ አልቻሉም ነበር ። ስለዚህ ያ ስሕተት ሊደርስ የቻለው ከሚልስ ልዑል ትያትር ቤት የተቀበልነው የመግቢያ ወረቀትና የማታው ከበብ የጥሬ ወረቀት ሲነበቡ በጥንቃቄ ባለመታየታቸው በሁለቱ ምክንያት የተፈጠረ የንባብ ስሕተት ነው ብለን ገምተናል ። ጉዳዩ ቀላልም ቢሆን የቀናቱ መለዋወጥ ጥር ጣሬ አስነስቶ ከባድ ችግር ሊቀሰቅስ ይችል ነበር ።

የጀርመን የመረጃ ክፍል ሪፖርት ጉዳዩን ያጠቃለለው እኛ ባቀድነው መሥመር ገብቶ ነው ። ይህም የሻለቃ ማርቲን ከለንደን የተነሳው የመሰነባበቻ ግብዣ በተደረገለት ቀን ነው ተብሎ ነበር ። ስሕተቱ ያመጣው የስሕተት ለውጥ ደግሞ ፤ "ሚያዝያ ፳፫ ቀን ጥዋት ከለንደን ተነስቶ አይሮፕላኑ ሂውልባ አጠገብ በመውደቁ ሬሳው ተገኝቷል" ተብሎ ተገልጿል ። እዚህ ላይ የእስፔይኑ ተወላጅ የሆነው ዶክተር የሰጠውን የምርመራ ውጤት ጀርመኖቹ አላስተዋሉትም ። ሂውልባ የነበረው ሰላዮቹ ውም ቢሆን የሐኪሙን ትንተና ሊያውቀው ይገባው ነበር ። ሰውዬው ከለንደን ስለ ተነሳበትና ስለ ሞተበት ቀን ልዩነት ሊጠራጠሩ በተገባቸው ነበር ። የእስፔይኑ ዶክተር ሰውዬው የሞተው ቀደም ካሉ ቀናት በፊት ሲሆን ሬሳው ሚያዝያ ፴ ቀን መገኘቱን ገልጿል ። በዚያም ጊዜ ሰውዬው የሞተው ቢያንስ ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት እንደሆነ አስረድቷል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ትንተና መሠረት ለሻለቃ ማርቲን መሞት ምክ ንያት የሆነው አይሮፕላን አባሕር ላይ የወደቀው ሚያ ዝያ ፳፩ ቀን ገደማ መሆን ይኖርበታል ። ከዚህ አገላለጽና ትንተና ምን ውጤት እንደሚገኝበት ለመግለጽ ችሎታ ያለኝ ፈላስፋ አይደለሁም ። እኛ ዕድለኞች ሆነን ነገሩ ተድበስብሶ ቃለፈ እንጅ በጥንቃቄ ተወያይተውበት ቢሆን ኑሮ የማቃለሉ አቅዳችን ጉድ ይፈላበት ነበር ።

ይህን ሊደርስ ይችል የነበረ አጋጣሚ ላለመቀበል አልደፍርም ። እኛ በፈለግነው አቅጣጫ ሁሉ ምርጫቸ ውን እንዲወስኑ ለእስፓንሾችና ለጀርመኖች ማነኛውንም ነገር አቅርበንላቸዋል ። እኛም ራሳችን ብንሆን ሁሉንም ነገር አጠቃለን ያወቅንና የተራቀቅን ነበርን ብዬ ብናገር እንደ ቂልነት ይቈጠርብኛል ። ብቻ እነርሱ ሊከተሉት የሚያስችል አማራጭ ማስረጃ አቅርበንላቸዋል ።

የሆነ ሆኖ ሻለቃ ማርቲን በአይሮፕላን ሲበር በተነሳ በቱ ቀን አይሮፕላኑ ከባሕር ላይ እንደ ወደቀ በዚያኑም ቀን እንደ ተገኘ አድርገው ጀርመኖች እንዳመኑበት ሪፖ ርቱ ያመለክታል ።

በሚቀጥለው ሪፖርት ደግሞ ጉጉት አሳድሮብን ነበር ። አስቀድመን እንደገመትነው በሂውልባ ስለሚደረገው የጀ ርመኖችና እስፓንሾች የተባብሮ መሥራት ብቁነት ምን እንደ ነበረ ልንረዳው ችለናል ። ጽሑፎቹን ለማግኘት የጣሩ ክፍልና የባሕር ኃይሉ መኰንኖች የቱን ያህል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲወዛገቡበት እንደ ነበረና የእንግሊዝ ቆንሲል ደግሞ ደብዳቤዎቹ እንዲመለሱለት ሲል ያቀረበው ጥያቄ በምክ ንያት ቾላ እንደ ተባለ የተያዘው መዝገብ ያመለክታል ። ይህ ነገር እንደሚፈጠር በእስፓንኞች ላይ ጽኑ እምነት ነበረን ።

በመጨረሻም ለመረዳት እንደቻልነው የጀርመኑ ሰላይ ወረቀቶቹን እስከ ተመለከታቸው ድረስ በየነበሩበት ፖስ ታ እንደ ነበሩ ሆነው አልተመለሱም ነበር ። ስለዚህ ፖስ ታዎቹ እንዳልተከፈቱ ሆነው እንዲገመቱ ለማስመሰል የተደረገው ጥረት ምንም ሊያስደንቀኝ አልቻለም ፤ ይህ እንደሚሆን አውቀን ተገቢውን ጥንቃቄ አስቀድመን ፈጽ መን ነበርና ነው ።

እንግዲህ የጀርመንን የመረጃ ድርጅት በሚመለከተው ረገድ የሆነ እንደሆነ አቸንፈናቸዋል ። በእነርሱም በኩል ሆኖ ጉዳዩን ለተመለከተው "የማታለያውን የዘመቻ ቅቅል አኝከው ውጠውታል" የተባለውን ቃል ሊስማማ በት ይችላል ። በማንኛውም አኳያና ግምት ቢሆን የመ ረጃው ድርጅት ጠቅላላውን እቅዳችን እንደ ትክክለኛነት ቈጥሮታል ። ግን የጀርመን ጦር ጠቅላይ እዝ ክፍል ጦር ነቱ ሲሲሊ ውስጥ እንደሚደረግ አምኖበት ዝግጅቱን ቀጥ ሎበት ቢሆን ኑሮ ይህ ነው የማይባል የክብር ድል አድራ ጊነት ይጐናፀፍ ነበር ። ግን የኛን ንፍሮ ቅመው አኝከው ውጠውታልና ተጠቃልለው ወደ ክተማቸው ገብተዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የጀርመን የጦር አዛዥ መዋተት ።

ታምብች ብተባለችው የጀርመን ክፍለ ሃገር በነበረው የጀርመን የባሕር ኃይል መዝገብ ቤት ውስጥ ባደረግነው ፍተሻና ጥናት የሰበሰብነው መረጃ እንደሚያመለክተው የማታለያው ዘመቻችን በጀርመን የጦር አዛዥ ዘንድ ያስከተለውን ጉዳይ ለማወቅ አስችሎናል ። የተገኘው ውጤት እኛ ካሰብነውና ተስፋ ካደረግነው የላቀ ነበር ።

የተባበሩት መንግሥታት ጦር ቱኒዚያን ከያዘ በኋላ የት እንደሚሄድ ምን እንደሚፈጽም ጀርመኖች ያውቃሉ ብለን የገመትነው ሐሳባችን ልክ ነበር ። ግን መልሰው ሠረዙት ። ይደርስብናል ብለን ያሰብነውንም ችግር በአንስተኛ ደረጃ ተመልክተነው ኑሯል ። በመዝገብ ቤታቸው ውስጥ የጀርመን ጦር አዛዥ በየካቲት ወር ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. ቱኒዚያ ለነበረው ጦር አዛዥ ያስተላለፈውን መልእክት ግልባጭ አግኝተነዋል ።

የሚቀጥለው ዘመቻችን በሜዲትራኒያ ባሕር አካባቢ እንደሚሆንና ምናልባትም ሲስሊን ለመያዝ ሳይሆን እንደ ማይቀር አምነውበት ዝግጅታቸውን ቀጥለዋል ። ሲስሊን ከያዝንም በኋላ በተከታታይነት ክሬትን፣ ሳርዲኒያንና ኮርሲካን ለመያዝ እንደምንዘምት ተረድተውታል ።

ስለዚህ እኛም ለንደን ውስጥ ሆነን የጦርነቱን እቅድ ስናቀነባብር በነበረበት ጊዜ ጀርመኖች የመከላከያ ኃይላቸውን በሲስሊ ውስጥ ሳያጠናክሩ እንደማይቀሩ ያሰብነው ልክ ኑሯል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በምዕራብ ሜዲትራኒያም በኩል ዝግጅታችን ሲከና ወን በነበረበት ወቅት ክሬትን ለመውረር እንዳልሆነ አው ቀውትኣ ነበር ። በዚህ በኩል የነበረን አስተሳሰብ በትክክል ኑሯል ። ግን በመልእክቱና በሪፖርቱም ላይ ሐሳባቸውን ሲያጠቃልሉ "ስለ እንግሊዞ አሜሪካን የጦር ኃይል የወረራ ዝንባሌ ጉዳይ ከልዩ ልዩ ክፍል የሚተላለፍልን ሪፖርት እንደሚያመለክተው ጠላት በከፍተኛ ዝግጅት የሚከናወን የማታለያ እቅድ እንደሚያዘጋጅብን ተረድተነዋል" ይላል። ስለዚህም ጉዳይ ቢሆን ጀርመኖች ትክክለኞች ነበሩ ።

ዳሩ ግን ጀርመኖችን እንደምን ለማታለል እንደሚ ቻል የጦሩ የበላይ አዛዥ ያውቅ ነበር ? እኛም የማስመሰ ያው እቅዳችን እንደምን ለማከናወን እንደምንችል በእ ርግጥ ያስቸግረን ነበር ።

የተያዘው መረጃ እንደ አረጋገጠልን በዚህ እምነታ ቸውና እቅዳቸው እስከ ግንቦት ወር መጀመሪያ ፲፱፻፵፫ ዓ፡ም ድረስ ሲሠሩበት እንደ ነበረ አውቀናል ። ግን ግንቦ ት ፱ ቀን ጠቅላላው እቅዳቸው ተለወጠ ። ይህም የሆነው ከሻለቃ ማርቲን ጋር የተያዘው ደብዳቤ ዜና ከጦሩ ዋና አዛዥ ዘንድ ከቀረበለት በኋላ ሆነ ።

ግንቦት ፱ ቀን የጀርመን የመረጃ ድርጅት ጉዳዩን ለጦሩ የበላይ አዛዥ ካቀረበለት በኋላ ስለ ሆነው ነገር ግንቦት ፲፬ ቀን የተጻፈውን ቀጥሎ ያለውን ጽሑፍ አግ ኝተናል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሪፖርቱ፤ ቀደም ሲል በቍጥር 2144/43 በ9-5-43 ያስተላለፍኩትን ትእዛዝ ይጠቅሳል ። ለደረሰን ጠቅላላ ጉዳይ የሚከተለው ጥናት ተጠስዶበታል ።

፩ኛ በሚዲትራኒያ ምሥራቃዊና ምዕራባዊ አቅጣጫ ስለሚደረገው ወረራ በሰፊው የሚታሰብበትና የሚጠና ነው ።

ሀ. በጄኔራል ዊልሰን እዝ ሥር የሚመራው ጦር በምሥራቅ ሜዲትራኒያ በኩል የሚደረገው ወረራ የካላማታ አቅራቢያና በአራክሶስ ደቡብ ጠረፍ የሚከናወን ይመስላል ። ለዚህም እንዲረዳ የ፵፮ኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ወደ ካላማታ አዛውሮ እንዲያርፍ እንደዚሁም ፫ኛው እግረኛ ክፍለ ጦር በኬፕ አራክሶስ እንዲሠፍር መደረጉ ኃይል ለማጠናከር መታሰቡን ያመለክታል ። ግን ክፍለ ጦሮቹ በከፊል ወይም በሙሉ አቋም የሚላኩ ለመሆናቸው ገና አልታወቀም ።

ጉዳዩን በዝርዝር ስንመለከተው ግን ፵፮ኛው እግረኛ ክፍለ ጦር ከታለመው ቦታ ደርሶ እስኪለማመድና እስኪጠናከር ድረስ ከ2-3 ሳምንታት ጊዜ ያስፈልገዋል ።

ይህ እቅድ ከመፈጸሙ በፊት በአንዳንድ ምክንያት ሊዘገይ ይችላል ። ይህም ሊታወቅ የሚችለው ደብዳቤው ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ነው ። የሆነ ሆኖ ወረራው ከሁለቱም ክፍለ ጦሮች በተውጣጡ ልዩ ተዋጊ ጓዶች የሚከናወን ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ሊፈ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጸም ይቻላል ። ይኸውም ከ፺ኛው አግረኛ ክፍለ ጦር አንድ ብርጌድ ፣ ከ፫ኛው አግረኛ ክፍለ ጦር ደግሞ አንድና ሁለት ብርጌድ ጦር ተዋቅቶ ምናልባት ተዘጋጅቶም ሊሆን ይችላል ። ይህም ጦር ምናልባት ከታወቁት ቀበሌዎች (ግብፅና ሊቢያ) ተመድቦ ይሆናል ። የምሥጢር መጠሪያውም "ሐስኪ" ተብሎ የተጻፈው የአንግሎ አሜሪካን የጦር አዝ ቡድን በጀኔራል ዊልሰን አዝ ሥር የሚገኘው ጦር የዶዴካኒስን ቀበሌዎች እንዲያጠቃ ተመሳሳይ የዘመቻ እቅድ ለማውጣት አስበዋል ማለት ነው ። በዚህ እቅድ ላይ በ፳፫/፬/፵፫ የነበረው የዊልሰን እቅድ ተቀባይነት አላገኘም ማለት ነው ።

ሰ በምዕራብ ሜዲትራኒያ በኩል የጀኔራል አሌክሳንደር ጦር ስለሚኖረው ዒላማ አልተጠቀሰም ። ለቀልድ ያህል በደብዳቤው ላይ ሳርዲኒያ ተጠቅሳለች ። ለዚህ ዘመቻ የተሰጠው የምሥጢር መጠሪያ "ብሪምስቶን" ተብሎ ነው ። ለማታለያው ዘመቻ "ብሪምስቶን" የተባለችው ግን "ሲሲሊ" ናት ።

፬ኛ ይህ ዜና የመነሰጸ ነገር እንዳይሰማ በተቻለ መጠን መጠበቅና ዜናውም ሊተወሰኑ ባለ ሥልጣኖች ብቻ እንዲነገር መጠንቀቅ ቃላቅ ምሥጢር መሆኑን አውቆ መጠበቅ መሠረታዊ ግዴታ ነው" ይላል የጀርመኖቹ ሪፖርትና አስተሳሰብ ።

ሁኔታውን በዝርዝር ስመለከተው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሪፖርት ቃላቅ ደስታ አጐናጽፎኛል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አስቀድሞ ማድሪድ የነበረው የጀርመን ሰላይ ነገሩን አማትቶታል ። ሎርድ ማውንትባተን ለአድሚራል ከኒንግ ሃም የጻፉትን ደብዳቤ ለጄኔራል አይዘንሃወር የተጻፈውን ደብዳቤ ያህል አስፈላጊነት አይኖረውም ብሎ ግልባጩን ለመላክ ተቸግሮበት ኑሩዋል ። ይህን ያሰበውስ ምናልባት በዳፒ ጦርነት ያልተሳካልን መስለን ለመታየት በማሰባች ንና ይህንኑም በመጥቀሳችን ነገሩን ንቆት ይሆን? ነገር ግን በተራ ቍጥር አንድ በለ ክፍል በተገለጸው ዐረፍተ-ነገር እኔ ለቀልድ ስል የሳርዲኒያን ጦርነት የጠቀስኩት ግምት ተሰጥቶታል ። "በቀልዱ ደብዳቤ ላይ ሳርዲንያ ተጠቅሳ ለች" ተብሏል ። ያም ሆነ ይህ የጀርመን የመረጃ ክፍል ድርጅት ያቀረብንለትን የማታለያ ድብልቅ ቅቅል አኝኮ ውጦልናል ። በዚህ መሠረት ጠቅላይ የጦር አዛዡም የመ ረጃ ክፍሉን አስተያየት ተቀብሎታል ። ለተደረገልን ለዚያ ሁሉ እምነትና በጎ ሥራም ሂትለርንም ጭምር ሳናመሰ ግን አናልፍም ። ከአድሚራል ደንቲዝ ማስታወሻ ላይ እንዳገኘነው በኛ የማታለያ ደብዳቤዎች ላይ ራሱ ሂትለር እንደ ትክክለኛ አምኖባቸው ኑሩዋል ። የነገሩትንም ሁሉ ተቀብሏል ።

በሰሜን አፍሪቃ ውስጥ ያ ሁሉ እልቂት ከደረሰባ ቸው በኋላ የሙሶሊኒን ኃይል ለማጠንከርና ሙሶሊኒንም ለማጽናናት አድሚራል ዶንቲዝን ሂትለር ወደ ኢጣሊያ ልኮት ነበር ። አድሚራሉም ከጀርመን ከተመለሰ በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

በጠቅላይ ጽ/ቤት ሆኖ ስለ ተያዙት ደብዳቤዎቻችን ሪፖር ቱን ለሂትለር አስተላለፈ። ግን ጽሑፎቹን ራሱ አላነበባ ቸውም ነበር።

ስለ ጠቅላላው "እንግሎ አሜሪካን ዝንባሌ" ሙሶሊኒ የነበረውን አስተያየት እንዲገልጽለት ሂትለር ዶንቲዝን በጠየቀው ጊዜ በሰጠው መልስ ውስጥ ሲስሊን ለመው ረር እኛ እንደምናስብና ከዚያም ሐሳባችን እንደማንገታ ሙሶሊኒ የሚያምንበት መሆኑን ገልጾለታል። በዚህም ጊዜ ራሱ ሂትለር ቀጥሎ ያለውን መልስ የነገረው መሆ ኑን በግል ማስታወሻው ጽፎታል።

"ዱቼ ሲስሊ ትወረራለች (ትያዛለች) ብሎ የሚያም ንበትን አስተሳሰብ ፉሕረሩ (ሂትለር) አይስማማበትም። ከዚህ ይልቅ እንግሊዞች ሳርዲኒያንና አካባቢዋን ለመው ረር እንደሚያስቡ የተገኘው ማስረጃ ሊታመንበት የሚ ቻል መሆኑን አምኖበታል" ይላል።

እኛን ግሪክን ይይዛሉ በሚለው አስተሳሰብ ላይ ሂት ለር ፈጽሞ አምኖበት እንደ ነበረ ተረድተናል። የተባበ ሩት መንግሥታት የጦር ኃይል ሲስሊን ከያዘ አስራ አም ስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሐምሌ ፳፫ ቀን ዝነኛ ውን የጦር መሪውን ጀኔራል ሮሚልን ቢግሪክ በኩል ለዘ መተው ጦር አዛዥ እንዲሆንለት ሾመው።

ሮሚልም ሐምሌ ፳፭ ቀን ወደ ግሪክ ሄደ። ወዲያ ውም ሙሶሊኒ ከሥልጣኑ በመፈንገሉ በኢጣሊያ ውስጥ የነበረውን የመከላከያ አቋም እንዲመራ ተመለሰ።



t.me/OLDBOOKSPDF

መቸም የሆነውን ሁሉ ነገር ጠቅልሎ ከሂትለር ላይ መጫንና በተፈጸመው ስሕተት እርሱን ብቻ መውቀስ ትክክል አይደለም ። ሂትለር የሙሶሊንን ሐሳብ ጠይቆ በተረዳበት ግንቦት ፲፬ ቀን የጀርመን የባሕር ኃይል የበላይ አዛዥ መኰንን ማስታወሻ እንደሚያመለክተው ከሆነ የጀርመን የጦር ኃይል አዛዥ መኰንኖች በኛ ደብዳቤዎች መሠረት ጉዳዩ ከተወያዩበት በኋላ ትክክለኛ ማስረጃዎች ናቸው ብለው ስለ ተማመኑባቸው ጦርነቱን የምንጀምረው በሳርዲኒያ እንደሚሆንና ምናልባትም የሚያመቸን ከሆነ በተገንጣይ ጦር ሲሲሊን እንደምንደበድብ ተማምነውበታል ።

ስለዚህ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ፡ም የጦር ኃይሉ አዋጊዎች ፤ የጦሩ የበላይ አዛዥ መኰንኖችና ራሱም ሂትለር በኛ ደብዳቤዎች ላይ መተማመናቸውን ተስማሙበት ። ስለዚህ የማስመሰያው ዘመቻችን አጥጋቢ ውጤት ሰጠ ። ያም ሥራችን በእንግሊዝ አሜሪካን የጦር ኃይል ዘንድ ምን ትርጉም እንደሰጠ ማረጋገጡ የኛው የራሳችን ድርሻ ነበር ።

የጀርመን እግረኛና የአየር ኃይል ምን ተግባር ሲያከናውን እንደ ነበረ ዝርዝሩን አላውቀውም ። ግን የጀርመን ፩ኛ የፓንዜር ክፍለ ጦር አንዳንድ ተግባር ሲሠራ እንደ ነበረ በማስረጃ ተረጋግጧል ። ይኸውም ይህ ክፍለ ጦር ትሪፖሊ ውስጥ ጠቅላይ ሠፈሩን ለማቋቋም ከፈረን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይ ተነስቶ ተጉዟል ። ይህም የተደረገው ከላማቃና አራ ክስስ ላይ የኛ ጦር እንዳይሠፍር ለመከላከል ተብሎ ነበር ። እንግዲህ ያን ያህል ርቀት ሊጓጉዝ የተሟላ የጎን ዜር ክፍለ ጦር ለማቋቋም የተፈጸመውን ብርቱ ድካም የተመለከተ ማንም ሰው እንደሚረዳውና ያንም ጦር ለጊ ዜው ከጦርነት ውጭ ማድረግ እና ሲስሊንም ለመያዝ እቅድ በናወጣም እንኳ ቅሉ የማታለያውን ዘመቻ ብቻ ማዘጋጀታችን የቱን ያህል የተፋጠነ ውጤት ለማስገኘት እንደቻለ ሊያነጻጽረው ይችላል ።

በተያዘው በጀርመን ቤተ መዛግብት ውስጥ ከገኘና ቸው ጽሑፎች ላይ እንደተረዳነው ደግሞ የጀርመን የው ጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለቱርክ መንግሥት አንድ ማስጠንቀ ቂያ ጽፎለት ኑሩዋል ። ያም ደብዳቤ ወታደሮችና የጦር መርከቦች ወደ ግሪክ ስለሚዘምቱና በቱርክ መንግሥትም ላይ ማናቸውንም ጉዳት እንደማያስከትሉ የቱርክ መንግ ሥት እንዲያውቀው የሚያብራራ ነበር ።

ጥንቃቄው የሚያመለክተን የጀርመን የባሕር ኃይል ዝግጅት የቱን ያህል ሰፊና ቀልጣፋ እንደ ነበረ ነው ። በዚህ አንጻር ደግሞ እኔ ባላውቀው ነው እንጂ የእግረኛ ውና የአየር ኃይሉ እቅድና መሰናዶ ከዚህ የበለጠ ግዙ ፍነትና ርቀትም ሊኖረው ይችል እንደ ነበረ በግምት ለመረዳት ይቻላል ፡ የባሕር ኃይሉን ዝግጅትና ቅልጥፍ ናም ቢሆን እንደዚህ ለመግለጽ የቻልኩት የዝርዝሩን አ ቋም የሚያስረዳ መዝገብ ቤት በማግኘታችን ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ግንቦት ፳ ቀን የጀርመን ባሕር ኃይል የበላይ አዛዥ በግሪክ በካላማታና በአክባቢዋ በ፫ አቅጣጫዎች ላይ የጀርመን የባሕር ኃይል እየተቀራረበ እንዲሰለፍ ትእዛዝ ሰጠ። ኢጣሊያኖች ይዘውት የነበረውን የግሪክን ምዕራባዊ ድንበር የጀርመን የባሕር ኃይል አዛዥ በቁጥጥሩ ሥር እንዲያደርግ ተወሰነ። ከዚህ ሌላ ደግሞ የጀርመን የወሰን መከላከያ ተዋጊ ክፍል በኢጣሊያኖች እገዛ ሥር ሆኖ እንዲሰለፍ ታዘዘ። በዚሁ ቀን ግሪክ ከጃቸው እንዳትወጣ ከወሰዱት እርምጃ አንዱ ይህ ነበር። የግሪክ ደሴቶች በኛ ኃይል እንዳይወረሩ ግን የነበረው ተስፋ ተዳክሞ የነበረው የጀርመን ኃይል ይከላከላል የሚል ነበር። ይህን ትእዛዝ ከሥራ ላይ ለማዋልም ልዩ ልዩ የባሕር ኃይል መጓጓዣና ተዋጊ መርከቦች እንዲዘጋጁ ተወስኖበት ነበር። ያ ሁሉ ዝግጅት የተከናወነው በሾለቃ ማርቲን ደብዳቤ መሠረት ነበር። በምሥራቅና በምዕራብ የሜዲትራኒያ አቅጣጫ የተባበሩት መንግሥታት ኃይል ጦርነት ያስነሳል ተብሎ ተገምቶ ስለ ነበረ በዚሁ አቅጣጫ መከላከል እንዲደረግ ለተሰጠው ትእዛዝ ምክንያት የሆነውን ማስረጃ የጠቀሱትም ''እስከ ዛሬ ድረስ ለወረራው የሚያገለግሉ የባሕር መጓጓዣ ሁለ ገብ ጀልባዎች የሚዘጋጁት በምዕራብ ሜዲትራኒያ በኩል ጦርነቱ እንደሚጀመር የታሰበበትና ከፍተኛ ዝግጅትም የሚከናወንበት መሆኑን ያመለክታል'' ብለው ነበር። እዚህ ላይ በማስመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰያው የዘመቻ ኢቅዳችን የተገበረውን ጉዳይና የዚህን ትእዛዝ መቀራረብ ለመገመት ይቻላል ።

በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ በሲሲሊ የነበረው የጀርመን የባሕር ኃይል ተዋጊ መርከብ ቡድን ወደ ሊገን ተዛወረ ፤ የኛም የምሬ ድርሻ እየተቀነሰ ሄደ ። በዚሁ ጊዜም ማና ቸውም ዝግጅት በምዕራብ ሜዲትራኒያ ክፍል መቀላጠ ፉም ቀጥሎ ነበር ።

የጀርመን የጦር ኃይል የበላይ እዝ ክፍል ዋና አዛዥ የነበረው ጀኔራል ኬትል ሰኔ ፲፬ ቀን በሂትለር ስም ያወ ጣውን ትእዛዝ እናገኘውማለሁ ። ከዚሁ ትእዛዝ ላይ በቀላሉ መረዳት የቻልኩትም ሳርዲኒያን ለመውረር ስንል ሲስሊን የማቃለያ እቅድ ማድረጋችን ምናልባት ተገን ጣይ ጦር አቅጣጫ ሊጠብቦ ደሴቷን ይይዛታል ተብሎ ታምኖበት የነበረውን መሠረት በማድረግ ነበር ። (ይህም ደግሞ ግንቦት ፲፬ ቀን በተሰጠው ውሳኔ ተገልጿል) ሌላ ው ያገኘነው ጽሑፍ የሚያመለክተው ደግሞ እጅግ የተ ጠናከረ የፓንዚር ተዋጊ ኃይል ለሁለት ወራት ያህል የሚበቃውን ዝግጅት አሟልቶ በሰኔ ወር ወደ ኮርሲካ እንደ ተላከና በሳርዲኒያና ኮርሲካ በኩል በተጨማሪ እን ዲከላከል በሂትለር ስም እንደ ታዘዘ ነበር ።

ሐምሌ ፱ ቀን የኛ ጦር ሲስሊን ከመያዙ ቀደም ብሎ ጀኔራል ኬየትል ለአድሚራል ዶንቴዝ ሰፋ ያለ ሐሳብ የሠፈረበት መልእክት አስተላልፎለታል ። ያም ጉዳይ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተባበሩት መንግሥታት ጦር በሜዲትራኒያ አካባቢ ለወ ደፊቱ ስለሚያከናውነው ጦርነት የሚያብራራ ነበር ። በኮ ርሲካ ሳርዲኒያና በሲስሊ በኩል ጦርነቱን እንደምንጀምር ገልጾታል ። (ይኸውም በአንድ ጊዜ ወይም ተራ በተራ ወረራውን እንደምናከናውን በመተንተን ነበር) እንደዚ ሁም ግሪክን ለመያዝ ጦርነት ማድረጋችን እንደማይቀር ተገልጿል ።

በሰሜን አፍሪቃ የነበረው የተባበሩት መንግሥታት ጦር ኃይል ከላይ በተደጋጋሚ የተገለጹትን ጦርነቶች ለመጀመርና ወረራውን ለማቀላጠፍ በቂ አቋም ይኖረ ዋል የሚል እምነትም ጄኔራል ዶንቲዝ ነበረው ። በተጨ ማሪም (የኢጣሊያ ደሴቶች ከተያዙ በኋላ) በኢጣሊያ ድንበር ከፍተኛ ኃይል እንደምናሠፍር ተረድቶታል ። በግሪክ በኩል የነበራቸው ጦር በተተከለ ኃይልና በስንቅ በኩል ቀሰስተኛ በሆነበት ወቅት በኢጣሊያ በኩል ጀር መኖች የነበራቸው እንቅስቃሴ የተቀላጠፈ ነበር ።

የብለ ቃል ኪዳኑ ጦር ግሪክን ከወረረ በኋላ ሮማኒያን እንደሚይዝ፣ በዚህም ምክንያት በሁንጋሪያና በሮማኒያ የሚኖረው የፖለቲካ ውጤት የላቀ እንደሚሆን ተረድቶ ውታል ። በመጨረሻም አድሚራል ዶንቲዝ በጀኔራል ኬትል ሐሳብ ተስማምቶበት ከሥራ ላይ እንዲውል ወስ ኗል ። ያም የመደምደሚያ ሐሳባቸው "በምዕራብ በኩል ጦርነቱ በፍጥነት እንደሚጀመር ተረጋግጧል" የሚለው



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ይህም በማንኛውም ሰዓት እንደሚሆን አረጋግጠ ዋል (እዚህ ላይስ አስተሳሰባቸው ልክ ነበር) ቀጥሎ ደግሞ በምሥራቅ በኩል ያለው የተባበሩት መንግሥታት ጦር ገና በመደራጀትና በመቋቋም ላይ ነው ብለዋል፤ (ይህ አገ ላለጽ ግን ስሕተት ነበር፤ ገና በመቋቋም ላይ ነው የተባ ለው ጦር ነበር ሲስሊን ለመያዝ በትደረገው ዘመቻ ተካ ፋይ የሆነው) ሐምሌ ፲ ቀን ጥዋት ሲስሊ በኛ ጦር ተያ ዘች ። ቢሆንም ዋናው የውጊያ ስልታችን ይህ እንደ ነበረ ጀርመኖች አሁንም አላሙኑም ነበር (የተያዙት ደብዳቤ ዎችም ማታለያዎች እንደሆኑ ገና አልተጠራጠሩም ።)

በጅብራልታር ከነበረው ኃይላችን ወደ ኮርሲኮና ሳር ዲኒያ የሚዘምት ጦር እንዳለ የጀርመን ሰላዮች እንዲከታ ተሉ የጀርመን ጦር የበላይ አዛዥ ትእዛዝ ሰጠ ። ምክን ያቱም እነርሱ የነበራቸው እምነት ሲስሊ ስትያዝ (በከፊ ልም ቢሆን ያልጠበቁት ነገር ስለ ሆነባቸው) የዋናውን ጦርነት አቅጣጫ ለማስለወጥ እንዳደረግነው አስመስለው ነበር ። ነገር ግን ሐምሌ ፲፪ ቀን የሲስሊ መያዝ ሁለት ናትቀ ስለ ሆነው ዋናው የጦርነት ዒላማችን እንደ ነበረች ለማ መን ተገደዱ ። ከተያዘው መዝገብ ቤታቸው ውስጥ ሁለት የመልእክት ግልባጮች (ቀሪዎች) አግኝተናል ። እነዚያም ደብዳቤዎች ኢጣሊያ ውስጥ የነበረው የጀርመን የባሕር ኃይል አዛዥና በባሕር ኃይሉ የበላይ አዛዥ መካከል የተ ለዋወጡ ነበሩ ። በደብዳቤዎቹ ላይ ለመረዳት እንደቻል



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ኢጣሊያ ውስጥ የነበረው የባሕር ኃይል ዋና አዛዥ ከሲሲሊ ወደ ኤጌን ግሪክን ከተባበሩት መንግሥታት ጦር እንዲከላከሉ ተዋጊ መርከቦች መላካቸውን በጥብቅ ተቃውሟል ። ተዋጊ መርከቦቹ ከሲስሊ በመነሳታቸው ጠረፉ ያለ ቁጥጥር በመሆኑ ለመከላከል ሳያስችል መቅረቱን ጨምሮ ገልጾታል ። ለወደፊቱም ቢሆን ተዋጊ መርከቦች ከሠፈሩበት አቅጣጫ ቢዛወሩ ለመከላከልም ሆነ ለተጠባበቂነት በቂ አቋም እንደማይኖራቸው አስታውቋል ።

በተሰጠውም መልስ ላይ የበለ ቃል ኪዳኑ መንግሥታት ጦር ምናልባት ሲሲሊን ለመያዝ እስኪዘጋጅ ድረስ ግሪክን ይይዝ ይሆናል የሚል ወታደራዊ ጥናትና አስተሳሰብ ስለ ነበረ፣ መሆኑ ተገልጾለታል ።

ግሪክ በተባበሩት መንግሥታት ጦር እንዳትያዝ የተደረገው መከላከል ለጊዜው በሁለተኛ ደረጃ የሚታሰብ እንደ ነበረ በተሰጠው መልስ ላይ በተጨማሪ ተገልጿል ። (ይህ የታሰበበት ምክንያት የማታለያው እቅዳችን ገና ተስፋ ያላስቈረጣቸው ተደማጭነት የነበረው ስለ ሆነባቸው ይሆናል ተሰሚነቱስ በሂትለር ዘንድም ነበር ይሆን?) በዚህ ጊዜ በተጨማሪ ወደ ኢጌን (የግሪክ ምሥራቃዊ የባሕር ጠረፍ ናት) እንዲላኩ ተሰናድተው የነበሩት ዐሥራ አንድ ተዋጊ መርከቦች በነበሩበት እንዲቆዩ ተወሰነና ኢጣሊያ ውስጥ በነበረው የባሕር ኃይል ዋና አዛዥ ትእዛዝ ሥር እንዲመደቡለት ሆነ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ አስቸኳዩ "የማታለያው ዘመቻ" ጉዞ ከግቡ ደረሰ። ግን ጀርመኖች ስለ ግሪክ አቋዋም በልዩ ልዩ ሐሳብ እየዋለሉ በተስፋ ይጠባበቁ ነበር። ስለዚህም ጉዳይ ቢሆን የተደረገው ጥናት በአጭሩ የሚከተለው ነበር።

የማታለያው ዘመቻ እቅድ ያወጣነውና ከግብም እንዲደርስ የሠራነው ሰዎች በአጭሩ ጀርመኖችን ሲረዱ የነበሩትን እስፓንሾች አታለንበታል። እስፔይንና በርሊን ውስጥ የነበሩትን የጀርመን የመረጃ ሠራተኞች አታልለንበታል። የጀርመንን የዘመቻና ጠቅላይ የጦር እዝ ጽ/ቤት አታልለንበታል። የጀርመንን ጦር የበላይ አዛዥ ጀኔራል ኬትልን አታልለንበታል። በመጨረሻም ራሱን ሂትለርን አታለነዋል። እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ ድረስ ከእጃችንና ከሐሳባችን ነቅቶ አልወጣም ነበር።

የምሥራቅ ሜዲትራኒያን ቀበሌ በሚመለከተውም ረገድ የሆነ እንደሆነ ግሪክን እንወራለን ብለን ዝግጅት በመጀመራችንና እውነት እንዲመስልልንም በሰፊው በመጣጣራችን እንደ እውነትና ትክክል ስለ ተገመተልን የጀርመን የመከላከያ ኃይል በዚያው እንዲሠፍር አድርገናል። የዚያ የተከማቸው ጦርም አዛዥነቱ ለፊልድ ማርሻል ሮሜል እንዲሰጥ ምክንያት ፈጥረን ሂትለርን አስገድደነዋል። በግሪክ የተከማቸው ጦርና አውሮፓን አቋርጦ ሊሸጋገር ተዘጋጅቶ የነበረው የፓንዜር ክፍለ ጦር በግሪክ እንዲከማች በመደረጉ የጀርመንን የጦር ስልት



t.me/OLDBOOKSPDF

አቃውሰነዋል ። ገንዘቡንና ጉልበቱንም መንግሥቱ ሠጡ ቶበታል ። በዚህም ምክንያት የሲስሊንና የኢጣሊያንን መሠረታዊ የመከላከያ ኃይል አስለቀቅነዋል ።

የሜዲትራኒያን ምስራቡዊ አቅጣጫ በሚመለከተው ረገድ ደግሞ ፣ ሲስሊን በመሥዋዕትነት ተቀብለን ጀርመኖች በኮርሲካና በሳርዲኒያን በኩል ብርቱ ብርቱ ምሽጎች እንዲሠሩ ተተኪ ኃይል እንዲከማችባቸው ለማድረግ እንዲገደዱ ምክንያት ፈጥረናል ። በሲስሊ ተከማችቶ የነበረው የጀርመን ኃይል ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲዛወርልን በደሴቶቹ አካባቢ የተባበሩት መንግሥታት ጦር ይይዛቸዋል ብለን የፈጠራ ዘመቻ በማቅረባችን ሲስሊን በነፃ እስከ መያዝ ያደረሰ እቅድ አውጥተን ጀርመኖችን አሳምነናቸዋል ። በዚህም የተነሳ በሲስሊ የነበሩት የጀርመን ተዋጊ መርከቦች ወደ ኢጌን ኢንዲዛወሩ አድርገናል ። ሲስሊም ያለ መከላከያ ኃይል እንድትቀርና የጀርመንን ታላላቅ መርከቦችም ኢጅበው በየውቅያኖሶቹ የሚርመሰመሱ የጦር መርከቦች እጥረት እንዲደርስ አድርገናል ። ይህ ሁሉ ውጤት የተገኘው የጊዜው ሁኔታ አስገድዶን በፈለሰፍነው የፈጠራ ጽሑፍ ምክንያት ነው ። የፈጸምነው ጥረትና ያስገኘውም ውጤት ታላቅ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ ። ነገሩን ስንጀምረው ካሰብነው ውጤት እጅግ የላቀ የድካም ፍሬ አግኝተንበታል ። በዚህ "ባልነበረው ሰውዬ" ወይም (በሬሳው ሰላይ) ምክንያት ስንትና ስንት



t.me/OLDBOOKSPDF

የእንግሊዞችና አሜሪካኖች ሕይወት ከእልቂት እንደ ተረፈ ሌሎችም ሊያውቁት ይገባቸዋል ። እቅዳችንና ጥረታችን ተዳምሮ ሲስሊን ያለ እልቂት ለመያዝ እንዳስቻለንና ለጠቅላላው በጦርነቱም ምን ውጤትና ለውጥ እንዳስገኘ ሌሎችም እንዲያውቁት ለማድረግ ከዚህ የበለጠ ምስክር የለም ።

ተ ፈ ጸ መ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በእስፔይን ውስጥ በምትገኝ ትንሽ ከተማ የመቃብር ቦታ ውስጥ የአንድ እንግሊዛዊ ሬሳ ለዘለዓለም አንቀላፍቷል ። ሰውዬው በሕይወት በነበረበት ጊዜ ለሃገሩ የፈጸመው አገልግሎት መጠነኛ ነበር ። ከሞተ በኋላ ግን ብዙዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሚፈጽሙት ይበልጥ ቃላት ተግባር ፈጽሟል ።

"ያልነበረው ሰውዬ" ወይም (ሰላዩ ሬሳ) እጅግ አስደናቂና አስገራሚ ታሪክ ነው ። በጣም የተራቀቀ ጥልቅ ችሎታና ዐይናውጣነት የተቀላቀለበት ከትሮይ የፈረስ ምስል ወዲህ በጦርነት ታሪኮች ውስጥ የተፈጸመ የሰላይ ተሰላይ ውጤት ነው ።

"በውትድርና ታሪክ ውስጥ በቅርብ ዘመን ከተፈጸሙት የማታለል ታሪኮች እጅግ አንግዳና አስገራሚ የሆነ ረቂቃዊ ስለላ ነው" ።



t.me/OLDBOOKSPDF



## እኔ እንደማምንበት ።

ስለ የክፍሉ ሥራ በአንድነት መወያየትና መነጋገር የተጠቃለለ ዘላቂ የሆነ የሥራ ውጤት ያስገኛል ።

በጋራ ዓላማ ላይ ግለኛ ሆኖ መታየት ፣ በየብቻ ሠርቶ የተለየ ዝናና ውዳሴ ለማግኘት መባዘን ግን ራስን፣ አካባቢንና ጠቅላላ አቋምን ሊያዛባ ይችላል ።

ማሞ ውድነህ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

## ከዚህ ቀደም
## ያሳተምኩዋቸው መ[illegible]ፍት ፡


፪ኛው የዓለም ጦርነት
የሲቲን ፈተና
ከወንጀለኞች አንዱ
ቤኒቶ ሙሶሊኒ
የበረሃው ተኩላ
የገባር ልጅ
ሁለቱ ጦርነቶች
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]

የ፮ቱ ቀን ጦር[illegible]ት
[illegible]ቡብ ሱዳን ብጥ[illegible]ጥ
[illegible]ር ን[illegible]ዋዛ
[illegible]ንትጎመሪ
የ[illegible]ሪክ
የኛ ሰው በደማስቆ
ምጽአተ እስራኤል
የአደ[illegible] ማኅደር
ከዳተኞቹ
ከሕይወት በኋላ ሕይወት
[illegible] ሰላዮች
ም[illegible] ምርጥ ሰላዮች
[illegible]ኞቹ
[illegible] ናቸው ።


t.me/OLDBOOKSPDF